# ፀላዒ ጽልመት - አፍቃሬ ብርሃን

ደምስ ሠይፉ
sebaradildiy@gmail.com



## እንደ ድልድይ

14 ዓመታትን ወደ ኋላ ተጉዤ አንድ የጊዜ ወደብ ላይ መልሕቄን ጣልኩ ... በስነጽሑፉ ዓለም በተለይም በስነ-ግጥምና በተውኔት መድረክ ላይ ይንቦገቦግ የነበረ ደማቅ ብርሃን የደበዘዘበት ዓመት ነበርና እዝን ማለቴ አልቀረም፣ 1992 ዓ.ም!! በዚህ ዓመት ኪነጥበብ ከባለውለታዎቿ አንዱን ተነጥቃለች፤ ስነግጥም ከመድብሏ አንድ ዕጹብ ቅኔ አጉድላለች፤ ቲአትር የመድረክ ፈርጧን አጥታለች፤ ከብርሃን ጋር በፍቅር የወደቀ፣ ብርሃንን ምልክቱ - ቅኔውና ተምሳሌቱ አድርጎ የነበረ ሰው ነፍስ ተነጥቃለች።

ለግማሽ ምዕተ ዓመት ብቻ ተለክታ በተዘረጋች የሕይወት መንገዱ ሲመላለስና በስነጽሑፉ ዓለም ሰማይ ላይ እንደ ተወርዋሪ ኮከብ በብርሃን ሲዋኝ የነበረው ይህ ቋሚ የስነጽሑፋችን ሐውልት ማነው? የት ተወለደ? ምን ሰራ? ... እያልን ወደ መቋጫችን በደራሲው ስም ምስጋናችንን ከምንቸራቸው በርካታ የሕትመት ውጤቶችና የመድረክ ገለፃዎች ላይ በቀጥታ የተወሰዱ እውነታዎችን እንጋራለን፤ ግና ጥንቅሩ ከደራሲው የሕይወት ክብ ውስጥ ሲሶ ያህል ያህል ብቻ የተሸረፈ መሆኑ ልብ ይባልልኝ።

## ልጅነት

1942 ዓ.ም. ወርሃ ሐምሌ፤ ጠቆርቆር ባለ ደመና በሚያጉረመርም ሰማይ የምናውቀው 11ኛ ወር፣ ከወሩም 5ኛ ቀን።በዚህ ዕለት አባቱ በጅሮንድ ሰይፉ አንተን ይስጠኝም ሆነ እናቱ የማርያም ወርቅ አስፋው ዕድሜ ልኩን በብርሃን ፍቅር የሚዋትት ሕፃን ከቤታቸው ስለመገኘቱ አልጠረጠሩም።በዚህ ዕለት የይርጋለም ከተማ ከራሷ አልፎ አቢሲኒያን የሚያካልል ፀሐይ ያውም በወርሐ ሐምሌ ይሰርፃል ብላ አልገመተችም።ግና ሆነ... በዚህ ዕለት ለቤተሰቦቹ ክብር፣ ለይርጋለም ኩራት፣ ለአቢሲኒያ ሐውልት የሆነው ደበበ ሰይፉ ተወለደ።

**ይርጋለም**

**<<ዋ... ይርጋ-ለም**

**የልጅነቴ ሕልም ቀለም**

**ዓይኔን የከፈትሽው ጨረር**

**ወርቅማይቱ ጀንበር ...>>**

ደበበ ገና ከልጅነቱ ፊደል ዕጣው የሆነ ጎበዝ ተማሪ ነበር።ዳዊትን ለመድገም ጊዜ አልወሰደበትም፤ አባቱ ከቄስ ት/ቤት አውጥተው መደበኛ ት/ቤት እንዲገባ ሲያደርጉት ልበ-ብሩህነቱን አይተው እዚያው የቤተክርስቲያን አገልጋይ ሊያደርጉት አስበው የነበሩት የኔታ በጣም አዝነው እንደነበር የደበበ እናት ያስታውሳሉ።

አባቱ አዲስ አበባ ደርሰው ሲመለሱ መጻሕፍትና መጽሔቶች ገዝተው ይመጡ ስለነበር ይህ ለደበበ ገና ከልጅነቱ ከፍተኛ የማንበብ ፍቅር እንዲያድርበት ከማድረጉም ሌላ ቲአትርና ሌሎች ዝግጅቶች በሚኖሩ ጊዜ ልጆቻቸውን ይዘው የመሄድ ልማድ ስለነበራቸው በማለዳ ነበር በቲአትር ፍቅር የተነደፈው።4ተኛ ክፍል እያለ ከእህትና ወንድሞቹ ጋር መጋረጃ ጋርዶ ድራማ ይሰራ እንደነበር እናቱ ያስታውሳሉ፤ በተለይ ደግሞ "ወ/ሮ ዓለም" ከተሰኘ መጽሐፍ ላይ ቃለ-ተውኔት እየወሰደና ተዋናይ እየመለመለ ለታላላቆቹ ድራማ የማሳየት ልምዱ የማይዘነጋቸው ነው።

ደበበ ከልጅነቱ ጀምሮ ከሰው ተገልሎ የመቀመጥ ልማድ ነበረው፣ ብቻውን ወራጅ ወንዝ እያየ መቀመጥ ያስደስተው ነበር።ምንም እንኳ ከቤተሰቡ ጋር ጥብቅ ግንኙነት ያለው ቢሆንም የግሌ የሚለውና ብቻውን በተመስጦ ወይም በንባብ የሚያሳልፍበት ሰፊ ጊዜ ነበረው።ታምራት እጅጉ የተባሉ ጓደኛው ሲናገሩ "ደበበ የልጅነት ትዝታዎቹን አውርቶ አይጠበግባቸውም፣ ስለ ይርጋለምና የልጅነት ዘመኑ ሲያነሳ ብትሰማ ፈዘህ ትቀራለህ - ስሜቱ ይሞቃል" ብለዋል።

## ደበበ እንደ ተማሪ እና አስተማሪ

ደበበ ይርጋለም ከተማ ራስ ደስታ በሚባል ት/ቤት የስምንተኛ ክፍል ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ ቤተሰቡ ወደ አዲስ አበባ በመዛወሩ የ2ተኛ ደረጃ ትምህርቱን በኮከበ ጽባህ ት/ቤት ሊያጠናቅቅ ችሏል፤ ቀጥሎም በቀድሞው የቀ/ኃ/ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ለአንድ ዓመት ያህል የቢዝነስ ትምህርት ከተማረ በኋላ በትምህርቱ ባለመደሰቱ ወይም በእርሱ አገላለጽ "አዕምሮን የማይቆነጥጥ" ትምህርት በመሆኑ ወደ አርትስ ፋኩልቲ ተዛውሮ ከኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል በስነጽሑፍ የመጀመሪያ ዲግሪውን በ 1965 ዓ.ም. ወስዷል።ከ 5 ዓመት በኋላም በዚሁ ዩኒቨርሲቲ የማስተርስ ዲግሪውን በእንግሊዝኛ ስነጽሑፍ በጥሩ ውጤት ተቀበለ።

የመጀመሪያ ዲግሪውን በማዕረግ እንደተቀበለ ከ 1966 ጀምሮ እስከ 1985 ዓ.ም. ድረስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመምህርነትና በረዳት ፕሮፌሰርነት ማዕረግ አገልግሏል።

ደበበ በቲአትር ጥበባት ክፍል ከ1981 — 1984 ዓ.ም. በሊቀመንበርነት ባገለገለበት ወቅት ብዙ ለውጦች አድርጓል፤ በምርምር ረገድም በኢትዮጵያ ስነ-ጽሑፍ ላይ በርካታ ምሁራዊ መጣጥፎችን በአማርኛና በእንግሊዝኛ አበርክቷል።ለዚህም ለማስተርስ ዲግሪው ያቀረበው "የኢትዮጵያ ስነጽሑፍ በእንግሊዝኛ ቋንቋ" ስራው ዋቢ ነው።

በኢትዮጵያ ሬዲዮ አማካሪና ረዳት አዘጋጅ እንደዚሁም ተርጓሚ የነበረው ደበበ ከፍተኛ የእንግሊዝኛ፣ መካከለኛ የፈረንሳይኛና አረብኛ ቋንቋ ችሎታ እንደነበረው ይነገራል።ያም ሆኖ ከአቅም በላይ ካልሆነ በስተቀር የውጭ ቋንቋ በቀጥታ በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ እየቀላቀሉ መጠቀምን ይቃወም ነበር።ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ ስለዚሁ ጸባዩ ሲናገር 'አማርኛን ስለማናውቀው ነው እንጂ ሰፊና ጥልቅ ቋንቋ ነው' የሚል አስተሳሰብ እንደነበረው አስታውሷል።በዚህም ምክንያት ለሙያዊ የስነ ጽሑፍ እሳቤዎች የሚመጥኑ ስያሜ ቃላት (Terminologies) በመፍጠር ይታወቃል።ለምሳሌ:- 'መቼት፣ ገጸባሕሪ፣ አያዎ እና ቧልታይ' የመሳሰሉት የሙያ ቃላት የእርሱ ፈጠራዎች ናቸው።

በተለያየ የሕይወት ልምድ፣ ተሞክሮና የኑሮ ደረጃ ላይ ከሚገኙ ሰዎች ጋር መገናኘት የሚወደው ደበበ በተለይ የታክሲ ሹፌሮች ወግ መስማት ያስደስተው ነበር፤ ለስራው ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጥ እንደመሆኑ ጥብቅ ስራ ከያዘ ሰው ማናገር ቀርቶ ማየት አይፈልግም ነበር።ለጽሑፍ ስራው ሌሊቱን የሚመርጠው ደበበ ለተወሰነ ሰዓት በጊዜ ተኝቶ በመነሳት እስከ ንጋት በጽሑፍ ስራ ያሳልፍ ነበር።ደራሲ፣ ሃያሲና የስራ ባልደረባው መስፍን ኃ/ማርያም ስለ ደበበ ሲናገር "በጣም ጠንካራ፣ ትጉህ ሰራተኛና ለተሰለፈበት ወደኋላ የማይል በማስተማር በኩል -ፈጣሪ (Innovator) ዓይነት ነበር" ብሏል።ተማሪው የነበረው ነቢዩ ተካልኝም "ስራውን ይወዳል፣ ውጤታማም ነበር፣ ብዙ ጊዜ ኢንፎርማል የሆነ ነገር ይመቸዋል፤ በራሱ መንገድ ነፃነት ይሰጠናል።ዲሞክራትም ነበር፣ ተማሪዎቹ ያከብሩታል፤ ጥሩ መምህር፣ አዋቂና ሊቀርቡት የሚችሉት ዓይነት ሰው ነበር" ብሏል።

ደበበ ካስተማራቸው ታዋቂ የጥበብ ሰዎች ውስጥ ጋዜጠኛና አርቲስት ተፈሪ ዓለሙና ጸሐፌ ተውኔት፣ ገጣሚና መራሔ ተውኔት ጌትነት እንየው ዋነኞቹ ሲሆኑ ጋዜጠኛ መሰረት አታላይ፣ ሙሉነህ መንግስቱ፣ አርቲስት ግሩም ዘነበ እና ገጣሚ መስፍን አሸብርም ተጠቃሽ ናቸው።በአሁን ሰዓት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በማስተማር ላይ የሚገኘው መ/ር ገዛኸኝ ጌታቸውም ከደበበ ሰይፉ ተማሪዎች አንዱ ነው።

### ደበበ እንደ ጥበበኛ

ደበበ በገጣሚነቱ በሰፊው የሚታወቅ ቢሆንም ፀሐፌ ተውኔት፣ ተርጓሚና የምርምር ባለሙያም እንደነበር የወግ ፀሐፊው ደራሲና ሐያሲ መስፍን ሃ/ማርያም በ "የብርሃን ፍቅር ቅጽ-2" መጽሐፍ መግቢያ ላይ ባሰፈረው ምስክርነት ያወሳል።ከመጽሐፍቱ ውስጥ "የቲአትር ጥበብ ከፀሐፌ-ተውኔቱ አንፃር" በሚል ርዕስ ያዘጋጀው ተጠቃሽ ስራውና ሎሬት ጸጋዬ ገ/መድህንን ከመሳሰሉ 17 ጸሐፍት ጋር ያሰናዳው "ጽጌረዳ ብዕር" የተሰኘ የግጥም መድብል የሚጠቀስ ሲሆን ቀደምት የግጥም ስራዎቹን የያዙት "የብርሃን ፍቅር ቅጽ-1" በ 1980 ዓ.ም. እንዲሁም "ለራስ የተፃፈ ደብዳቤ /የብርሃን ፍቅር ቅጽ-2" ደግሞ በ 1992 ዓ.ም. የህትመት ብርሃን ከጎበኛቸው ስራዎቹ ውስጥ እጅግ ተወዳጆቹ ናቸው።ደበበ በርካታ ወጥና ትርጉም የተውኔቶች ስራዎችን የፃፈ ሲሆን የተወሰኑትም ለመድረክ በቅተውለታል፤ ከስራዎቹ ውስጥም "እናትና ልጆች፣ ከባሕር የወጣ ዓሳ፣ እነሷና እነሱ፣ ሳይቋጠር ሲተረተር፣ የሕፃን ሽማግሌ፣ ክፍተት፣ ዕድምተኞቹና ጋሊሊዮ ጋሊሊ" ይጠቀሳሉ።"ክፍተት" የተሰኘው የትርጉም ተውኔት በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በተደጋጋሚ ታይቷል።ደበበ ለበርካታ ዓመታት የኢትዮጵያ ደራሲያን ማሕበር ሊቀመንበር ሆኖ ከመስራቱም ባሻገር "ብሌን" የተሰኘው የማሕበሩ መጽሔት አዘጋጅም ነበር።በቀድሞው የኩራዝ ሕትመት ድርጅት ውስጥ የቦርድ አባል ሆኖ ይሰራ እንደነበር ከዋነኞቹ ምንጮቻችን አንዱ የሆነው "ደማቆቹ " የባለታሪኮች ድርሳን ያወሳል።

ፊርጥ መጽሔት በባለታሪካችን ተማሪ በሆነው መሰረት አታላይ አማካይነት ስለ ደበበ ባሰፈራት መጣጥፍ "ገና በልጅነቱ ባገኘው ነገር ላይ፣ በወዳደቀ ወረቀትና በጋዜጣ ቅዳጅ ሳይቀር ግጥም መፃፍ ይወድ ነበር፤ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ እያለ ግጥም እና አጫጭር ልብ ወለድ ይጽፍ የነበረው ደበበ በአንድ ወቅት የምስራች የስነ ጽሑፍ ክፍል ባዘጋጀው የስነጽሑፍ ውድድር /ዘላለም/ የተሰኘ አጭር ልብወለዱ አንደኛ ወጥቶ ከሌሎች ጸሐፍት ስራዎች ጋር በአንድ ጥራዝ ታትሞለታል" ሲል ጠቢቡን አስታውሷል።

ደበበ ለሕትመት ያልበቁ በርካታ ስራዎች እንዳሉት ይነገራል።ከተማሪዎቹ አንዱ የሆነው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህሩ ገዛኸኝ ጌታቸው የደበበን የሕይወት ታሪክ በመጽሐፍ ለማሳተም እንቅስቃሴ እያደረገ መሆኑን ቆየት ባለ አንድ መርሐ ግብር ላይ ያስታወቀ ሲሆን ያልታተሙትን 29 የእንግሊዝኛ እና 34 የአማርኛ ግጥሞቹን በ3ተኛ ቅጽ ለማሳተምና በአማርኛ ስነግጥም ላይ ደበበ የሰራቸውን ሂሳዊ ስራዎች መግቢያና የግርጌ ማስታወሻዎች አክሎ ለማሳተም ከቤተሰቦቹ ጋር ስምምነት ላይ መድረሱን አዲስ ነገር ጋዜጣ ጽፎ ነበር፤ ይህ ጅምር የት ደርሶ ይሆን?...

ደበበ ስለራሱ የግጥም ስራዎች ሲናገር 'ግጥሞቼ ግልብ ናቸው' ቢልም ነፍሱን ይማረውና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የስነግጥም መምህር የነበረው ብርሃኑ ገበየሁ ግን 'በጭራሽ! እንዲያውም የደበበን ግጥሞች ጥልቀት እና የሃሳብ ረቂቅነት ስናጠናው ብንኖር እያደር እንደመማለን' ባይ ነበር።ሃያሲ ደራሲና የወግ ፀሐፊው መስፍን ኃ/ማርያም በበኩሉ ደበበ ሰይፉ በርዕስ አመራረጡና በሚያስተላልፋቸው ልብ የሚነኩ መልዕክቶች ብቻ ሳይሆን በስንኞች አወራረድ፣ በዜማና በቤት አመታቱ በአጠቃላይ በውብ አቀራረቡ ተደራሲያንን የሚመስጥ ገጣሚ ነው፤ ስለተፈጥሮ ሲገጥም ፀሐይና ጨረቃ፣ ቀስተደመናና የገደል ማሚቶ ያጅቡታል፤ ስለፍቅር ስንኞችን ሲቋጥር የፍቅረኞችን ልብ እንደ ስዕል ቆንጆ አድርጎ በቃላት ቀለማት ያሳያል።ክህደት ላይ እንደ አንዳንድ ገጣሚያን አያላዝንም፤ ይልቁንም ውበትና ሕይወትን አገናዝቦ 'ያውላችሁ ስሙት፣ እዩት' ማለትን ይመርጣል... በደልን አስመልክቶ ከፃፈ በደል በወፋፍራም እጆቹ ያነቃችሁ እስኪመስላችሁ ድረስ ይዘገንናችኋል... ;ብሏል።ተወዳጁ ጋዜጠኛ፣ ተርጓሚና ባለቅኔ ነቢይ መኮንንም ደበበ በሎሬት ጸጋዬና በገጣሚ ዮሐንስ አድማሱ መካከል የሚገኝ ገጣሚ ነው፤ እናም በሁለት ሰው መካከል የሚገኝን ሰው መተርጎም /መግለጽ/ ያስቸግራል ... ግጥሞቹ ሰውና ተፈጥሮ ላይ የሚያተኩሩ (ሮማንቲሲዝም / ወሸነኔያዊ) ናቸው፤ ብሶት ተኮር በሆነው አፃጻፉ ከዮሐንስ አድማሱ ጋር ይመሳሰላል; በማለት ምስክርነት ሰጥቷል።

## ደበበ እንደ ሰው

ደበበ በሃገራችን የኪነጥበብ ታሪክ ውስጥ ጉልህ ቦታ የነበረው ጠቢብ ቢሆንም የግል ሕይወቱ ግን እጅግ አሳዛኝ ነበር።አቶ ታምራት የሚባሉ የደበበ የዩኒቨርሲቲ ጓደኛ ስለ ደበበ ሲናገሩ 'ትዳር አለመያዙንና ልጆች አለማፍራቱን በመጥቀስ ከስነጽሑፍ ሌላ እምብዛም ለሕይወቱ የሚጨነቅ እንዳልነበር' አውስተዋል።'ሁሌም ከላይ የቆዳ ጃኬትና በቀላሉ ተስቦ የሚጠለቅ ጫማ ያደርግ የነበረው ደበበ በሁለት ልብሶች ብቻ ተጣብቆ እንደኖረ' ገልፀዋል።አመጋገቡንም በተመለከተ 'ምግብ ይበላ ነበር ማለት አይቻልም' ሲሉ ነበር የገለጹት።

ደበበ የባከኑ ሰባት ዓመታቶቼ ይላቸዋል ከ1986 እስከ 1992 ዓ.ም. ድረስ ያሉትን ተከታታይ ዓመታት፤ ምክንያቱ ደግሞ በህመሙ መባባስ ምክንያት ማንበብና መፃፍ እያቃተው የመጣበት ጊዜ ስለነበር ነው።በአንድ ወቅት የስነጽሑፍን ሰው ሲያዩ ስለጤንነቱ አሊያም ስለሌላ ነገር አይጠይቁትም፤ 'ምን ተፃፈ' ነው ሁሌም ... እስከሚያቅለሽልው; በማለት ከመከራዎቹ ጋር ብቻውን ለተውነው አንባቢዎቹ ወቀሳ ሰንዝሯል።በዚህ የጽኑ ሕመም ዘመኑ ከቤት እንኳ መውጣት ያቅተው የነበረ ሲሆን ማስተማር ማቆሙን ተከትሎ ከዩኒቨርሲቲው ፈርሞ የተረከባቸውን ጠረጴዛ፣ መጋረጃና ወንበር መልሶ ፋይሉን ነፃ ባለማድረጉ / ወይም ደግሞ የሚያደርግለት ባለማግኘቱ/ ባለዕዳ የሚል ሰነድ ከፋይሉ ጋር ተያይዞ እንዳለ መስማት በእውነት ያማል።መ/ር ገዛኸኝ ይህንኑ ለአዲስ ነገር ሲገልጽ "በዩኒቨርሲቲው የሚገኘው የደበበ ፋይል 15 ጠረጴዛዎች፣ 18 ወንበሮች፣ 2 ሼልፍ፤ 4 መጋረጃ፣ 1 ምንጣፍ፣ 1 ታይፕ ራይተርና 1 የጠረጴዛ መብራት ዕቃዎቹ እዚያው ቢሮው እያሉ ተመላሽ ባለመደረጋቸው ብቻ ባለዕዳ አሰኝተውታል" ብሏል።ማንኛውም ሕሊና ያለው ሰው ለ 20 ዓመታት ያስተማረበትና ትውልድ የቀረጸበት ዩኒቨርሲቲ ያለ ጡረታ ማሰናበቱ ሳያንስ ፋይሉን ለማቆሸሽ መትጋቱን ሲያይ 'ጥናቱን ይስጥሽ እማማ' የሚለውን የራሱ የደበበን ግጥም በህሊናው ማመላለሱ አይቀርም:-

**<<. . . ሲታደጉሽ ካልታደግሽማ**

**ሲኖሩልሽ ከገደልሽማ**

**በራስሽ የጨከንሽ አንቺ!**

**ጥናቱን ይስጥሽ እማማ...>>**

ደበበ ምንም እንኳ አካሄዱና አጠቃላይ አተገባበሩ ባይዋጥለትም ለአብዮቱ ዘመን ድጋፍ ነበረው፤ በዚህ መነሻነትም በርከት ያሉ ግጥሞች ጽፏል።ይሁንና አብዮቱ የሚጠብቀውን ለውጥ ማምጣት አለመቻሉ ያሳዝነው ነበር።ይባስ ብሎ በተለያየ ጎራ መገኘት ሃሳብን አፋጭቶ ለሃገር የሚበጅ መሰረት ለማደርጀት ሳይሆን ለመገዳደል ምክንያት መሆኑን ማየቱ ምቾት ነስቶታል።ለዚህ ነው ደበበ የአብዮት ደጋፊነቱን ወደ ኋላ ብሎ በኢሕአፓ ደጋፊነታቸው ለግድያ ይፈለጉ የነበሩ ሰዎችን መኝታ ቤቱ ኮርኒስ ውስጥ በመደበቅ እንዲሁም በየለቅሶ ቤቱና በተለያዩ ቦታዎች በደርግ ከሚታደኑ ሰዎች ጋር በመዞር ራሱን ለአደጋ አጋልጦ ሌሎችን ለማዳን የተነሳው፤ ይህንንም ምስክርነት ከብዙ ሰዎች መስማቱን መ/ር ገዛኸኝ ያስታውሳል።

## የብርሃን አሳሹ ፍፃሜ

ደበበ ... ያ የብርሃን አፍቃሪ፣ ለሰው ችግር ባዛኝ፣ የራሱን ምቾት ናቂ፣ የጥበብ ባላባት፣ የኪነት አራቂ፣ በቅኔ ተራቃቂ ... ዕድሜ ልኩን ሃገሬን እንዳለ፣ ለሃገር እንደተቀኘ፣ ለሃገር እንደዘመረ ... ሃገር ግና ለርሱ አንዳች ሳታደርግለት እንዲሁ ባክኖ ከስጋ ኑረቱ ታቀበ።በሌሎች መጉደል ሲያነባ ኖሮ ዳግም በእኛ ላይ ጎደለ... ለግማሽ ምዕተ ዓመት ከራስ ዓለም ሽክርክሪት ውጪ ስለሌሎች ስትጦዝ የነበረች ነፍሱ የምድር ዓለም ኪራይዋ አብቅቶ ተሰናበተች።ደበበ ለ 8 ዓመታት ያህል በጠና ከታመመ በኋላ ሚያዝያ 16 ቀን 1992 ዓ.ም. በ 50 ዓመቱ ዐረፈ።የቀብር ስነስርዓቱ የተፈጸመው በአዲስ አበባ ቅ/ዮሴፍ ቤተክርስቲያን ሲሆን የመቃብር ሐውልቱ ላይ በ 1968 ዓ.ም. የከተባት ዘላለማዊ ግጥሙ ሰፍራለች:-

**ለምን ሞተ ቢሉ**

**ንገሩ ለሁሉ**

**ሳትደብቁ ከቶ፣**

**ከዘመን ተኳርፎ**

**ከዘመን ተጣልቶ።;**

ገጣሚው ብቸኝነትና ባይተዋርነት ይሰማው እንደነበር ከዓመታት በፊት የገለጸባት ይህች ግጥም ወደኋላ ላይ በመረረ መከፋትና ኩርፊያ ወደ መቃብር መውረዱን የመተንበይዋ ነገር ምንም እንኳ የደራሲው ነገን በብዕሩ ጫፍ የማየት አቅም አጉልታ በማሳየት ብታስደምመንም የዕድሜ ልክ ቁጭት ፈጥራ እህህ ማሰኘቷም አይቀርም።

ዛሬ ደበበ በጥቂት የስነጽሑፍ ቤተኞች ዘንድ ካልሆነ ብዙም የማይነሳ፣ በትውልድ ቀዬው ሳይቀር ጀግንነቱ የማይነገርለት ሆኗል።የዚህ ጽሑፍ አጠናቃሪ በአንድ ወቅት በይርጋለም ከተማ ተገኝቶ ከልጅ እስከ አዋቂ ደበበ ሰይፉን ታውቀዋለህ/ቂዋለሽ?; እያለ ሲጠይቅና ከተማዋን ዳር እስከ ዳር ሲያካልል ቢውልም በመገረም የሚያፈጡበትን እንጂ አውቀዋለሁ የሚሉትን ሳይታደል ቀርቶ አዝኖ መመለሱን ያስታውሳል፤ ነቢይ በሃገሩ...; መሆኑ ነው።

እነሆ ከባለታሪካችን የሕይወት ሰፌድ ላይ ጥቂቷን ብቻ ቆነጠርን፤ በመግቢያዬ እንደገለጽኩት ለዚህ የደበበ የሕይወት ሸራፊ አስተዋጽዎ ያደረጉ በርካታ የሕትመት ውጤቶች አሉ:- ከነዚህም ውስጥ 'ደማቆቹ-ፀሐያተ ሌሊት መጽሐፍ'፣ 'አዲስ ነገር ጋዜጣ'፣ 'አዲስ አድማስ ጋዜጣ' (5 ተከታታይ እትም)፣ 'ጠብታ መጽሔት'፣ 'የካቲት መጽሔት'፣ የደበበ ሁለት የግጥም መድብሎች እንዲሁም መ/ር ገዛኸኝ ጌታቸው (አዋሳ '60 ሻማ የኪነጥበብ ማሕበር' ባዘጋጀው ዝክረ ደበበ ሰይፉ መርሐ-ግብር ላይ የሰጠው ገለፃ) በዋቢነታቸው እራትና መብራት ይስጥልኝ ልላቸው እጅ ነስቻለሁ። ♦

መልዕክተ ኢትዮጵያ

# ለምን ጦር ሰባቂ ይበዛል?

## የኢትዮጵያዊነት ፈተና



ስነ ጥበብ እንደ ስሙዋ መልኩዋና አገልግሎቱዋ ብዙ ነዉ። አምባገነኖች ለራሳቸዉ ፍላጎት ይጠመዝዙዋታል። እንዲያዉም የሶሻሊስት ርዕዮተ አለም የሚያራምዱ ጥበበኞች እንደሚነግሩን ከሆነ ሶሻሊስታዊ ስነ ጥበብ አለች። ይህች ስነ ጥበብ ታዲያ ዋና ግቡዋ ሶሻሊዝምን ማራመድ እና ወደ ህዝቡ አዕምሮ ዉስጥ ሶሻሊዝምን ከመክተትም በዘለለ የህዝቡ ስነ ባህሪ በሶሻሊስታዊ መርህ እንዲታነጽ ማድረግ ነዉ። ብልህ ምዕራባዉያን መንግስታት የሀገራቸዉን እሴት በመላዉ አለም ለማሰራጨት ብሎም የሀገራቸዉን ሀያልነት ለመስበክ ይገለገሉባታል። የሆሊዉድን የፊልም ስራዎች ማስተዋል በቂ ነዉ። የሆሊዉድ ፊልሞች ምዕራባዉያን ሲያሸንፉ ብሎም የእነሱ ባህላዊ እሴት ፍጹም የበላይ መሆኑን ለመላዉ አለም እንደሰበኩ ይኖራሉ።

አንዳንድ ባለ አዕምሮ የስነጥበበ ባለሞያዎች ደግሞ ስነጥበብን የሰዉ ልጆችን እኩልነት ለማራመድ እንደ ቁልፍ መሳሪያነት ይጠቀሙባታል። አንዳንድ የዋሆች እንደሚመስላቸዉ የስነ ጥበበ ሞያተኞች ከወገናዊነት የነጹና አቁዋም አልቦ ይመስሉዋቸዋል። ስነ ጥበበኞች ግን በዚህኛዉም ሆነ በዚያኛዉ ወገን ወይም በራሳቸዉ ማዕከላዊ ዛቢያ ላይ ቢሽከረከሩም ከወገናዊነት እና አንድን ጭብጥ ከማራመድ ነጻና ገለልተኛ መሆን አይችሉም።

በአሁኑ ዘመን ያሉ ኢትዮጵያዊ የስነ ጥበበ ባለሞያዎችን በሶስት ጎራ ከፍለን ልናያቸዉ እንችላለን። አንደኛ ደረጃ ላይ የሚገኙትና በርከት ያሉት ያለዉን ስርአት ለማገልገል ብቻ የሚኖሩ ናቸዉ። ሌላም ስርዓት ቢመጣም መልሰዉ ስርዓቱ እንደሚፈልገዉ የሚያገለግሉ ናቸዉ። ምንም አይነት የተለዩ ስርዓት ቢመጣ ትናንት ጥቁር ያሉትን ዛሬ ነጭ ብለዉ ለማቅረብ አይቸገሩም። እነሱ አቁዋም የምትባል ነገር የላቸዉም። በአንድ ወቅት ስለ አንድ ዘፋኝ አንድ የሀገራችን ፖለቲከኛ ሲጠየቅ የጨመሩባቸዉን ነገር እንደ ማንቆርቆሪያ ማንቆርቆር ብቻ ነዉ ስራቸዉ እንዳለዉ።

ሁለተኞቹ ቡድኖች ደግሞ ከኢትዮጵያዊነት ይልቅ የጎሳ ብሄረተኝነተ እሴትን ማዕከላቸዉ ያደረጉ ናቸዉ። ፈጹም የራሳቸዉ አቁዋም አላቸዉ። ኢትዮጵያ የጋራ እሴት አላት ብለዉ አያስቡም/አያምኑም። ኢትዮጵያ ሀገር ናት ብለዉም አያምኑም። በርቀት ህልማቸዉ ኢትዮጵያ ብትፈርስ ደስተኛ ናቸዉ። ሶስተኞቹ ቡድኖች ደግሞ ኢትዮጵያዊነት እሴትን የስነ ጥበብ ስራቸዉ ማዕከል ያደረጉ ናቸዉ። በእነዚህ ቡድኖች ህሳቤ ደግሞ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር የጋራ ማንነት ያላት ከሰዉ ዘር መነሻ እስከ አሁን የቀጠለች ሳባዊት ኩሻዊት ካማዊት እሴት የተዋሃደባት ብሎም ክርስትና እስልምና አይሁድነት አብሮ ተለዉሶ የወጣባት ኢትዮጵያ አለች። እነዚህ የስነጥበብ ሀይሎች ሀይለኛ ናቸዉ። ለያዙት አላማም የማያወላዳ ፍልስፍና አላቸዉ። ሀገሪቱ መከራ ዉስጥ በወደቀችበት ጊዜና ህዝቡ በሚደናገርበት ሰዓት ስለ ኢትዮጵያዊነት በማቀንቀን የህዝቡን ህብረት ሲሰብኩ ተስተውለዋል። እንዲህም ይላሉ። "ቢለያይም ቁዋንቁዋ አንድ ነዉ ደማችን .." ብለዉ ስለ ኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት ሳያፍሩና ሳይሸማቀቁ ያቀነቅናሉ። ስለ ሌሎቹ ሌላ ጊዜ እመለስበት ይሆናል።

ለዛሬ ግን ቴዲ አፍሮ ላይ ማተኮር ፈልጌአለሁ። ምክንያቴ ደግሞ ቴዲ አፍሮ የሰሞኑ የጭብጨባ ወጀብ ብቻ ሳይሆን የዱላም መዓትም እያረፈበት ያለ የጥበብ ሰዉ በመሆኑ ነዉ። ቴዲ አለም ዋንጫ ላይ ኢትዮጵያን ወክሎ ሊሳተፍ ሲልም ሆነ አሁን ከኮካ ኮላ ጋር ተጣላ ሲባል እየተነሳ ያለዉ አቡዋራ ምክንያቱ አንድና አንድ ነዉ። ቴዎድሮስ ካሳሁን ኢትዮጵያዊነት የጋራ እሴትን ማዕከሉ አድርጎ መዝፈኑ ነዉ። በቴዎድሮስ ካሳሁን የማይናወጥ እምነት ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር የጋራ ማንነት ያላት ከሰዉ ዘር መነሻ እስከ አሁን የቀጠለች

ሳባዊት ኩሻዊት ካማዊት እሴት የተዋሃደባት ብሎም ክርስትና እስልምና አይሁድነት አብሮ ተለዉሶ የወጣባት ሀገር ነች። በዘፎኖቹ የሚሰብከን ይሄን ነዉ። ጥያቄዉ ግን ቴዲ አፍሮ እንዲህ ስለ ህዝብ ዉህድነት ሲሰብክ ለምን ጦር ሰባቂዎች በዙበት የሚለዉ ነዉ?

ቴዲ አፍሮ የጠለቀ ጭብጥ በቁዋጠሩ ሙዚቃዎቹ እንደሚነግረን ኢትዮጵያዊነት የጋራ እሴት አለዉ። ይህ የጋራ ኢትዮጵያዊ እሴት አይሁዱን: እስላም ክርስቲያኑን ያፋቅራል።ይህ የጋራ ኢትዮጵያዊ እሴት ጥንታዊና ስር የሰደደ የጋራ ምድር ያለዉ የጋራ ታሪካዊ መሰረት ያለዉ ዉህድ ኢትዮጵያዊ ህዝብን አስተሳስሮ አቁሞአል። ኢትዮጵያዊነት ለቴዲ አፍሮ የጎሳዎች ድምር ሳይሆን የኢትዮጵያዉያን ማህበረሰብ ዉህደት ነዉ።ይህ ዉህደት ደግሞ ከድምር የበለጠ የጋራ መስተጋብር ነዉ (the whole is greater than the sum)። ይህ ማለት ለቴዲ አፍሮ የሀሳብ ማጠንጠኛዉ ብሎም መድረሻ ራዕይዉ ዉህድ የሆነዉ ኢትዮጵያዊ እሴት ነዉ።

ቴዲ ከሙዚቃ በላይ በገዘፈዉ ጭብጡ የሚያስተላልፈዉ የጋራ ኢትዮጵያዊ እሴት መልዕክቱ አንድ ነዉ። ይሄዉም ህያዉ የሆነ ቆሞ የሚሄድ እና የሚራመድ በሁሉም ኢትዮጵያዊ ማህበረሰብ የተገነባና በዉህደት የተሰራ ኢትዮጵያዊነት ነዉ። ለዚህ ማሳያዉ የአድዋ ድልን የገለጸበት የተራቀቀ ዘይቤ ነዉ። ቴዲ አፍሮ እንደሚተርክልን ያ ድል የዚህ ወይም የዚያ ብሄረሰብ/ማህበረሰብ ድል ሳይሆን የሁሉም ዉህድ ማህበረሰብ ድል ነዉ። ኢትዮጵያዊ ማህበረሰቦቹን በጀግኖቻቸዉ ወክሎ ዉህድ ሂደቱን ግን ከድምር በዘለለ ያቀርበዋል። ይህን የገለጸዉ በዉህዱ ኢትዮጵያዊነት ዘይቤ ነዉ።

በዚህ የአድዋ ዉህድ ድልም የኢትዮጵያዊነት የጋራ ማንነት ተጠብቆአል። ከዚህም ዘሎ ቴዲ እንደሚተርክልን የመላዉ የጥቁር ዘር ቀና ብሎ በማንነቱ እንዳያፍር ዉህዱ ኢትዮጵያዊ ህዝብ ታሪክ ሰርቶአል። የአሜሪካዉ የታሪክ ተመራማሪ ፕሮፌሰር እንዳሉትም የአድዋ ድል የለወጠዉ የመላዉን የአዳምን ዘር የታሪክ ፍሰት ነዉ። በፕሮፌሰሩ ታሪካዊ ትንታኔ መሰረትም የአድዋ ድል የመላዉ የጥቁር ዘር አዲስ የማንነት ዉልደት ምዕራፍ ነዉ። ቴዎድሮስ ካሳሁን ከፕሮፌሰሩ ጋር የመከረ ይመስል የፕሮፌሰሩን ሀሳብ አንድ በአንድ በሙዚቃ ሰንቆ አቅርቦታል። የሚገርመዉ የቴዎድሮስ ካሳሁን ግጥም የተጻፈዉ ፕሮፌሰሩ መጽሃፋቸዉን ከማሳተማቸዉ በፊት ነበር። ፕሮፌሰሩም ቢሆኑ መጽሃፋቸዉን ያሳተሙት የቴዲን ዘፈን ሰምተዉ አይደለም። የራሳቸዉን ምርምር አድርገዉ እንጅ።

ቴዲ አፍሮ ስለጥንታዊ ሳባ: ስለ ባህረነጋሽ: ስለ ታላላቅ የህዝብ ዉህደት ሂደቶች እንዲሁም ሁለቱ የሀገሪቱ ታላላቅ እምነቶች እንዴት ተቻችለዉ በጋራ እንደ ኖሩ ለማሳዬት ይባትታል። ቴዎድሮስ ካሳሁን ልዩ ልዩ የሀገሪቱን ቁዋንቁዋዎች በአንድ አቀናብሮ ለማሳዬት በተቻለዉ ይሞክራል። ኢትዮጵያዊነት እሴት ልባቸዉን ቀስፎ የያዛቸዉ ወገኖች ያጨበጭባሉ። አክራሪ የጎሳ ብሄረተኞች ጥርሳቸዉን ይነክሳሉ። ጥርሳቸዉን ነክሰዉም አይቀሩም ጦር በዚህ ሰዉ ላይ ይወረዉራሉ። አድዋ ባርነትን እንጅ ምን አተረፈልን ሲሉ በነጭ ቅኝ ባለመገዛታቸዉ እየተቆጩ ይጽፋሉ። ያባቶቻቸዉን ታሪክ በሙሉ በእግራቸዉ ረግጠዉ ከኢትዮጵያዊ የጋራ ማንነት ይልቅ በኢትዮጵያዉያን መሃከል ልዩነትና ጥላቻ ከፍ ብሎ ይዉለበለብ ዘንድ አበክረዉ ይሰራሉ።

ቴዎድሮስ ካሳሁን የተሸከመዉ እሜት ኢትዮጵያዊነት የጋራ እሴት አለዉ ብሎ ለሚያምነዉ ኢትዮጵያዊ ወገን የኩራት ምንጭ ሲሆን ኢትዮጵያዊነት የጋራ እሴት የለዉም: ኢትዮጵያዊነት አቀንቃኞች መደምሰስና መጠረግ አለባቸዉ ብለዉ በአቁዋም ለጸኑ አክራሪ የጎሳ ብሄረተኞች ግን የብስጭት ምንጫቸዉ ነዉ። ለዚህ በቂ ምክንያት አላቸዉ።

አክራሪ የጎሳ ብሄረተኞች ዋናዉና የመጨረሻ ግባቸዉ አንድ ብቻ ነዉ። እሱዉም ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር ተረት ተረት ናት ስለሆነም መገነጣጠል አለባት የሚል የማያወላዉል እና የማያወላዳ አቁዋም አላቸዉ። ሆኖም ይሄን የመጨረሻዉን ግባቸዉን ወደ መድረክ ከማቅረባቸዉ በፊት ሊሰሩዋቸዉ የሚገቡ የደረጃ በደረጃ የቤት ስራዎች አሉዋቸዉ። እነዚህን የደረጃ በደረጃ የቤት ስራዎች ልዩ ልዩ ኢትዮጵያዊ ማህበረሰቦች/ብሄረሰቦች በደንብ እንዳይረዱዋቸዉ ማደናገሪያ ዘዴዎች አብጅተዉላቸዋል። ህዝቡ የሚያስተዉላቸዉ በብዥታና በድንግርግርም እንዲሆን ህዝቡን በልዩ ልዩ መልክ ያደናግሩታል። ከማደናገሪያቸዉ ዋና ዋና ነጥቦችም:-

**...ኢትዮጵያ ስትዋረድ ደስ ይላቸዋል:: ኢትዮጵያዊ ሰዉ የላትም ሲባል ዳንኪራ ይረግጣሉ:: ኢትዮጵያ ታሪክ የሌላት ምናምንቴ ሀገር ናት የሚል ሀሳብ ሲሰሙ ደስታቸዉ ጣሪያ ይነካል:: ኢትዮጵያ የሚል ቃል ሲሰሙ ያማቸዋል ብቻ ሳይሆን የጥላቻ ዛር ያንዘፈዝፋቸዋል...**

-ኢትዮጵያ የሚባል ወጥ ህዝብ የለም:: ኢትዮጵያ እያለ የሚጮህዉ ይሄኛዉ ወይም ያኛዉ ማህበረሰብ ብቻ ነዉ:: ሆኖም ኢትዮጵያ እያሉ መጮህ ትምክህት እና ጊዜዉ ያለፈበት የሞኞችና የሁዋላ ቀሮች ባህል ነዉ:: ኢትዮጵያ የሚባለዉ ሀገር በመቶ አመት ዉስጥ የተፈጠረ ተረት ተረት አገር ነዉ::ጥንታዊ ታሪክ አለዉ እሚባለዉ የፈጠራ ድርሰት ነዉ:: አሁን የምናያት ኢትዮጵያ በምኒልክ በቅኝ ግዛት የተፈጠረች ሃገር ነች::

-ይሄኛዉ መሬት የእኛ መሬት ብቻ ነበር:: እነ እከሌ መጥተዉ ወረሩን:: ስለዚህ እነዚህን ከዚህ መሬት ላይ ጨፍጭፈን እናባራቸዉ::

-ይሄኛዉ ህዝብ መጤ ህዝብ ነዉ:: ነዋሪና ባለቤቶች እኛ ነን:: በመሆኑም በሀገሩ ላይ ያለዉ ሀብት ሁሉ ለእኛ ይገባል:: አሁን እዚህ ከተማ ዉስጥ ፎቅ ሰርተዉ እና ሱቅ ከፍተዉ ልዩ ልዩ ንግዶችን አከናዉነዉ ሀብት ያፈሩ ማህበረሰቦች በሙሉ ሃብታቸዉን ያፈሩት በዘረፋ ነዉ:: ስለሆነም እዚህ ከተማ የሚነግደዉ ማህበረሰብ የኛ ወገን ስላልሆነ የሰራዉ ሱቅ : የሰራዉ ፎቅ እና ያፈራዉን ሀብት ሁሉ ተወላጁ እጣ ተጣጥሎ ሊወርሰዉ ይገባል::

- እኛ እንዲህ ተበድለናል እነዚያ ደግሞ እንዲህ ተበድለዋል:: ስለሆነም ሀገሩን በጋራ እናፍርሰዉ::

- ሀገሩ ሲመራና ሲተዳድር የነበረዉ በአንድ ማህበረሰብ ሆኖ የኢትዮጵያ ታሪክም ምንም የጋራ እሴት የለዉም:: ህዝቡም አልተዋሃደም:: ለምሳሌ ንጉሰ ነገስት አጼ ኃይለስላሴ እንዲሁም ንግስት ኢሌኒ የብዙ ኢትዮጵያዊ ዉህድ ዉጤት ናቸዉ የሚባለዉ ሀሰትና ተረት ተረት ነዉ::

- ከዚህኛዉ ማህበረሰብ ጋር አትጋቡ:: ከዚህኛዉ ማህበረሰብ ጋር ከተጋባችሁ ግን የማህበረሰባችሁ ጠላት ናችሁ::

-ስለ ኢትዮጵያ አንድነትና ታሪክ የሚያቀነቅኑ ኢትዮጵያኒስቶችን ማሸማቀቅ አለብን

በነዚህ ሁሉ ማደናገሪያዎች ግን ጥላቻን ስለመርጨታቸዉ እርግጠኛ መሆን ይፈልጋሉ:: ኢትዮጵያዉያን ሆድ እንዲባባሱ ማድረጋቸዉን ማረጋገጥ ዋናዉ ስራቸዉ ነዉ:: እናም አክራሪ የጎሳ ብሄረተኞች ቅደመ መገንጠል ስራቸዉን በድንብ ሳያርፉና ሳይታክቱ እየሰሩ ነዉ:: አልደከሙም አልታከቱም:: የትም ቢሆኑ አቋማቸዉ አንድ ነዉ:: አይወላዉሉም:: በኢትዮጵያ ምደር ቢመቻቸዉም ባይመቻቸዉም: የመጨረሻዉ ጣሪያ ላይ ቢደርሱም: ከስር ቢሆኑም: በዉጭ ሀገር ቢኖሩም ይህችን የመገንጠል ህልማቸዉን አይተዋትም:: በስነልቦናቸዉ እራሱ ከብዙሃኑ ኢትዮጵያዊ ግንጥል ናቸዉ:: እናም ጠንክረዉ ይሰራሉ:: ስራቸዉ የደረጃ በደረጃ የቤት ስራ እንዳለበት ጠንቀቀዉ የተረዱት ከረዥም ጊዜ የትግል ልምድ ብሁዋላ ነዉ::

ለምሳሌም በቋንቋዋ : በታሪክ : በባህል: በእምነት በመልክዓምድር በስነልቦና ከብዙሃኑ ኢትዮጵያዊ ጋር አንድ የነበረዉ የኤርትራ ህዝብ በአክራሪ የጎሳ ብሄረተኞች የሀሰት ፕሮፖጋንዳና ነገን ባላገናዘብ መልክ እንዴት የተለዩ ህዝብ ተብሎ እንደሄድ በደንብ አጥንተዋል:: ምንም እንኩዋን ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል እንጅ ኢትዮጵያ ቅኝ ያልገዛቻት ሀገር መሆኑዋን ልባቸዉ ቢያዉቅም ኤርትራ በኢትዮጵያ ቅኝ የተገዛች አገር የሚለዉ የሀሰት ፕሮፖጋንዳ በደንብ እንደሰራ አስተዉለዋል:: ሆኖም ይሄን ፕሮፖጋንዳ በደንብ መሬት ለማዉረድ እረዥም አመታት አስፈላጊ እንደነበረና የኤርትራን ህዝብ ኢትዮጵያዊ አይደለም ብሎ ለማሳመን ጊዜ ፈጅቶ እንደነበረ በደንብ አስተዉለዋል:: ለዚህም የስነጥበብ ድርሻ ከፍ ያለ እንደነበር ተሞክሮን ከኤርትራ ወስደዋል::

እናም አሁን ኢትዮጵያ በዝግታ ትፈርስ ዘንድ ትግል የያዙ የጎሳ አክራሪ ሀይሎች ሞኝ አይደሉም:: በጣም ብልህና ከፍተኛ ልምድ ያካበቱ ሀይሎች ናቸዉ:: ደግሞም ልምድ የሚያካፍላቸዉ አለ:: የትግል ልምዳቸዉ በደንብ እንደነገራቸዉ እና እንዳስረዳቸዉ ኢትዮጵያዊነት እጅግ ዉህድነት ስለሆነ በቀላሉ ብትንትኑን ማዉጣት እንደማይችሉ ተረድተዋል:: አክራሪ የጎሳ ብሄረተኞች

በልባቸዉ የማይክዱት ሀቅ አለ:: ይሄዉም ኢትዮጵያዊነት ዉህድነት መሆኑን:: ፕሮፌሰር መስፍን እንዳሉት ኢትዮጵያዊነት አይሁድነትን ; ክርስትናን እና ሙስሊምነትን ጠምዝዞ ዉህድ ኢትዮጵያዊ እሴትን የማልበስ አቅምና ጉልበት ያለዉ ታላቅ ሚስጥረ መሆኑን አክራሪዎቹ የጎሳ ብሄረተኞች ተረድተዋል:: እንዴዉም በድንብ አድርገዉ አጥንተዉታል::

ደግሞም አሁን ሌላ የተረዱት ነጭ እዉነት አለ:: ይሄዉም ኢትዮጵያዊነት ስሜት እና ለጋራ ኢትዮጵያዊ እሴት ተቆርቁሮ የመቆም ጉልበት ከህዝባችን ዉስጥ ሲሙዋሽሽ አስተዉለዋል:: በድንብ ተረድተዋል:: በዚህም ልባቸዉ ተነፍቱዋል:: በከፍተኛ የድል ተራራ ላይ የወጣ ስሜትን ለብሰዋል:: እናም ከንግዲህ አንዳንድ የቀሩ እንጥፍጣፊ ኢትዮጵያዊነት ስሜት የሚያዉለበልቡ የሚያርገበግቡ ግለሰቦች ከመጡ እንዳያንሰራሩ አድርጎ መሰባበር ወሳኝ መሆኑን አስምረዉበታል::

የኢትዮጵያዊ ብሄረተኝነት እሴትን ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመደምሰስ የሚደረግ የርብርቦሽ ስራ ብቻ እንደቀራቸዉም መክረዋል:: እናም ቴዲ አፍሮ ብቻዉን በመድረኩ ላይ የኢትዮጵያዊነት የብሄረተኝነት እሴትን: የዚህችን ጥንታዊትና ባለታሪክ ሀገር የጋራ እሴትን ከፍ አድርጎ ሲዘምር አስተዋሉ:: ወደ መጨረሻዉ ግብ ተራመድን ሲሉ እንኩዋን ለኢትዮጵያ ለጥቁር ዘር በመላ መኩሪያ ይሆን ዘንድ ታሪክ የሰሩትን ታላቁን ዳግማዊ አጼ ሚኒልክን በጋራ የሀገር እሴትነት ወክሎ ብቅ አለ:: ስንት ቢሊዮን ብርና ሰዓት አፍሰዉ ቀብርነዉ ያሉትን ታሪክ እፍ ብሎ ብድግ አድርጎ ወደ ህዝብ ሲያቀርበዉ የኢትዮጵያ ህዝብ አስደንጋጭ በሆነ ደስታ ተቀበለዉ:: ያኔም አክራሪ የጎሳ ብሄረተኞች ተበሳጩ:: ስለ ጥንታዊት ሳባ ሲያቀነቅን ተረት ተረት ታሪክ ያወድሳል ሲሉ ጣት ቀሰሩበት:: ስለ ሙስሊምና ክርስቲያን ፍቅርና ህብረት ሲያቀነቅን ምን ህብረት አላቸዉ ሲሉ መግለጫ አወጡበት:: አንዳንዶች ለክርስትና የተቆረቆሩ መስለዉ ሌሎች ለእስልምና የተቆረቆሩ መስለዉ መግለጫ አወጡበት:: ሆኖም ግባቸዉ አንድ ነበር:; ዉህድ ኢትዮጵያዊነት እንዳይሰበክ እና የጋራ ኢትዮጵያዊ እሴት እንዳይሰበክ ነበር:: ቴዲ አፍሮን የጠሉት እነሱ የሚያቀነቅኑትን የጎሳ እሴት ከመሸከም ይልቅ የኢትዮጵያዊነት እሴት ስለተሸከመ ብቻ ነዉ::ቴዲ ኢትዮጵያዊነት ሞቴ ነዉ ብሎአል::ኢትዮጵያዊነት ትምክህቴ ነዉ ብሎአል:: አክራሪ የጎሳ ብሄረተኞች ደግሞ ሞት ለኢትዮጵያዊነት የጋራ እሴት ብለዋል::

ቴዎድሮስ ካሳሁን አሁንም በኢትዮጵያዊነት የጋራ እሴት ዙሪያ መዞሩን ቀጠለ:: ስለ ፍቅር ይዘምራል ስለ ታላላቅ ኢትዮጵያዊ አባቶቻችን ይሰብካል ስለ ጥንታዊት ኢትዮጵያ ያቀነቅናል:: አክራሪ የጎሳ ብሄረተኞች ተረት ተረት ስለሚሉት ኢትዮጵያዊ የጋራ እሴት ሁሉ በማንሳት ኢትዮጵያዊነት የሚያማልለዉን ኢትዮጵያዊ ህዝብ በሀሴት ዳንኪራ ያስረግጣል:: እናም አክራሪ የጎሳ ብሄረተኞች ተበሳጩ:: አሉም ከእንግዲህ ብዙም ኢትዮጵያዊነት ብሄረተኝነትን የሚያቀነቅኑ ሰዎች ስለሌሉ እየነጠልን ቴዲን ማጥቃት ተገቢ ነዉ ሲሉ በትር አነሱ:: እናም ቴዎድሮስ ካሳሁን አሁን የጥቃት ኢላማቸዉ ሆኑዋል:: የማህበረሰብ ድረገጾችን እንዲሁም ማንኛዉንም ሚዲያ በመጠቀም በቴዲ ላይ የስድብ ናዳ ይዘንባል::

ደግሞም ሰሞኑን ከብራዚል የአለም ዋንጫ ተሳታፊነቱ መስተጉዋጎሉ ተአምራዊ ዳንኪራን ፈፕሮላቸዋል:: አንዴ በዘረኝነት ይከሱታል ሌላ ጊዜ በችሎታ ማነስ:: አስከትለዉ ደግሞ በምኒሊካዊነት:: ሲብስባቸዉም የኢትዮጵያን የሀሰት ተረት ተረት ሰባኪምነት ይከሱታል:: ለአክራሪ የጎሳ ብሄረተኞች ኢትዮጵያ ተረት ተረት ነች:: ታሪኩዋ ሁሉ ሀሰት ነዉ:: ንግስት ሳባ ተረት ተረት ነች:: በመጽሃፍ ቅዱስ ያለችዉ ኢትዮጵያ ሀሰት ነች:: ነብዩ መሐመድ በታላቅ ባለዉለታነት የተናገሩላት ኢትዮጵያ ሀሰት ነች:: አባቶቻችን አብርሃና አጽብሃ አንዱ አክሱም ላይ አንዱም ሸዋ ላይ ሆነዉ ዛሬ ባሌ እና ሶማሊያ የሚባለዉን አካባቢ እንዲሁም ከምዕራብና ከደቡብ ያሉ ሰፊ ኢትዮጵያዊ አካባቢዎችን አንድ አድርገዉ ሲያስተዳድሩ የነበሩት ታሪክ ሀሰትና ተረት ተረት ነዉ:: ለአክራሪ የጎሳ ብሄረተኞች አሁን ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚለዉ ህዝብ እራሱ እንኩዋን ሀሰት ነዉ:: ለአክራሪ የጎሳ ብሄረተኞች በ19ኛዉ ምዕተ ዓለም አሃመነስ የሚባል ኢትዮጵያዊ ፈላስፋ 16 ፕላኔቶች ስለመኖራቸዉ የጻፈዉ ፍልስፍና ተረት ተረት ነዉ:: ለአክራሪ የጎሳ ብሄረተኞች

ኢትዮጵያዉያን የሚያደርጉት ነገር ሁሉ ተረት ተረት ነዉ:: ከዚህም በላይ አጥብቀዉ የሚጠሉት ነገር ታዲያ ኢትዮጵያዊነት የጋራ ማንነት አለዉ የሚለዉን ጭብጥ አንስቶ የሚያርገበግብን ሀይልን ነዉ::

አንዳንድ የዋህ ኢትዮጵያዉያን እንደሚያስቡት አክራሪ የጎሳ ብሄረተኞች እያጠቁት ያለዉ ቴዎድሮስ ካሳሁንን በግለሰብ ደረጃ ይመስላቸዋል:: ላንዳንዶች የመሰላቸዉ አክራሪ የጎሳ ብሄረተኞች የጠሉት ቴዲ አፍሮን ነዉ:: ሚስጥሩ ግን እነዚህ ሰዎች የጠሉት አንድ ነገር ብቻ ነዉ:: ኢትዮጵያዊ የጋራ እሴት የሚባል ነገር ፈጽሞ እንዲኖር አይፈልጉም:: የኢትዮጵያ ታሪክ የዉሸትና የጭካኔ ታሪክ ነዉ ሲሉ ክደዋል:: ኢትዮጵያዊ ማንነቱን እንዲጠላ እየሰሩ ነዉ:: የኢትዮጵያ ህዝብ ለስንት ሽሕ ዘመናት አብሮ ኖሮም በፍጹም ያልተዋሃደ ህዝብ ብሎም እንደ ዘይትና ዉሃ ፈጽሞ ያልተቀላቀል ህዝብ ነዉ ሲሉ ኢትዮጵያዉያንን በጎሳ ከረጢት ዉስጥ ብቻ ልኬታቸዉን ሰፍተዉላቸዋል:: ቴዎድሮስ ካሳሁን ደግሞ እዚህ እጎሳ ከረጢታቸዉ ዉስጥ አልገባ ብሎዋቸዋል::ሰዉዬዉ ከጎሳ ከረጢት የገዘፈ ሰብዕና አለዉ:: ዛሬ ዉጭ አገር ድረስ ሄደዉ ፒ ኤችዲና ማስተር አንጠልጥለዉ ሲያበቁ ስለጎሳና ቀበሌያቸዉ ሲዘምሩ ዉለዉ ሲያለቅሱ ቢያድሩ የማይታክቱ ምሁራን እንደ አሸን በፈሉባት ኢትዮጵያ ዉስጥ አንድ ሙዚቀኛ ግን ከጎሳ ከረጢቱ በላይ የገዘፈ ሰብዕና ለብሶ ብቅ አለባቸዉ:: እናም ተረበሹ::

አክራሪ የጎሳ ብሄረተኞች ሙሴን የስራ አመራር ስርአታ ያስተማረዉን የኢትዮጵያዉያን አባትን የዮቶርን ታሪክ ክደዋል:: የመጽሀፍ ቅዱሱን ታሪክ ማራከስ ሲያቅታቸዉ የጎጃም ቄሶች በግዕዝ የጻፉት ተረት ተረት ነዉ ሲሉ ዉሸትን ከረባታቸዉ አድርገዋል:: የእንግሊዘኛዉ መጽሃፍ ቅዱስ ሲመጣላቸዉ ደሞ ይህ መጽሃፍ ቅዱስ የሚጠቅሳት ይህችኛዋ ኢትዮጵያ አይደለችም ሲሉ በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ ያላቸዉን እጅግ ጥልቅና ስር የሰደደ ጥላቻ ነግረዉናል:: የኢትዮጵያዉና ነገስታት ታሪክ የሀሰት ታሪክ ሀሰት ነዉ:: ክብረ ነገስት የሚባለዉም የነገስታት ታሪክ መጽሀፍ በትግሬ ደብተራ የተጻፈ ተራ የሀሰት ሰንድ ነዉ ሲሉ ኢትዮጵያዊ የሆነዉ ነገር በእገር ይረገጥ ዘንድ ከአንዳንድ ተንኮለኛ ፈረንጅ ጸሃፊዎች የቃረሙዋትን ቆራጣ መረጃ ለማቅረብ መጽሃፍትን ጽፈዋል:: እንግዲህ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር ምንም የእዉነት የሆነ እሴት የላትም ማለት ነዉ:: በአክራሪ የጎሳ ፖለቲከኞች አይን::

አክራሪ የጎሳ ብሄረተተኞች ሌላዉ የማሳሳቻ ስልታቸዉ ደግሞ የኢትዮጵያ ታሪክ የነገስታት ታሪክ ስለሆነ ዋጋም የለዉ:: እንደ ኢትዮጵያ ታሪክም ልንቆጥረዉ አይገባም ይሉና ይሄን የኢትዮጵያ ታሪክ ብሎ አንስቶ ማቀንቀን ተገቢ አይደለም ሲሉ በብልጠት ኢትዮጵያዊ ታሪክ ይደብዝዝ ዘንድ ይሰራሉ:: የነገስታትና የሀገር መሪዎች ታሪክ እንጅ ወትሮስ ከሃገር ታሪክ ጋር ተሳስሮ የሚነሳዉ የያንዳንዱ ዜጋ ታሪክ የተጻፈበት ሀገር ወትሮስ የት አለ? እንግሊዝ ነዉ? ሩሲያ ነዉ? ቻይና ነዉ? ነዉ ወይስ የት? ሌላዉ ቀርቶ በአሁኑ ዘመን በዲሞክራሲያዉያን ሀገራት ( ለማጣቀሻ አሜሪካን ማሰብ በቂ ነዉ) ታሪክ የሚጻፈዉ በፕሬዝዳንቱ ዙሪያ የሚሽከረከሩ ሀገራዊ ዉሳኔዎችን እያጣቀሰ እንጅ ፕሬዝዳንቱ ማዕከል ያልሆኑበት ታሪክ የት ይጻፋል? ሀገራዊ ዉሳኔዎች ሁሉ የመጨረሻ የመቁዋጫ ዉሳኔ እና የተፈጻሚነት ትዕዛዝ የሚያገኙት በሀገር መሪዉ እስከሆነ ድረስ የሀገራት ታሪክ ማዕከል ሆነዉ የሚወጡት ፕሬዝዳንቱ ናቸዉ:: ሆኖም አክራሪ የጎሳ ብሄረተኞች ይሄ ጠፍቶአቸዉ አይደለም:: ብቻ አንድ ነገር ይፈልጋሉ:: ያም ነገር በዚህም ሆነ በዚያ ተብሎ ኢትዮጵያዊ የጋራ እሴት ጠፍቶና ተደምሥ ማዬት የመጨረሻ ግባቸዉ ነዉ:: ይሄን የኢትዮጵያዊነት የጋራ እሴት የሚያራግብ ታሪኩን የሚያጣቅስ ሰዉ ከዚህች ሀገር ለመጨረሻ ጊዜ ተደምሥ ማዬት የሚቋዋምጡበት ወቅት አሁን ሆኖ አግኝተዉታል:: ኢትዮጵያዊ የጋራ እሴትን የሚያቀነቅን ግለሰብ እጅግ ትንሽ አቅም ቢኖረዉም የጥላቻ ቀስታቸዉ ማነጣጠሪያ ይሆናል::

አክራሪ የጎሳ ብሄረተኞች የተለያዩ ማህበረሰቦችን/ ብሄረሰቦችን/ በሚወክሉበት ጊዜ እርስ በእርሳቸዉ አይዋደዱም::ሊጠፋፉ ይደባባሉ:: ሆኖም አንድ ነገር ላይ ይስማማሉ:: ይሄዉም ኢትዮጵያዊነት የጋራ እሴትን በማጥቃት ላይ አንድነት አላቸዉ:: እናም በሳሳዉ ኢትዮጵያዊነት ብሄረተኝነት ደን ዉስጥ አንድ ብላቴና ቴዎድሮስ ካሳሁን ወዲህና ወዲያ ሲወራጭ አስተዉለዋል:: ይህ ኢትዮጵያዊ ብላቴና በታላቅ አክብሮት ንግስተ ሳባን ይጠራታል:: አክራሪ የጎሳ ብሄረተኞች ግን ይህ የኢትዮጵያዊነት ታሪክ ዉሸት ነዉ ሲሉ ገና ዱሮ ደምድመዋል:: እናም ይሄን ታሪክ የሚያነሳ ሰዉ ተረት ተረት ታሪክ ያጣቅሳል እያሉ ሞራሉን ለመስበር ኢትዮጵያዊ

ትምክህቱን ለማንኮታኮት መስራት ከጀመሩ ቆይተዋል:: ኢትዮጵያዊነት እና የኢትዮጵያዊነት የጋራ እሴት በማንም ቢነሳ : በምንም መልክ ቢነሳ: በየትኛዉም መልክ ቢነሳ ፊታቸዉ ይደምናል : ልባቸዉ ይጠቁራል እራሳቸዉን ለጸብና ለስድብ ያዘጋጃሉ::

የአክራሪ የጎሳ ብሄረተኞች ጉልበት ገና እየበረታ ይሄዳል:: ጩህትና ስድቡም ገና ምድር ያንቀጠቅጣል:: ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር ተረት ተረት ሀገር ነች የሚለዉ ቃላቸዉም እስከ ደመና ገና ይወጣል:: የኢትዮጵያዊነት የጋራ እሴትን የሚሰብክን ብሎም የኢትዮጵያዊ ብሄረተኝነት እሴትን የሚያቀነቅንን ሁሉ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመደምሰስ የሚደረግ ርብርብ ጉልበቱን ታክቲኩን እና ስልቱን እየቀያዬረ እና እየበረታ እንደሚመጣ ጥርጥር የለዉም:: በጥቂቱ ግን ዛሬ ዱላዉ በቴዲ አፍሮ ላይ እዬወረደ ነዉ:: ቴዲ አፍሮ በብራዚል አለመሳተፉ ያስደሰታቸዉ ይመስል ጥላቻቸዉን በቴዲ አፍሮ ዙሪያ ያጠሩ መስለዉ (በርካታ ተቀባይ እንዲያገኙ) ቀረቡ እንጅ የዳንኪራቸዉ ምንጭ ኢትዮጵያ በአለም መድረክ ላይ እንደ ሀገር ተወክላ አለመቅረቡዋ የፈጠረባቸዉ የደስታ ስሜት ነዉ::ኢትዮጵያ የሚለዉ ስም ያማቸዋልና::

ኢትዮጵያ ስትዋረድ ደስ ይላቸዋል:: ኢትዮጵያዊ ሰዉ የላትም ሲባል ዳንኪራ ይረግጣሉ:: ኢትዮጵያ ታሪክ የሌላት ምናምንቴ ሀገር ናት የሚል ሀሳብ ሲሰሙ ደስታቸዉ ጣሪያ ይነካል:: ኢትዮጵያ የሚል ቃል ሲሰሙ ያማቸዋል ብቻ ሳይሆን የጥላቻ ዛር ያንዘፈዝፋቸዋል:: አክራሪ የጎሳ ብሄረተኞች የረጅም ጊዜ ግባቸዉ ኢትዮጵያዊነትን የሚሸከም ግለሰብ እንዳይወጣ : ኢትዮጵያዊ እሴትም ተንኮታኩቶ እንዲጠፋ ስለሆነ ኢትዮጵያዊነት በአለም መድረክ ላይ እንዲወከል አይፈልጉም:: እናም ኮካ ኮላ ቴዲ አፍሮን ስላገደዉ ደስ ያላቸዉ ኢትዮጵያ ስለተዋረደች ነዉ:: ኢትዮጵያ ስለደበዘዘች ነዉ:: እነሱ የሚፈልጉት የዚህ ዘመን ትዉልድ በሙሉ እንደ እነሱ በየ ጎሳዉ ከረጢት ገብቶ ስለጎሳና ቀበሌዉ ብቻ እንዲዘምር ነዉ:: ከጎሳና ከቀበሌ የዘለለ ኢትዮጵያዊ ሰብዕና ያለዉ ሰዉ ከመጣ ግን በጥላቻ ፕሮፖጋንዳ ይወርዱበታል::

በአሉ ግርማ ደራሲ ብቻ ሳይሆን አንዳንድ እይታዎቹ ትንቢት ጭምር ያዘሉ ይመስሉ ነበር:: ሀዲስ በሚለዉ መጽሃፉ ዉስጥ በንጉሱ ዘመን እንኩዋን አክራሪ የጎሳ ብሄረተኝነት ብልጭ ብልጭ ስትል ጠቆም አድርጎ በርካታ አንባቢ ሊረዳዉ በማይችል መልክ አቅርቦ ሲያበቃ የአደጋዉን ርቀትም እንደ ቀልድ አሳይቶ አልፎ ነበር:: ያኔ በስነጥበብ ስራ ጥቆማ ነገሮችን ቀደሞ አስተዉሎ የሚያቀድና የተሻለ ሁኔታን መፍጠር የሚችሉ አስተዋይ የሀገር መሪዎች ቢኖሩ ኖሩ መድሃኒቱን ማሳብ ይችሉ ነበር::

እናም ዛሬ አክራሪ የጎሳ ብሄረተኞች ጉልበት ከመበርታቱ የተነሳ የኢትዮጵያዊ ብሄረተኝነት እሴት አራማጅ ሀይሎች ምንም የጋራ ነጥብና ታሪካዊ መሰረት እንዳይኖራቸዉ በሀሰት ፕሮፖጋንዳ ቀንድ ቀንዳቸዉን ከማለት ዘሎ ግለሰባዊ ጥቃት



ሸንቁጥ አየለ
(shenkutayele@yahoo.com)

ላይ ደርሶዋል:: እንደተባለዉም ጨህቱና ድንፋታዉ ከደመናት በላይ ደርሶዋል:: ሆኖም በእግዚአብሄር መዝገብ የተጻፈዉ ኢትዮጵያዊነት ነዉና በምድር ላይ ያለ ምንም ሀይል ኢትዮጵያዊነትን ሊያሸንፈዉ አይችልም:: ቴዲና በርካታ ኢትዮጵያዉያን ሀገራችን ቅድስት ነች ብለው ያምናሉ:: ይሄም አክራሪ የጎሳ ብሄረተኞችን ያበሳጫቸዋል:: ኢትዮጵያዊነት ትምክህት ይጎረብጣቸዋል:: ሆኖም መጽሀፉን ገላልጦ ማንበብ ነዉ:: ቅድስናዋን የሰጣት እግዚአብሄር እንጅ ሰዉ አይደለም:: ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያዊነቱን አይለዉጥም እንዳለ መጽሀፉ:: ነብዩ መሐመድም ይሄን ቅድስናዋን ስለተረዱ ፍትህ ወደ ማይዛባባት ቅዱሳን የእዉነት ሰዎች ወዳሉባት ሀገር ሄዳችሁ ታላቁን እምነት እስልምናን ጠብቁ ብለዉ ለተከታዮቻቸዉ ያስረዱት ያለምክንያት አይደለም:: ቴዲ አፍሮ ሀገሪቱ የተሰጣትን እና የሆነችዉን አቀነቀነላት እንጅ ቴዲ አፍሮ የፈጠረላት እሴት የለም:: እናም ይህች ኢትዮጵያዊ ትምክህቱ ስለሆነች ቴዲ አፍሮ እንዲህ ብሎ ዘፈነላት:: እስላም ክርስቲያኑ የሚፋቀርባት ... :: እናም ቴዲ አፍሮ የጥቃት ኢላማ ሆነ:: ለምን ቢባል? ኢትዮጵያዊነት እሴትን አራምዱዋልና:: ኢትዮጵያዊነት ትምክህትን ሰብኮአልናል:: ኢትዮጵያዊነት ዉህደትን አቀንቅኑዋልና::

ቴዲ አፍሮ የጠለቀ ጭብጥ በቁዋጠሩ ሙዚቃዎቹ እንደሚነግረን ኢትዮጵያዊነት የጋራ እሴት አለዉ:: ይህ የጋራ ኢትዮጵያዊ እሴት እስላም ክርስቲያኑን ያፋቅራል::ይህ የጋራ ኢትዮጵያዊ እሴት ጥንታዊና ስር የሰደደ የጋራ ምድር ያለዉ የጋራ ታሪካዊ መሰረት ያለዉ

ዉህድ ኢትዮጵያዊ ህዝብን አስተሳስሮ አቁሞአል:: ኢትዮጵያዊነት ለቴዲ አፍሮ የጎሳዎች ድምር ሳይሆን የኢትዮጵያዉያን ማህበረሰብ ዉህደት ነዉ::

ይህ ዉህደት ደግሞ ከድምር የበለጠ የጋራ መስተጋብር ነዉ (the whole is greater than the sum):: ፕሮፌሰር መስፍን እንዳሉትም ኢትዮጵያዊነት አይሁድነትን : ክርስትናን እና ሙስሊምነትን ጠምዝዞ ዉህድ ኢትዮጵያዊ እሴትን የማልበስ አቅምና ጉልበት እንዳለዉ ሁሉ ዛሬ የሚጮሁትን አክራሪ የጎሳ ብሄረተኞችን ሁሉ ቀስ ብሎ ይዉጣቸዋል:: ኢትዮጵያዊነት ምንድነዉ? ምንስ የጋራ እሴት አለዉ? ብሎ ለሚጠይቅ ሁሉ ካማዊነት ሴማዊነት ኩሻዊነት በጋራ ተገምደዉ ተዋዉጠዉና ተሰናስነዉ በዉህደት የፈጠሩት ኢትዮጵያዊ እሴት አለ:: ቴዲ አፍሮ የስነ ጥበቡ ጭብጥ ማጠንጠኛ ማዕከል ያደረገዉ ይሄን ኢትዮጵያዊነት የጋራ እሴት ነዉ:: እናም ቴዲ ላይ ጦር የሚያሰብቅበት ይሄንኑ ሀቅ በማቀንቀኑ የተነሳ ነዉ:: ጦሩ የተወረወረዉ ወደ ኢትዮጵያዊነት የጋራ እሴት ላይ እንጅ እንደ ግለሰብ ወደ ቴዲ አፍሮ ላይ አይደለም:: ቴዲን ማኮላሸት ከተቻለ ሌሎች በኢትዮጵያዊነት የጋራ እሴት ዙሪያ የሚያቀነቅኑ የስነጥበብ ባለሞያዎች እንዳይወጡ ማድረግ ይቻላል የሚል ታሳቢ ነዉ የተያዘዉ::

# ኢህአዴግ ሆይ 2900 ዓመታትን መልስልን!

መለሰ እንግዳ










> እኛ ያለንን አንፈልግም ብለን ወርውረን ለኪራይ የሀገራቱን አንጡራ ሀብት እያባከንን ሀገር መራን ማለት ይቻላል? አሁንማ ጅቡቲም አንገራገረች መሰለኝ ለ30 ዓመት በነጻ የኢትዮጲያን ከርሰ-ምድር ውሃ እንድትጠቀም መደረጉም የሰሞኑ ትኩስ ወሬያችን ነው፡፡

23 የክሽፈት ዓመታትን ያስቆጠረው ኢህአዴግ ምን እዚም እንደተደረገበት አይታወቅም ኢትዮጲያ ከተፈጠረች 100 ዓመቷ ነው ብሎን እርፍ! እኛም ደግሞ 3000 ዓመቷ ነው ብለን እንጽፋለን፡፡

ከወደብ ተጠያቂነት፣ ከድንበር ወሰን ጋር በተያያዘ ለሚነሱ ነበልባል ጥያቄዎች ምላሽ ከማጣቱ የተነሳ እኔ አይደለሁም አይነት አካሄድ ለመጠቀም የአገሪቱን ስልጣኔ በክህደት ከደመደመ ቆዬ፡፡

ኢትዮጲያ ገና እንደ ሀገር ስትመሰረት የነበሩት ጥንታዊ መንግስታትን ብንመለከት ፑንት፣ ዳማት፣ አክሱም፣ ላሊበላ እያለን እስከ ራሱ ኢህአዴግ ድረስ መምጣት እንችላለን፡፡ነገር ግን የህዝብ ኩራት ኢትዮጲያዊነት ስሜት የማይመቸው ኢህአዴግ የስልጣኔን ስረ መሰረቶች ለመደምሰስ ሞከረ እንጂ ከቶ ሊሳካለት እንደማይችል አሁን ሊገባው ባይችልም ወደፊት ሳይወድ በግድ እንደሚገባው መቶ በመቶ እርግጠኛ ሆኖ መናገር ይቻላል፡፡ምክንያቱም ሶስት ሺህ ዘመንን ተሻግሮ በጠንካራ ሰንሰለት የታሰረው ኢትዮጲያዊነት በአጭር ጊዜ ሊፈረስና ሊከሽፍ ስለማይችል፡፡

ስሙ ባልተጠቀሰ አንድ የግሪክ መንገደኛ (The periplus of the Eritrean sea) በተሰኘ ርዕስ ተፅፎ የተገኘው የመጀመሪያው አክሱማዊ ንጉስ ዞስካለስ እና ስሙ ከኖረበት ዘመን ጋር ከሰነዱ ገፅ የተለያየ አንድ አክሱማዊ ንጉስ በአዱሊስ ወደብ የንግድ እንቅስቃሴ ያካሂዱ እንደነበር ያስረዳል፡፡ባለመቶ ዓመት የስልጣኔ ባለቤቶች የሀገሪቱን የባህር በር ጠርቅመው ዘግተው ‹‹እነ ቦስትዋናና መሰል ሀገሮች ካለወደብ ነው ያደጉት›› በማለት ለማስተካከል ይሞክራሉ፡፡እሺ እነቦስትዋና ከጅምሩ ያልነበረባቸውን በጥረት አደጉ መልካም ነው፡፡እኛ ያለንን አንፈልግም ብለን ወርውረን ለኪራይ የሀገራቱን አንጡራ ሀብት እያባከንን ሀገር መራን ማለት ይቻላል? አሁንማ ጅቡቲም አንገራገረች መሰለኝ ለ30 ዓመት በነጻ የኢትዮጲያን ከርሰ-ምድር ውሃ እንድትጠቀም መደረጉም የሰሞኑ ትኩስ ወሬያችን ነው፡፡አጃኢብ! ‹‹ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባ›› አለ ወገን ያሳዝናል፣ ያሳፍራል፣ ያበሽቃልም፡፡

እነ ካሌብ ደቡብ አረቢያ ድረስ ተሻግረው ኢትዮጲያውያንን ይታደጉ አልነበረምን? ይደርስባቸው ከነበረው ጭፍጨፋ በኢህአዴግ ዘመን ምነው ኢትዮጲያዊነት ረከሰ፣ እንኳን በአረብ አገር በሰቆቃ ህይወታቸውን ለሚገፉ በርካታ እህቶቻችን መታደግ ቀርቶ እዚሁ ኢትዮጲያችን ውስጥም አልደላንም፡፡እማማ ኢትዮጲያማ ሶስት ሺህ ዓመት የስልጣኔ ባለቤት ናት፡፡

ሌላው ቢቀር በአክሱም የቆሙ ሀውልቶች፣ የእነ ላሊበላ ውቅር አቢያተ ክርስቲያናት፣ የእነ ፋሲለደስ ግንብ የየትኛው ስልጣኔ ውጤቶች ይሆኑ? ሁሉን ነገር ኢትዮጲያውያን ያውቃሉ፡፡

ኢህአዴግ ታሪክን ከነበረው ይዘት ቀይሮ ለራሱ በሚመቸው መልኩ በመቀሌ ዩንቨርስቲ አስተባባሪነት 60 ሚሊዮን ብር መድቦ እየሰራ አይደለምን (ከአገር በስተጀርባ አስራት አብርሃም) እናም ኢህአዴግ ሆይ 2900 ዓመታትን መልስልን ስንል በእርግጥም ከልብ ነው፡፡ልቦና ከሰጠን በቅንነት ከተግባባን አገራችን የሁላችንም ናት፡፡

## ስልጣኔና ብሄር ተኮር ፌደራሊዝም

ስልጣኔ የሚለውን ቃል በብዙ መልኩ ልንተረጉመው እንችላለን፡፡ለዚህ ጽሁፍ አመቺ የምንለውን ትርጉም ላስቀምጥና ወደ ሚቀጥለው ጉዳያችን እንገባለን፡፡እንግዲህ ስልጣኔ ስንል የሰው ልጅ የአስተሳሰብ ደረጃ ከነበረበት እየተሻሻለ እየተለወጠ ሲመጣ ከአኗኗር፣ ከአመጋገብ፣ ከአለባበስና እንዲሁም ከቴክኖሎጂ ጋር ከመወዳጀት ጀምሮ ያለውን ሊያጠቃልል ይችላል፡፡

በዚህ ከተስማማን ኢህአዴግ በአገራችን ስልጣን ከተቆናጠጠና አገሪቱን ከመሩ መንግስታት የቅርባችን አሁንም አብሮን ያለ ነው፡፡ሆኖም ከእርሱ ቀድመው ከነበሩት መንግስታት ሃገሪቱን በተሻለ በብቃትና፣ በአስተዋይነት ለመምራት እድሉንም በመዳፉ አስገብቶ ነበር፡፡ነገር ግን አልተጠቀመበትም፡፡የስልጣኔ ዘመን እየጨመረ ሲመጣ መንግስታዊ አስተዳደርም ዘመናዊ፣ አለማቀፋዊና ለዜጎች መብት ከለላነት ሙሉ ሽፋን የሚሰጥ መሆን ነበረበት፡፡ከኢህአዴግ በፊት ሁሉም አገራዊ ፍቅርና አንድነት የነበረው ህዝብ የኢህአዴግ ትውልድ ግን በአገሩ ጉዳይ ላይ "ምናገባኝ" የሚል እየተበራከተ የሄደበት ጊዜ ላይ ደርሰናል፡፡(ተርብ የሆኑ የአገር ፍቅር የሚያንገበግባቸው ዜጎች መኖራቸውን ሳንዘነጋ) ኢህአዴግ ብሄር ተኮር ፌደራሊዝም መጠቀሙ በእንዲህ አይነት አገራዊ መሰረት የተቃኘ ትውልድ እንዲፈጠር መንገዱን እንደከፈተ ብዙዎች ይስማማሉ፡፡የዚህች መጣጥፍ አቅራቢም በብሔር ብሔረሰቦች እኩልነት ያምናል፡፡ነገር ግን ኢህአዴግ ጭምብሏን ተጠቅሞ የኢትዮጲያን አንድነት ከአጭር የስልጣኔ ባለቤትነት ጋር በማስተሳሰር ለማኮላሸት እየጣረ ነው፡፡

ሌላው ኢህአዴግ የአገሪቱን ስልጣኔ በመቶ ዓመት የደመደመበት ምክንያት "የሶስት ሺህ የስልጣኔ ባለቤት" የሚለውን ዓረፍተ ነገር ስንመለከት ፍጹም የሚያግባባና ኩራትን በመላው ኢትዮጲያዊ የሚያሰርጽ ሁላችንንም አንድ የሚያደርግና ብሔራዊ ኩራታችንን የሚጨምር በመሆኑ ለኢህአዴግ አትዋጥም፡፡ስለዚህ ብሔራዊ ክብርን በማኮሰስ ብሔራዊ ውርደትን መጥራት፡፡

ገዥው ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘበት ጊዜ አንስቶ በተለያዩ ጊዜያት፣ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ህዝቦች በባህል ተከባብረው፣ ተጋብተው፣ ተሳስበው በሚኖሩበት ረጃጅም እጆቹን እንደ ፍላጻ በመወርወር ማድማቱን እንደቀጠለ ነው፡፡ስልጣኔን በማራከስ በወንድማማች መካከል ግጭትን መዝራት አለመተማመንን መዘርጋት በኢትዮጵያውያን ዘመን ተሻጋሪ የትብብር መንፈስ መክሸፉ አይቀርም፡፡ ከደማችን ጋር የተዋሀደውን የኢትዮጲያዊነት ስሜት፣ ለዘመናት ፀንቶ የቆየው ማንነታችን እንዲህ በቀላሉ ማልፈስፈስ የሚቻል አይመስለኝም፡፡

## መፍትሄው ምንድን ነው?

እንደ እኔ እምነት በኢትዮጲያ ጉዳይ ላይ ያገባናል የሚሉ የሀገሪቱ ልሂቃን በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ ያሉ አንጋፋ ምሁራን ፍጹም ቅንነት በተመላበት መልኩ ለብሔራዊ እርቅ ሃገራዊ መግባባት ላይ ለመድረስ የሚቻልባቸውን መንገዶች ያለመታከት መቀስቀስና መጠቆም ሲቪክ ማህበራት፣ የታሪክ ባለሙያዎች እንዲሁም የሀገር ሽማግሌዎች አገሪቱ ያለፈችባቸውን ቀደምት የስልጣኔ ዳናዎች በመጥቀስ ኢትዮጲያዊነት ወደ ቀድሞው ስሜት የሚመለስበትን አቅጣጫ በማሳየት በግልፅ መሳተፍ የታሰሩ የፖለቲካና የህሊና እስረኞች ጋዜጠኞችን እንዲሁም የሙስሊሙ ማህበረሰብ መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴዎችን ከመንግስት ጋር በግልፅ በመነጋገር የሚፈቱበትን መንገድ መጥረግ፡፡

በመጨረሻም ኢትዮጲያዊነት እናጥፋው ቢሉ የሚይጠፉ፣ እናኮስሰው ቢሉ ፈጽሞ ሊኮስስ የማይችል ዘመን ተሻጋሪና እንደ ከበረ ድንጋይ በተራራው አናት ላይ ሲበራ የሚኖር እንጂ በ100 ዓመት ተገድቦ በፕሮፖጋንዳ ጋጋታ የሚተንና የሚናድ እንዳልሆነ ኢትዮጲያውያን እናውቃለን ኢህአዴግም ያውቀዋል፡፡ "በውኑ ኢትዮጲያዊ መልኩን ነብር ዥንጉርጉርነቱን ሊቀይር ይቻለዋልን?" እንዲል ታላቁ መጽሐፍ፡፡

ክብር ለኢትዮጲያዊነት ይሁን!

# እኔን የሚያበሽቁኝ

ብዙሀን መገናኛዎቻችን
በተለይ FM ሬድዮናችን
በተለይ ፕሮግራማቸው
በተለይ አዘጋጅ ጋዜጠኞቹ

## በመጀመሪያ የመገናኛ ዘዴዎች ታሪክ እና ዓይነታቸው፤

የብዙሃን መገናኛ ዘዴዎች በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ተለይተው ሊታዩ ይችላሉ፡፡ እነሱም የህትመት እና የኤሌክትሮኒክስ ብዙሃን መገናኛ ዘዴዎች በመባል ድልድል ይወጣላቸዋል፡፡ በአለም ታሪክ እንደሚታወቀው የህትመት ብዙሃን መገናኛ ዘዴው ከ550 ዓ.ም ገደማ በፊት እንደተጀመረ ይነገርለታል፡፡ በጀርመናዊ ጉተንበርግ የመፃፊያ መኪና የፈጠራ ግኝት መውጣቱን ተከትሎ ማለት ነው፡፡ በእርግጥ የሰው ልጅ የድንጋይ ላይ ፅሁፍ ከጀመረ ብዙ ሺህ ዓመት ነጉደዋል፡፡ ወደ ሀገራችን ኢትዮጲያ ስንመለስ የህትመት ስራ ከብዙዎቹ የአፍሪካ ሀገሮች ቀድሞ በኢትዮጲያ የዘመናዊ ስልጣኔ አባት በሚባሉት በአፄ ምኒልክ በ1881 ዓ.ም እንደተጀመረ ታሪክ ያስረዳል፡፡ የመጀመሪያዋ ጋዜጣም አዕምሮ በመባል ትጠራ እንደነበረ የህትመት ጊዜዋም ሳምንታዊ በመሆን በ200 የቅጅ ብዛት ለቤተ መንግስት አካባቢ ሰዎች እንደምትሰራጭ ዋና ይዘቷም የኢትዮጲያን ነፃነትና የግዛት አንድነት በሰፊው ማስፋትና የአንድነትን ጠቃሚነት ከማንኛውም ህዝባዊ ጉዳይ በላይ አድርጎ ለማሳየት መሞከር እንደሆነ የጋዜጣዋ ታሪክ ያስረዳል፡፡ በእርግጥ የጋዜጣዋ ዋነኛ ዓላማ የነበረው በዘመኑ የአውሮፓ ኢምፔሪያሊስቶች አፍሪካን የመቀራመት ሴራ ውጤቱ አስከፊ በመሆኑ ሀገራችን ለነጻነት እና ለሉዓላዊነት መከበር የምንከለፍውን ተጋድሎ ከፍተኛ የታሪክ, የህዝብ አደራ መሆኑን በአንክሮ ለአምፔሪሊስት ፊታውራሪ መሪዎች ለእንግሊዝ, ፈረንሳይ, ጣሊያን … ማሳየት እንደነበረም መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ ነው፡፡ የህትመት ብዙሃን መገናኛ ዘዴው ከአፄ ምኒልክ በኋላ በመጡት ገዥዎች የየራሱን ልዩ ልዩ ገፅታ እያስተናገደ ዛሬ ካለበት ካለበት ደረጃ ላይ ሲደረስ በኢትዮጲያ እንደብዙዎች የስልጣኔና የጀግንነት, ተምሳሌቶች ቁልቁለት እየወረደ ክሽፈቱን እያፋጠነ ይገኛል፡፡ ካለንበት 21ኛ ክፍለ ዘመን አንጻር ምንም ይህ ነው የሚባል ጉልህ ለውጥ ማምጣት ተስኖት ማለት ነው፡፡

ሌላው እና ሁለተኛው ብዙሃን መገናኛ ዘዴ ዛሬ በአለም ላይ በከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኘው የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ነው ይህም ቴሌቪዥን, ሬድዮ እና የድህረ-ገፅ መገናኛ ዘዴወችን አጣምሮ የያዘ ነው፡፡ ወደ ኢትዮጲያ ተጨባጭ ሁኔታ ስንመጣ በሶስቱም የኤሌክትሮኒክስ የስርጭት ዘዴዎች እዚህ ግባ የማይባል ሁኔታ ይታያል፡፡ በሀገሪቱ በመንግስት ባለቤትነት የተያዘ አንድ የቴሌቪዥን ጣቢያ እና ከሁለት የማይበልጡ ብሄራዊ ሽፋን ያላቸው ሬድዮ ጣቢያዎች እንዲሁም የተወሰኑ በመንግስት የሚተዳደሩ የFM ጣቢያዎች ይገኛሉ፡፡ በዋና ከተማችን ከሚገኝ የFM ሬድዮ ጣቢያዎች 1 ጣቢያ ነው በግል ይዞታነት የሚተዳደረው ሸገር 102.1 ነው፡፡

ሁሉም ሬድዮ ጣቢያዎች ማለት በሚያስደፍር መልኩ የህዝብ ወገንተኝነትን ሳይሆን የመንግስትን የፕሮፖጋንዳ ተግባር ያስፈፅማሉ፡፡ በአብዛኛው በሀገሪቱ ሰማይ ስር ልማት, ልማት, ዕድገት ዕድገት, ሰላም ሰላም ዲሞክራሲ ዲሞክራሲ ሞልቶ እንደተትረፈረፈ, የህዝቡም ኑሮ በጣም እየተሻሻለ, በጥቅሉ ማርና ወተት እየዘነበ መሆኑን ነጋጠባ የሚደሰኩሩት ተግባራቸው ነው፡፡ከዚህ የተረፈውን ጊዜም ለሀገራችን ወጣቶች ምንም ፋይዳ ሊያመጣ የማይችለውን ይልቁንም የራስን አስረስቶ የሌሎቹን የማያስናፍቀውን የአውሮፓ እግር ኳስ በጥልቀት, በስፋት በሙሉ ጊዜ ስርጭት እየተቀባበሉ ያራግቡታል፡፡

አንድ የሚድያ ተቋም የራሱ የሆነ ኃላፊነት እንዳለበት እየታወቀ, ህዝብ ያለበትን ወቅታዊ ችግር በመፍትሄ ለውሶ እንደማቅረብ, በሱስ እየናወዘ የሚገኘውን ትውልድ ሌላ የስነ-ልቦና ማስኮብለያ ዘዴ እየፈጠሩ ከራሱ ከሀገሩ መነጠል ተገቢ ባልሆነም ነበር፡፡ ግን እየሆነ ያለው ፍንትው ብሎ የሚታየው ይሄ ሀቅ ብቻ ነው፡፡

መሽቶ ሲነጋ ስለ አውሮፓ እግር ኳስ ብቻ የሚወራባት፣ የሚተነተንባት፣ የራሷ ዘርፈ ብዙ ችግሮች ያሉባት ሀገር ኢትዮጲያ ነች፡፡

ባለፈው ቅዳሜ ግንቦት 30 የወሩ የመጨረሻ ቅዳሜ በስራ የደከመ አዕምሮየን ለማዝናናት በከተማይቱ ከሚሰራጩ FM ጣቢያዎች አንዱ ላይ አድርጌ ስፈልግም ጣቢያ እየቀያየርኩ በምፈልገው መጠን ባይሆንም በተገኘው ልክ እያደመጥኩ በነበረበት ጊዜ ከሸገር FM 102.1 ታዲያስ አዲስ ከተባለው ፕሮግራም አንድ ለራሴ የገረመኝ ነገር ሠማሁ፡፡ አንዲት አድማጭ ወደ ጣቢያው ስልክ ደውላ ፕሮግራሙን እንዴት እንደምትወደው ገለጸች አያይዛም ቅንጡ ውሻዋ፤ ሙዚቃ እንዴት እንደምትወድ በኩራት እያወራች ሙዚቃ ስትሰማ በዳንስ ፍቅር ልቧ የሚጠፋውን ውሻዋን ሙዚቃ በማስደመጥ ለፕሮገራሙ አድማጮች ምስክርነቷን አረጋግጣ ስትጨርስ በድጋሚ የጣቢያው ጋዜጠኞች ስንዱ ለተባለችው ውሻ ሙዚቃ በመጋበዝ ከእንስሳት ወደ ሰውነት ሊያሳድጓት ችለው ነበር፡፡ የውሻዋ ባለቤት ስለውሻዋ የህይወት ታሪክ ከዚህ ቀደም ስላጋጠሟት የውሻ ገጠመኞች እና ገድል እየተረከች እርሷም የነደደ የውሻ ፍቅር ጭምር እንዳለበት ገልፃ ይህንን ባደረገችበት ተሳትፎዋ የገንዘብ ሽልማት በስጦታነት ተበርክቶላት ወጣች፡፡ ልብ በሉ እንደ ጋዜጠኛው የተሰጠው የገንዘብ ሽልማት ውሻዋን ጭምር ታሳቢ ያደርግ ነበር፡፡

አሁን እኔን ወደ አበሸቀኝ ጉዳይ ስመለስ እነዚህ ፕሮግራሞች በልዩ ልዩ የአገልግሎትና የንግድ ተቋማት ገንዘብ ድጋፍ አድራጊነት /sponsorship/ ከጣቢያው የተገዙ የአየር ሰዓታት ናቸው፡፡ የገንዘቡ ከፋዮች ወይም ማስታወቂያ አሰሪዎች በደንብ ልታጤኑት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ እናንተ በከፈላችሁት ገንዘብ ውሻ ሙዚቃ እየተጋበዘበት ለውሻ መዝናኛ ገንዘብ ስጦታ እየተሰጠ ነው፡፡እናንተ ይህን በምታደርጉበት ጊዜ በርካታ ወገኖቻችሁ በረሃብ ጠኔ ተይዘው የጣራሞት ድምጽ እያሰሙ በክፍ ደዌ ተይዘው የህክምና ተቋማትን በር በገንዘብ እጥረት ምክንያት መርገጥ ተስኗቸው የሞት ጣር እያጣጣሩ ድምጻቸው የወገንን ርዳታ እየተማጸነ የድረሱልኝ ጥሪ እያሰማ ነው፡፡ በሌላ በኩል ብሶታቸውን ችግራቸውን ሮሮዋቸው የሚተነፍሱበት አማራጭ ዘዴ ባለማግኘታቸው የወገን ያለህ እያሉ የመከራ ህይወት እየገፉ ናቸው፡፡

እናንተ በተለይም ፕሮግራም sponsor በማድረግ የገንዘብ ድጋፍ የምታደርጉ የንግድና የአገልግሎት ተቋማት በደንብ ልታስቡበት የሚገባ ጉዳይ ይመስለኛል ሀብትም ዝናም ከሀገር ጋር ነው፡፡ ሀገር ደግሞ እንደ ሀገር ቆሞ ለመታየት የሁሉም ሰው

ወደ ገጽ 15 ዞሯል

# ልማታዊ መንግስት ...

ከገጽ 16 የዞረ

ራሱን መከላከል የማይችልን ሰራዊት ከመበተን ውጭ ምን ምርጫ ይኖራል?

ለበጎውም ለክፉውም ተጠያቂው ሁልጊዜ ሌላ ነው:: እንዲያውም ይህ የአፍሪካውያን በተለይም የምስራቅ አፍሪካ ችግር ይመስለኛል:: ለምሳሌ ሶማሊያ ሂዳችሁ አንድን ሶማሌ ለምንድነው መንግስት የሌላችሁ፤ ይህን ያህል ጊዜ የአለም መሳቂያ የሆናችሁ ብላችሁ ብትጠይቁት መልሱ 'በኢትዮጵያ ምክንያት ነው' ነው ሊሆን የሚችለው:: ራስን መጠየቅ፤ እውነታን መጋፈጥ መንፈሳዊ ወኔ ይጠይቃላ:: ቅንጅት ፈረሰ:: ማን አፈረሰው? አቶ እከሌ:: አለቀ:: ከዚያ በቃ ስድብና አሉባልታ ነው:: እንዴት አርጎ አፈረሰው? በምን ምክንያት አፈረሰው? የሚሊዮኖችን ድርጅት አንድ ሰው እንዲያፈርሰው እንዴት እንፈቅድለታለን፤ እኛ ሞተን ነው በቁማችን? አንዱ ፓርቲ ቢያፈገፍግስ የቀሩቱ ለምን አልቀጠሉም? ወዘተ የሚሉ መሰረታዊ ጥያቄዎችን ማንሳት ከእውነት ጋር መታረቅን፤ ሀላፊነት መውሰድን ይጠይቃል:: ራስን መጠየቅ ደግሞ በጣም ያስፈራል:: ለሁሉም ችግር ኢህአዴግን እያሙ መኖር ሲቻል ለምን ራስህን ትጠይቃለህ? ግን ከእውነት የተጣላ ህዝብ ትንሳዔ አይኖረውም:: እውነት መነጋገር መጀመር ይኖርብናል:: መንግስት ከሰማይ አይወርድም፤ ከህዝቡ ነው የሚወጣው:: ቀዳማውዊ ኃይለስላሴ አርበኞችን እያገለሉ ባንዳ በመሾም ይወቀሳሉ:: እውነቱ ግን ግማሹ የኢትዮጵያ ህዝብ በሰባራ የጣሊያን ሊሬ የሚታለል ባንዳ ነበር:: እነበላይ ዘለቀን አምስት አመት ሙሉ ሲጠዘጥዛቸው የነበረው የጣሊያን ወታደር ሳይሆን በሰባራ ሊሬ የተገዛ ጎጃሜ ነበር:: በትግራይ፣ በጎንደር፣ በኢሊባቦር ወዘተ ብናይ ታሪኩ ተመሳሳይ ነው:: አፄ ምኒሊክ የአድዋን ዘመቻ ሲያውጁኮ ለኢትዮጵያ ህዝብ አገራችን ተደፍራለችና ጠላታችን መክተን እንመልስ አይደለም ያሉት፤ ለልጆችህ፣ ለሚስትህና ለዕምነትህ ስትል ተከተለኝ ነው ያሉት:: በሚገባው ቋንቋ፤ በግል ህይወቱ ነው የመጡበት:: ያኔ ይቅርና በ 21 ኛው ክፍለ ዘመን ለምን ከተማ ይስፋፋል ብሎ የሚቃወም ከጎጡ ያለፈ ማሰብ የማይችል ትውልድ እኮ ነው ያለው (የፖሊቲካ ትርፍ የሚያገኙ መስሏቸው እንዲህ አይነቱ ጎጠኛ ጥያቄ ፍትሀዊ መሆኑን ሊነግሩን የሞከሩ 'ተንታኞችም' አይተናል):: ይህ ሁሉ የመንግስት ፖሊሲ ያመጣው ነው ምናምን ማለት ይቻላል:: ነገር ግን መንግስት ጭንቀላቱን የወሰደበት ሰው የለም፤ ማሰብ መቻል የእያንዳንዱ ሰው ሀላፊነት ነው::

እንዲያውም ስለተጠያቂነትን አመክኗዊ ብንሆን ከብዙ ስህተት በዳንን:: ከአስር አመት በፊት የገጠመኝን ላውጋችሁ:: አንድ አዲስ አበባ ሜክሲኮ ታክሲ መያዣው ላይ የሚለምኑ ትግሬ ነበሩ:: አንድ ቀን ታክሲ ውስጥ እያለሁ እኒያ ትግሬ መጥተው ስለአቡነአረጋዊ ብለው ይለምናሉ:: ፊት የተቀመጠው ተሳፋሪ ብስጭት ብሉ ሂድ ከዚህ አንተ ቆሽቋሻ ትግሬ፤ ኧረ ከላይና ከታች ሁናችሁ እንደ ሳንዱይች ጠበሳችሁን ሲል ሁላችንም ባነጋገሩ ሳቅን:: ግን በምን ሂሳብ ይሆን ኢህአዴግ በሚሰራው ግፍ እኒያ ምስኪን የሚጠየቁት? እንደአብዛኛው ኢትዮጵያዊ በፍርሃትና በጉስቁልና የሚኖር ትግሬ ምን ተጠያቂነት አለበት? ህዝባዊ ውክልና የሌለው አምባገነን መንግስት ይቅርና በህዝብ የተመረጠ መንግስት እንኳን ቢሆን ለሰራው በደል ተጠያቂነቱ ያ መንግስት በሰራው ወንጀል ተሳታፊ የሆኑት ግለሰቦች ብቻ ናቸው:: በመንግስት ሀጢያት ህዝብ የሚጠየቀው በምን ሎጂክ ነው? ባለፉት ዘመናት 'የአማራ' ገዥዎች የፈጸሙት በደል ካለ (ካለ የምለው በአለም ላይ ጉልበት እንጂ ሰብአዊ መብት የሚባል ጽንሰ ሀሳብ ባልነበረበት ዘመን የነበሩ ነገስታትን በሰብአዊ መብት ጥሰት መክሰስ መሀይምነት ስለሚመስለኝ ነው) አብሮ ሲበደል የኖረው አማርኛ ተናጋሪ ህዝብ ምን ተጠያቂነት አለበት? አንድ ሰው እንኳን በገዥወቹ በደል ይቅርና ወላጅ አባቱ በሰራው ወንጀልም የሚጠየቅበት ምክንያት የለም:: አብዛኞቻችን ግን ከስሜት ሆያሆየ ወጥተን እንዲህ ያሉ እውነቶችን መቀበል ያስቸግረናል::

<u>መ. የመቻቻልና የመተባበር መንፈስ</u>

መቻቻልና መተባበር ለአፍሪካውያን ብርቅ ናቸው:: ብዙ ሰው ይህን አለመቻቻል የአፍሪካ ህዝቦች የተለያየ ቋንቋ ተናጋሪ ከመሆናቸው ጋር ያያይዙታል:: ይህ ስህተት ነው:: ሲጀመር የተለያየ ቋንቋ የሚናገሩት የአፍሪካ ህዝቦች ብቻ አይደሉም:: እንዲያውም የቋንቋና ሀይማኖት መመሳሰል የመቻቻል ቅመም ቢሆን ኖሮ ሶማሊያ የመቻቻል ተምሳሌት በሆነች ነበር:: እውነቱ ከድንቁርና ወጥቶ ከጎጥ ባሻገር ማየት አለመቻል ነው:: ችግሩ ሳይለፉ ባቋራጭ ደጃዝማች መሆን መፈለግ ነው:: ለምሳሌ በጎሳ የተደራጁ የፖለቲካ ቡድኖች ሁሉ የጎሳቸው ዘላቂ ጥቅም ከአጠቃላዩ የኢትዮጵያ ህዝብ ጥቅም የተለየ እንዳልሆነ የሚረዱ ይመስለኛል:: ግልጽ እኮ ነው፤ የኢትዮጵያ ህዝብ መሰረታዊ ችግር ድህነት፣ ኋላቀርነት፣ የፍትህ መጓደል፣ የዲሞክራሲና ነጻነት እጦት ወዘተ ናቸው:: እነዚህ ችግሮች ደግሞ ሊወገዱ የሚችሉት በየጎጡ በመፍጨርጨር ሳይሆን አገራዊ ራዕይ ሰንቆ በጋራ በመስራት ነው:: እያደጉ ያሉት እስያዊያንም ሆነ ሌሎች የበለጸጉ አገራት ታሪክ በሙሉ የሚያረጋግጠው ይህንኑ ነው:: ነገር ግን ራሳቸውን የየጎሳቸው የማይተካ ደጃዝማች አርገው የሚያቀርቡ ግለሰቦች ከሌላው ጋር በጋራ ለመስራት ያስፈራቸዋል:: ውድድር ያስፈራላ:: ከሌላው ጋር መስራት በቋንቋ አጋጣሚ ሳይሆን በሀሳብ ጥራትና ተጨባጭ ውጤት መመዘን ያስከትላላ:: ኤርትራ ባትገነጠል ኑሮ ወይ መለስ ወይ ኢሳያስ ምትክ የሌለው መሪ የመሆን እድላቸው ያከትም ነበር:: ያን ደግሞ አይፈልጉትም:: አሁንም እኮ በኢትዮጵያ 'ቅኝ ገዥነት' ተማረው መገንጠል የሚሹት ሀይሎች ህልማቸው ራሳቸውን እንደ ኢሳያስ ምትክ የሌለው መሪ ማድረግ ነው:: እንጂማ ኤርትራን ማየት ብቻ ከመገንጠል የሚያተርፍ እንደሌለ በተረዱ ነበር:: መቸም ከኤርትራ የተሻለ ስትራቴጂካዊ መልክዐምድር ወይ ደግሞ ከሻእብያ የተሻለ አደረጃጀትና የአመራር ልምድ አለን ብለው እንደማያስቡ እገምታለሁ::

በአገራዊ ጉዳዮች ላይ ለመተባበር ተመሳሳይ መልክ፣ ጸባይ፣ የፖሊቲካ አቋም ወዘተ አያስፈልግም:: እንደ ህዝብ ዘላቂ ጥቅማችን የተሳሰረ መሆኑን መረዳት ብቻ ይበቃል:: ብዙዎቻችን ግን ሁሉን ነገር በአጭር ጊዜ የፖለቲካ መነጽር ነው የምናየው:: ኢህአዴግ ግድብ ሲሰራ የሚያማቸው ኢትዮጵያውያንን ማየት በጣም ያማል:: የረቀቀ አጀንዳ ካላቸው ምዕራባውያን 'የአካባቢ ጥበቃ ተቆርቋሪዎች' ጋር ሆነን በማናውቀው የምንጮህም አለን:: ሰሜኒያ በመቶው ህዝብ የኤሌክትሪክ ብርሀን በማያውቅበትና የአገሪቱ የደን ሽፋን በአስደንጋጭ ሁኔታ ተጨፍጭፎ እያለቀ ባለበት አገር ይኼ ግድብ ያንን ደረጃ (ስታንዳርድ) አያሟላም ወዘተ እያሉ አፍሪካን ከትርፍ የምግብ እህል ማራገፊያነት ባለፈ የማያዩ ተመጻዳቂዎችን ፕሮፖጋንዳ ማስተጋባት ደመኝነት ነው:: አላማችን አገራዊ ከሆነ ወያኔ ይቅርና ሰይጣንም ቢሆን ኢትዮጵያ ውስጥ ግድብ የሚሰራ ከሆነ ከቻልን ድንጋይ ማቀበል ነው ያለብን:: መተባበር

ያለብህ ለኢትዮጵያ ስለሚበጅ እንጂ ግላዊ የአጭር ጊዜ ትርፍ ስለሚያስገኝልህ መሆን የለበትም:: ከእስያውያን መማር ያለብን ሌላው ቁልፍ ጉዳይ ይህ ይመስለኛል፤ ትልቁን ስዕል ማየት::

ሠ. ታታሪነትና ተወዳዳሪነት

ኢትዮጵያውያን ሰነፎች ነን በሚለው ቁንጽል አነጋገር አልስማማም:: የአገራችን ገበሬና ነጋዴ የምሳ ጊዜ እንኳን አያውቅም:: የተማረውም ቢሆን ለግል ጉዳዩ ልቡ እስኪጠፋ ነው የሚሰራው:: አበሻ የሚያለምጠው የሚሰራው ስራ የተለየ የአጭር ጊዜ የግል ጥቅም ካላስገኘለት ብቻ ነው:: ለምሳሌ ተቀጣሪ ሲሆን ቢተጋም ባይተጋም ደመወዙ እንደማይቀርበት ያውቃል:: ያኔ ማልመጡ ነው:: የሃላፊነት ስሜት ለአብዛኞቻችን ባዕድ ነው:: የአገር ፍቅርም በአብዛኛው ከፉከራ አያልፍም:: እያንዳንዳችን በየተሰማራንበት የምናደርገው ተደምሮ አገራዊ ፋይዳ እንዳለው ያ ደግሞ ሲሆን በህይወታችን የምናየው ያ ባይሆን እንኳን ልጆቻችን አንገታቸውን ቀና አድርገው እንዲሄዱ የሚያስችል ውጤት እንደሚያመጣ ወይ አይገባንም ወይ ግድ የለንም:: ደሃ የሆንነው በምርጫችን መሆኑን የምንረዳ አይመስለኝም:: በድሮው ጊዜ ድህነት እዳ ነበር፤ አሁን ግን ምርጫ ነው:: ድህነት ማጥፋት ተዓምር መስራትን አይጠይቅም:: ድህነትን የተጸየፉ ህዝቦች በአጭር ጊዜ አሽቀንጥረው ሲጥሉት አይተናል:: እኛም ድህነትን አሽቀንጥረን የማንጥልበት ምንም ምክንያት የለም፤ ግን ሀላፊነት መውሰድ ይኖርብናል:: ያ ደግሞ ሁሉን መቃወም ብቻ ሳይሆን መደጋገፍን ይጠይቃል:: ተወዳዳሪነትንና በተገቢ ውድድር ማመንን ይጠይቃል:: አውቃለሁ ውድድር ለብዙወቻችን ያስፈራል:: ለምሳሌ በአራችን ወደ መቶ የሚጠጉ የፖለቲካ ፓርቲወች አሉ:: አንድላይ የማይሰሩት መሰረታዊ የሆነ የአይዲዮሎጂ ወይም ሌላ ልዩነት ስላላቸው አይደለም፤ ውድድርን ስለሚፈሩ እንጂ:: ሁሉም ራሱን የየጎሳው እንደራሴ አድርጎ የሚያቀርበው እኮ በዋነኝነት ውድድርን ከመፍራት ነው:: የግላችን የሆነው ተምረንም የማይለቀን ምቀኝነት የሚባል በሽታ በመሰረቱ ጤናማ ውድድርን ከመፍራት ነው የሚመነጨው፤ ከውድድር ጣጣ ለመዳን ተወዳዳሪውን ማጥፋት:: መቀጠል ይቻላል::

## ማጠቃለያ

እንደቻይና ብልጽግናን የሚሻ ህዝብና መንግስት እንደቻይናውያን በኮንፊሽሲዝም ማመን የለበትም:: እንደቻይናውያን ጠንካራ አገራዊ ራዕይ፣ እውነተኛ የአገር ፍቅርና የሃላፊነት ስሜት፣ የመቻቻልና የመተባበር መንፈስ፣ ታታሪነትና ተወዳዳሪነት ሊኖሩት ግን የግድ ይላል:: ከምንም በላይ አንድ ህዝብ የራሱን መስቀል መሸከም የግድ ይለዋል:: በአለም ታሪክ ዋሽንግተን ዲሲ በመሰለፍ የመጣ ለውጥ ስለመኖሩ አንድም ማስረጃ የለም፤ ሊኖርም አይችልም:: ሰብአዊ መብት፣ የህግ የበላይነት ወዘተ ከዲስኩር (ሪቶሪክ) ባለፈ የማንም አገር የውጭ ፖሊሲ ማጠንጠኛ ሆኖ አያውቅም:: አለም አሁንም በአመዛኙ የውድድር እንጂ የትብብር መድረክ አይደለችም:: ስለሆነም የምር ለውጥ ከፈለግን በግልም በጋራም መጠየቅ ያለብን ራሳችንን ይመስለኛል:: በዚሁ ላብቃ::

ስላም

# ሰልስቱ ...

ከገጽ 5 የዞረ

የቅንጅትን አመራሮች እና ደጋፊዎች እስሩንም ፣ጠብመንጃውንም፣ህጉንም፣ፕሮፖጋንዳውንም ተጠቅሞ ደብድቧቸው እስካሁንም ስማቸው እንዳይነሳ የሚፈልገው::

## ተስፋ አለ?

ስልሳን ሳይደፍኑ ሞት የቀደማቸው አቶ መለስ የሚመሩት ፓርቲ ዋና ከመሆን አልፈው ፓርቲው ማለት እሳቸው፤ እሳቸው ማለትም ሃገር እስከ ሚመስል ድረስ የአምባገነንነትን ከፍታ ረግጠው ነበር::ሰውየው ወደ አምባገነንነቱ ከፍታ ይወጡ የነበረው ዋና ዋናዎቹን የዲሞክራሲ መርሆዎች እየረጋገጡ ስለነበር የዲሞክራሲ እምብርት የሆነውን በምርጫ መንግስትን የመቀየርን ተስፋ እያደር አስልለውት ወደ ማይቀረው ሄደዋል::አሁን አቶ መለስ የሉም! በሚታይ ሁኔታም የእርሳቸውን የአምባገነንነት ጫማ ሞልቶ አድራጊ ፈጣሪ የሆነ አመራር ፓርቲው ያገኝ አይመስልም::ይህ ማለት ኢህአዴግ ሳይወድ በግድ ወደ ቡድን አመራር እየገባ ነው ማለት ነው::በቡድን አመራር ውስጥ ደግሞ ሁሌ በአንድ አይነት ሁኔታ ማሰብ አይቻልምና እንደ 2002ቱ ምርጫ ኢህአዴግ ፓርላማ ወንበርን ሁሉ ጠቅልሎ የመያዙ አካሄድ ቢያንስ ለተመልካች ሲባል በሁሉም የፓርቲው ዘዋሪዎች ዘንድ ተቀባይት ላያገኝ ይችላል::በመሆኑም በምርጫ የሚወዳደሩ ፓርቲዎች በተሻለ ሁኔታ ኢህአዴግን በምርጫ የሚገዳደሩበት ሁኔታ የመፈጠር እድሉ ከባለፈው ምርጫ አሁን የተሻለ ይሆናል::በተወዳደሪ ፓርቲዎች በኩልም ኢህአዴግ የምርጫ ቦርድን እና ሌሎችን የዲሞክራሲ ተቋማትን ጠፍንጎ የያዘበትን እጁን ያላላ ዘንድ አበክረው መስራት ይኖርባቸዋል::ለዚህም በየሳምንቱ በየፓርቲው ስም ሰላማዊ ሰልፍ ከመጥራት በዘለለ የገዥውን ፓርቲ ገታራ አቋም ሊፈታተኑ የሚችሉ የተለያዩ የትግል ስልቶችን ለመጠቀም በሚያመሳስላቸው መስክ በጋራ መቆም ይጠበቅባቸዋል::

## እሳቤ ሁለት፣ አሁንም ጠብመንጃ?

ደርግ ለሰላማዊ የመንግስት ለውጥ መንገድ ባለመክፈቱ ባለጋራዎቹ በጥይት ቋንቋ ያናግሩት ዘንድ ግድ ነበር::ከጅሩ የኮሎኔል መንግስቱ ኃ/ማርያምን ታሩ በሽጉጥ በመጭረፍ የትጥቅ ትግልን በዋና ከተማ የጀመሩት ኢህአፓዎች ነበሩ::ለውጥ ፈላጊዎቹ ትግላቸውን ከዋና ከተማ ወደ አሲምባ ዳገት ለማድረግ እዛው ሲደርሱ የትግራይ ምድር ለትግራዊ አማፅያን ብቻ ባይ የህወሃት ተጋዳላዮች በአንድ በኩል የደርግ ጥይት በሌላ በኩል እንደገና ዳቦ በሁለት ስለነደደባቸው ፍፃሜያቸው አሳዛኝ ተሸናፊነት ሆነ::

በእነሱ መቃብር ላይ የለመለመው ህወሃት ታዲያ ራሱን ኢህአዴግ ወደ ሚባል ግዝፈት አሳድጎ ደርግን መገንደሱ ተሳካለት::ስልጣንን በብዙ የሚወድ መንግስትም ሆነና ባለጋራን ለማስተናገድ ባለ ሳምንት ሆነ::ኢህአዴግ ተቀናቃኞቹን ሁሉ በፍቅር ሰብስቤ በሃገሪቱ አካታች መንግስት መስርቻለሁ ቢልም ገና ከጠዋቱ ነበር ብረት አንግተው እርሱ ጥሎት ወደ መጣው ጫካ የነጎዱ ባለጋራዎች የተነሱበት::በተለይ አርበኞች ግንባር የሚባለው ታጣቂ ቡድን ኢህአዴግ በመጀመሪያዎቹ የስልጣን ዘመኖቹ ሞከር ያደረቸውን በጎ የዲሞክራሲ ጅማሬዎች ለማየት እንኳን ፋታ ሳይሰጥ ነው ወደ ጫካ የገሰገሰው::ስለሆነም የዚህ ቡድን የትግል እድሜ ከኢህአዴግ ረዥም የስልጣን እድሜ እምብዛም አያንስም::በውጤት ደረጃ ሲታይ ግን ቡድኑ አለም የለምም ለማለት በሚስቸግር ወደ አለመኖር ባደላ ሁኔታ ላይ ይገኛል::በእርግጥ ኢህአዴግም ደርግን ለመጣል በማግስቱ አልተሳካለትም ይልቅስ አስራ ሰባት መራራ የትግል ጊዜያትን ጠይቆት ነበር እንጅ::የኢህአዴግ ትግል ግን ነፍስ ያለው፣እታገልልታለሁ ይለው ከነበረው ህዝብ ጋርም በመገናኛ ብዙሃን እየተገናኘ ስለድል ውጤቱ ሲናገር መኖሩ ይታወቅ ነበር፤ትግሉም ከቀን ቀን የሚያድግ በኋላም ወደ ድል የተለወጠ ነበር::የአርበኖች ግንባር ግን ይህን ሁሉ ሲያደርግ ያልተስተዋለ እንዲሁ እንደ ተረት አለ ተብሎ ሲነገርለት (ለዛውም በጣም አንዳንዴ) ብቻ የሚሰማ አፈ ታሪክ ወደመምሰሉ የሚያደላ ቡድን ነው::

ሌላው በትጥቅ ትግሉ ጎራ ሊጠቀስ የሚችለው ድርጅት ኢህአዴግ የሽግግር ዘመኑን ካዳመቀለት በኋላ የአገልግሎት ዘመኑ እንዲያበቃ ያደረገው ኦነግ ነው::ይህ ድርጅት ከጫካ የመጣው የኢህአዴግ ሰራዊት ብዙ ልምድ ያለው በመሆኑ የሃገሪቱ የመከላከያ ሰራዊት እንዲሆን፣ የኦነግ ወታደሮች ደግሞ ትጥቃቸውን ፈተው ካምፕ እንዲገቡ አቶ መለስ ያመጡትን "ድንቅ" ወጥመድ ሳያቅማማ በመቀበሉ ነበር ቀድሞ ጥርሱን ያጣው:: የኋላ ኋላ በውሃ ቀጠነ የልቡን ካደረሰው ኢህአዴግ ጋር መነታረኩ መሪዎቹን ወደ ባህር ማዶ ጄሌዎቹን ወደ ጫካ ገፍቶ ከሰላማዊ ትግል ጋር አፋታው::ከዚህ በኋላ በግላጭ ጥራኝ ዱሩ ብሎ የትጥቅ ታጋይ መሆኑን ያወጀው ኦነግ ሽበሽ ገድሎ ለዙፋኑ የበቃውን ኢህዴግን በሚያሳስብ መልኩ ጫና መፍጠሩም ሳይሳካለት ጭራሽ ለሶስት ተፈርክሶ አቻውን አርበኞች ግንባርን ወደ መምሰሉ ተቃርቧል::

ከኦነግ እና አርበኞች ግንባር በተሸለ መልኩ የኢህአዴግን ቀልብ የመሳብ እና የማስፈራት ግርማ ያለው ኦብነግ ይመስላል::ይህ ቡድን ከሁለቱ በተለሻለ በጦር ሜዳ ስላከናወነው ወታደራዊ ጀብድ፣ ስለአጠቃው ጥቃት ወዘተ ብቅ እያለ የሚናገር፣መዘዙ ለንፁሃን ቢተርፍም በአካባቢው የኦብነግ መገኘት ኢህአዴግን ቢያንስ ተገዳዳሪ እንዳለው በሚያስታውስ ሁኔታ ወታደራዊ ጥንቃቄዎች እንዲያደርግ እንዳስገዳደው የሚያስታውቅ ድባብ አለ::ሆኖም ኦብነግም መንግስት በፍተሻ ሰላማዊ ሰዎችን እንዲያደክም ከማድረግ ባለፈ የሚወራለት ስጋት ያመጣ አይደለም::

ከላይ የተነሱት ቡድኖች በጉልህ የሚታወቁ ኢህአዴግም ስለመኖራቸው እውቀና ሰጥቶ በተለያየ ጊዜ የሚያወግዛቸው ናቸው እንጅ በሃገሪቱ የሚንቀሳቀሱ ብቸኛ ብረት አንጋቾች ናቸው ማለት ያስቸግራል::እነዚሁ ጎላ ያሉናቸው የሚባሉትም እንደሚሉት ኢህአዴግን ከወንበሩ ማንሳት ቀርቶ እንደ ባለጋራ ነገሬ ብሎ እንዲያስባቸው የሚበቃ ስጋት መፍጠሩም አልተሳካላቸውም::ለታጣቂዎቹ አቅም ማጣት እና የትጥቅ ትግሉ መንገድም ውጤት አልባ የሆነባቸው የተለያዩ ምክንያቶች ይኖራሉ::ኢህአዴግ ከደርግ በተለየ ከኩታ ገጠም ሃገራት ጋር ያለው መልካም ግንኙነት የትጥቅ ታጋቹ ወታደራቸውን የሚያሰለጥኑበት፣ ሲሸነፉም የሚያፈገፍጉበት፣ ቁስለኛ ወታደሮቻቸውን የሚያሳክሙበት ደጀን መሬት እንዲያጡ ማድረጉ አንዱ ምክንያት ነው::በዚህ ረገድ ሱዳን ለኢህአዴግ ደርግን ማሸነፍ ትልቅ አስተዋፅኦ ነበራት::ይህን የሚያውቀው ኢህአዴግ ታጣቂዎቹን አሸባሪ ብሎ ፈርጆና ከጎረቤት ሃገሮች ጋር የፀረ-ሽብር ህብረት ስምምነት ተፈራርሞ ደጀን ያሳጣቸዋል::በመሆኑም እድሜያቸውን የሚመጥን ማስፈራት እዳይኖራቸው ሆኗል::የትጥቅ ትግሉ እንዳይሳካ ካደረጉት ምክንያቶች ሁለተኛ ሊሆን የሚችለው የኢህአዴግ ዥጉርጉር ፖለቲካዊ ማንነት ታጣቂቹ ወታደሮች እንደልብ እንዳያገኙ ሳያደርግ አልቀረም::ኢህአዴግ አሁን አሁን አምባገነንነቱ እያደላ ቢመጣም በዲሞክራሲያዊ እና በአምባገነንነት መሃል ሚናውን ያልለየ ተፈጥሮ አለው::ይህም በሰላማዊ መንገድ ስልጣን ያስረክብ ይሆናል የሚለውን ተስፋ እንዳይጠፋ ስላደረገው ረዥም ጊዜ የትጥቅ ትግሉ አማራጭ እምብዛም እየታሰበ አልነበረም ::ይህ ደግሞ ኢህአዴግ ጫካ በነበረበት ጊዜ በደርግ የለየለት አምባገነንነት ተስፋ ቆርጠው የትጥቅ ትግሉን የማቀላቀሉ አእላፍ ወጣቶች አይነት የወታደር ብዛት የአሁኖቹ ታጣቂዎች እንዳያገኙ ከልክሎ እርምጃቸውን የኋሊት አስመስሎታል::ሶስተኛ ምክንያት የኢትዮጵያ ህዝብ ረዥም ዘመን በእርስበርስ ጦርነት በመሰላቸቱ የትጥቅ ትግሉን ከማሰብ ይልቅ ረዥም ጊዜ ቢወስድም ሰላማዊ ትግልን ተስፋ ወደ ማድረጉ እንዲያዘነብል መሆኑ ነው::ከዚህ በተጨማሪ ከእሱ በፊት በነበሩ መንግስታት ባልተሞከረ ሁኔታ ኢህአዴግ በተወሰነ መልኩ የሰላማዊ ትግል ሃሳብ በሃገሪቱ እንዲከተል አድርጓል ::ይህ ከነችግሩም ቢሆን ኢህአዴግ የጀመረው በጎ እርምጃ ነው::በመሆኑም ወደ ትጥቅ ትግል መመለስን ወደ ኋላ እንደ መሄድ የመቁጠሩ ዝንባሌ በሃገሪቱ ፖለቲካ የሚታይ ነው::ሆኖም ግን ኢህአደግ እያደር በከባድ እርምጃ ወደ አምባገነንነት የሚያደርገው ጉዞ ይህን እሳቤ አይፈታተነውም ማለት አይቻልም::ለሶስተኛው የለውጥ እሳቤ ማለትም በህዝባዊ ሰላማዊ አመፅ ዙሪያ ሃሳቦችን ለማንሳት ሳምንት መመለስን ወደድኩ:: ♦

ድርጅትዎንና አገልግሎትዎን
በዚህ ሳምንታዊ ጋዜጣ
ያስተዋውቁ
0934-680524

# ቀሽም !

ቃልኪዳን ኃይሉ
kalkidan hailu

ራዚ የሽልማት አይነት ነው::ይህ የሽልማት አይነት በአድናቆት፤ ጎሽ ደግ አደረክ፤ ለምስጉኑ ስራህ፤ ላስደመምክ ላስደነገጥከን፤ ለምድራችን ለየት ያለ ነገር ስላመጣህ፤ ህይወትን ስለቀየርክ፣ ያልጠበቅነውን ስላመጣህ፤ አይሆንም ያልነውን ስላደረከው፤ ስለጀግናው ስራህ፤ ስለድንቅ ፈጠራህ፤ ስለሰጠህን የተለየ ነገር፤ ለማለፊያው ግብርህ፤ ፓፓፓፓፓፓፓ... ብለን አይደለም የምንሸልመው::

እንደውም ከዚህ በተቃራኒ ለማፈሪያው ስራህ፤ ብዙ ጠብቀን ትንሽ ስለሰጠህን፤ ስለቀሽሙ ውጤትህ፤ ስላልጠበቅነው ውድቀትህ፤ ስለደካማው ብቃትህ፤ ስላሳፈርከን፤ ባትሰራው ኖሮ፤ ባትሞክረው ኖሮ፤ አይጠበቅም ካንተ... ተብሎ የሚሸለም ነው::

ይሄ ምኑን ሽልማት ሆነው ትችት ነው ትሉ ይሆናል::ግን አይደለም ሽልምት ነው::ለዚህ ሽልማት ሰዎች ይታጫሉ፤ በተከበረ አዳራሽ እንዲመጡ ይደረግና ሽልማቱ ይካሄዳል አሜሪካ ውስጥ::ይህ ሽልማት ከታላቁ ኦስካር ሽልማት ከመሠጠቱ በፊት እንዲሁም አካዳሚ አዋርድ ከመካሄዱ አንደ ቀን በፊት የሚሰጥ ነው::በአመቱ ቀሽም የተባለውን ፊልም የተወኑ፤ ዳይሬክት ያደረጉ፤ ረዳት ተዋንያን፤ ማጀቢያ ሙዚቃ የሰሩ፤ የቀረፁ...ወዘተ ብቻ የአመቱ ቀሽሞች በጋዜጠኞች፣ በታዋቂ እና አዋቂ የፊልም ባለሙያዎች ተመርጠው የሚሸለሙበት መድረክ ነው::

እ.ኤ.አ በ1981 በጆን.ቢ.ዊልሰን በተባለ ግለሰብ ሎሳንጀለስ በሚገኘው መኖሪያ ቤቱ አስራ ሁለት ታዳሚያንን በማስተፍ ነበር የጀመረው::በአሁኑ ሰአት ሲ.ኤን.ኤንን ጨምሮ ሌሎች ታላላቅ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ያስተላልፉታል::ይህን ሽልማት ብዙ የምናደንቅ እና የምናከብራቸው አርቲስቶች ተቀብለዋል::ሲልቨር ስታሎን፣ ሃሊ ቤሪ፣ማዶና፣ አሎንድ ሽዋዚንገር፣ ኤዲ መርፊ፣ ፓሪስ ሒልተን፣ ኦፕራ፣ ቶም ክሩዝ፣ ኬቲ ሆልምስ... ከብዙ በጥቂቱ የአመቱ አስቀያሚ ተብለው ሽልማት የወሰዱ ናቸው::

አስደናቂው ነገር ለቀሽሞች ሽልማት መዘጋጀቱ አይደለም፤ ቀሽም ተብለው በመድረክ ላይ መወደስ ልበለው ትችት መስጠት መቻላቸው አይደለም::እሱ አይደለም የሚያስደንቀው::የሚያስደንቀው አንቱ የተባሉ የፊልም ዳይሬክተሮች አምና ታላቁን ኦስካር የበሉ፤ ህዝቡ የሚያብድላቸው፤ የሚያደንቅ የሚያጨበጭብላቸው... አክተር፣ ዳይሬክተር፣ ረዳት ተዋናይ...ሽልማቱ ላይ መገኘታቸው ነው::ተገኝተውም አመስግነው መቀበላቸው ነው::

ይህ ነው መብሰል ማለት::ሽልማት መቀበል እኮ ብርቅ አይደለም፤ ውዳሴን በህዝብ ፊት ማግኘት ትልቅ ነገር ቢሆንም ሰነፍ ነህ ተብሎ ባጨበጨቡልን ህዝብ መሀል መቆም፤ ምንም አትችልም ተብሎ ሽልማት መቀበል፤ ያሳፍራል ተብሎ ህዝብ ካለ እውነት ነው ብሎ በሽልማት ስነስርአቱ ላይ መገኘት ድንቅ ምግባር ነው::የብስለት ትክክለኛ መገለጫው ነው::

የእኛዎቹ አቀንቃኞች፣ ተዋንያኖች፣ አርቲስቶች... በአጠቃላይ የኪነ ጥበብ ሰዎቻችን ሎቲ ማንጠልጠሉን፤ ቅጥ ያጣ ያኗኗር ስርአቱን፤ ባህልና ምግባር የተጣረሰ አለባበሱን፤ ከልክ ያለፈ መዝናናቱን፤ ረብ የለሽ ኑሮውን፤ ያልተረጋጋ የትዳር ህይወቱን፤ሴሰኝነቱን... ከመውረስ ይልቅ እንዲህ ያለውን በጎ ባህል ቢቀዱ ቢመለከቱ ለዚህች ሀገር የኪነጥበብ እድገት አሌ የማይባል አስተዋጽኦ ይኖረዋል እላለሁ::

የእኛዎቹን ታዋቂ ሰዎች (celebrities) እንኳን ቀሽም ናችሁ ብለናቸው አይደለም ጥሩ ሰርታችኋል፤ ከጎበዞች መሀከል አንዱ ሆናችሁ ተመርጣችኋል ብለን ጋብዘናቸው "እኔ ካለሸነፍኩ አልመጣም፤ ዳኞቹ የሀገሬ ልጆች አይደሉም፤ ከዳኞቹ አንዱ ይቀናብኛል፤ እኔን ሆን ብላችሁ እንድሸነፍ ታደርጉኛላችሁ፤ አይመጥነኝም አትመጥኑኝም..." በሚሉ ሰበቦች አክብረን የጠራናቸው አርቲስቶቻችን ራሳቸውን ንቀው ይቀራሉ::

ጎበዝ የምንላቸው እንዳሉ ሁሉ ብዙ ብዙ ቀሽሞች በትያትሩ፣ በማስታወቂያው፣ በፊልሙ፣ በስነጽሑፉ፣ በስእሉ፣ በዲዛይኑ፣ በትወናው... እንደሞሉ ግልጽ ነው::ለዚህም የራዚ ሽልማትን እኛ ሀገር እናድርገው ብንል ሀገር ምድሩ ይቃጠል ነበር::እነዚህን በገሀድ የተሳሳቱትን ሰዎች በአደባባይ ምንም አትችሉም፤ ሌላ ስራ ሞክሩ፤ ይቀራችኋል፣ አስተካክሉ... ቢባል ብዙዎች በቁጣ ድብልቅልቅ ነው የሚሉት::

በማስታወቂያ ጩኸት የሚታየውን ፊልም፤ በመጢደን የሚነበበውን መጻህፍ፣ ጋዜጣ፣ መጽሔት፤ ሳያውቁ መታወቅ የሚፈልጉት የሬደዮ ፕሮግራም አዘጋጆችን፤ ሳያዝናኑን መዝናኛ ፕሮግራም የሚሉን፤ ለማስታወቂያ ገንዘብ ብቻ የሬዲዮ እና የቴሌቭዥን ሰአት የገዙትን፤ መገናኛ ብዙሀኑን መገናኛ "ዘመድ ወዳጅ" ያደረጉትን፤ መታወቅ የሚገባውን ትተው ራሳቸውን ያስተዋወቁትን ቀሽም! ብንላቸው ምን የሚሉ ይመስሏቹሀል?

"የኢትዮጵያ ህዝብ ይህን ጉዳይ ዝም ሊል አይገባም፤ ስም የማጥፋት ዘመቻ ነው፤ ጉዳዩን ወደ ህግ ወስጄዋለሁ፤ የአእምሮ ጥበቃ ማህበር አንድ ሊል ይገባል፤ ህዝቡ ይፍረደኝ፤ እንዴት ቢደፍሩኝ ነው?"... የሚሉ ትችት እና ቁጣዎች ይሰነዘራሉ::

በአደባባይ መደነቅ እንጂ መታረም አንፈልግም፤ በብዙሀን ፊት መመስገን እንጂ ይህን አስተካክሉ መባል ሞታችን ነው፤ በበነነ በተነነው ጭብጨባ ስለለመድን ይህ ይህ ጎድሏል የሚል አስተያየት እና ተግሳፅ የሞት ያህል ይከብደናል፤ የተገኘውን ሽልማት እና ምስጋና መቀበል እንጂ ለተሳሳትን ላሳሳትነው ጉዳይ ሀላፊነት መውሰድም ሆነ ይቅርታ መጠየቅ ለእኛ ሽንፈት ነው፤ በሰው ፊት ከብደን መታየት እንጂ ተመሳስለን መኖር አይሆንልንም፤ የወጣንበትን ማህበረሰብ ቢያንስ በኑሮ አንድ ደረጃ እንደምንበልጠው ለማሳየት እንጥራለን እንጂ ከቀድሞው አንድ ደረጃ ጥራት ያለው ስራ ስንሰራ አንታይም::

እርግጥ ነው በሀገራችን በተቋም ደረጃ የቀሽሞች የደካሞች ሽልማት ባይኖርም::እርስ በእርሳችን እንደምንተቻች፤ ከማበረታታት ይልቅ መኮርኮም እንደሚቀናን፤ የሰላውን በማያንፅ ምክርና ተግሳፅ የምናዶለዱም፤ ሊያፈራ ያለውን ያበበውን በቅናትና ጥላቻ የምናከስም፤ ሌላውን ጀግና ማለት እራሳችንን ፈሪ እንደማለት ሆኖ የሚሰማን፤ ወዳጃችንን ማስተለቅ ለራሳችን ውድቀት የሚመስለን፤ ከእኔ በላይ ላሳር ያልን፤ እራሳችንን የማእዘን ድንጋይ ያደረግን፤ መታወቅ እንጂ ሌላውን ማሳወቅ የማንፈልግ... ብዙ ነን::

አንዴ ጋዜጠኛ ጌጡ ተመስገን የሚመራው የፊልም ምርቃት ላይ ተገኝቼ ነበር::የደራሲ ተክሉ ጥላሁን "አስርቱ ቀናት" የሚለው ፊልም ነው::በእለቱም ጋዜጠኛ ጌጡ ከተናገራቸው ንግግሮች ውስጥ "ማድነቅ መሰልጠን ነው..." የሚለው አባባሉ እጅጉን ተመችቶኝ ነበር::

"ማድነቅ መሠልጠን ነው!" እውነት ነው ሁላችንንም ያስማማል::ስናደንቅ ብዙ ብርቅዬዎችን እናፈራለን፤ ለሌሎች ቦታ ስንሰጥ ያልታየ ብዙ በጎ ነገር ያሳዩናል፤ ሌሎችን ስናከብር ይበልጥ ራሳችንን እናስከብረዋለን፤ ዋኖዎቻችን ብዙ ይሆናል፤ ነጸብራቆቻችን ይበልጥ በዓለም ላይ ያንፀባርቃሉ::የትኛው የኢትዮጵያ አይድል እንሆነ ባላስታውሰውም "የሚሞክሩትን ስናበረታታ የሚችሉት ይፈጠራሉ" የሚል አባባል ነበራቸው::

ማድነቅ መሰልጠን መሆኑን ካመንን ሌሎችን ስናበረታታ ብዙዎች እንደሚፈጠሩ ከገባን ለአስተያየት እና ለትችትም ልባችንን ልንከፍት፤ አእምሮአችንን ልናዘጋጅ ግድ ነው::መደነቅ እስካለ መተቸት አለ፤ መጨብጨብ እስካለ ሊጮህብንም ይችላል፤ ማሸነፍ እስካለ መበለጥ እና መሸነፍ ግድ ነው::ወቀሳ ለማጥፋት አይደለም፤ ቀሽም ነው ማለት ምንም አትችልም ማለት አይደለም::ብዙ የምናደንቃቸው የባህርማዶ አቀንቃኞች ቀሽም ስራ ነው የሰራኸው፤ አስቀያሚ ነው ተብለዋል::ያ ማለት ዘልአለም አትሰራም ማለት አይደለም::ይልቁንስ ለነገ የጠራ እና የበሰለ ለማውጣት እንጂ::

# ሀገሮሙ ለሀዋርያት ወለነቢያት

ዛሬ ስለ አንድ ስለገረመኝ ነገር ላወጋችሁ ፈለግኩ::ክርስትና በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን እስልምና ደግሞ በሰባተኛው ክፍለ ዘመን ወደ ኢትዮጵያ እንደገቡ የታሪክ ድርሳናት ቢተርኩም እንደ ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ግን ሀገራችን በነቢያትና በሀዋርያት ተሞልታ አታውቅም::የምን ነቢይና ሀዋርያ አንደምትሉ ማወቅ ባልችል መገመት አይሳነኝም::ነቢይ በሀገሩ አይከበርም እንጅ ሁሉም ቅዱስ ሁሉም ነቢይ ሆኗል::በግብር አምላክ ይመርምር እኔ ያልኩት በስም ነው::ድሮም እኮ ሙሴን ነቢይ ያለው አምላክ እንጅ ፈርዖናውያንማ አልተቀበሉትም ነበር:: ሞሀመድስ ቢሆን ቋሪሾች አይንህን ለአፈር ብለውት አልነበር? እኛ ግን ይህን አንልም::ምክንያቱም ዲሞክራሲ ባለበት ሀገር ይህን ማድረግ ከሀያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ሰብዓዊ ፍጡር አይጠበቅምና!!

ይህን ጉዳይ ያለ ነገር አላነሳሁትም::ባለፈው ሰሞን አንድ የቀድሞ ወዳጄን ሀዋሪያ ሆኖ ባገኘው ደንቆኝ ይህችን መጣጥፍ ሞነጫጨርኩ::ይህ ጓዴ ድሮ ‹‹መኩሪያ›› ይባል ነበር ያሁኑን አያድርገውና::‹‹መኩሪያን›› አዲስ አበባ እግር ጥሎኝ ሂጄ ‹‹ቶማስ›› ሆኖ ሳገኘው መደነቁን በውስጤ አፍኜ አዲሱን ስሙን ‹‹ቶም›› በማለት አቆላምጬ ጠራሁት- በረከቱ ቢደርሰኝ ብዬ::

እናም ጉዳዩ ለኔ ለራሴ ቢያሳስበኝ በብዕር ተነፈስኩት::እኔ ደግሞ በውስጤ ያለውን ካልተነፈስኩ ያመኛል::አንድ የኔ ቢጤ ጸባይ ያለው ሰው ከድሮ ነገስታት ጋር ቀረቤታ ነበረው አሉ::እናም በወቅቱ የነበሩት ንጉስ ዘውድ ሳይደፉ የማግኘት እድል ገጠመውና የንጉሱን መላጣ አየ::ንጉሱም መላጣቸውን ከእርሱ ውጭ የሚያውቅ ሰው ባለመኖሩ ‹‹ይህች ጉድ ብትሰማ በስቅላት ትሞታለህ›› ብለው ያስጠነቅቁታል::ሰውየው ደግሞ ካልተናገረ እንደኔ ያመዋልና መናገር ፈለገ::ግን ደግሞ መኖር ይፈልጋል::ሳይሞት መተንፈስ የሚችልበትን ዘዴ ሲያስብ አንድ ነገር ብልጭ አለለት::ስለሆነም የቀበሮ ጉድጓድ ፈልጎ አንገቱን ወደ ጉድጓዱ በማስገባት ‹‹ንጉሱ መላጣ ናቸው›› ብሎ ደጋግሞ ጮኸ::እናም ጤንነቱንም አገኘ ህይወቱንም አተረፈ::እኔም ልጁን ቀጥታ መናገር ፈራሁና በወረቀት ጻፍኩት::እኔ ግን እንደ ሰውየው ከንጉሱ ጋር አልተሳፈጥኩም::ንጉስንማ መናገር አግባብ አይደለም!!

ለማንኛውም ኢትዮጵያ በስም ሀዋርያትና ነቢያት ሞልተዋታል እያልኳችሁ ነው::‹‹ሰዋ›› ብቻ ሳይሆን ሀገሪቱም የተጠመቀች ወይም የሰለመች እስኪመስል::

ስም ይወጣ ከቤት ይቀበል ጎረቤት እንዲሉ አባቶቻችን ልጆቻቸውን በልዩ ልዩ አጋጣሚ ይሰይሙ ነበር::ለምሳሌ የልጅ ጉጉታቸውን እውን ያደረጉ ጥንዶች ልጃቸውን ስመኝ ሊሉ ይችላሉ::አጋጤና መመኪያዬ ነህ ሲሉ ድጋፌ ነህ፣ ደጀኔ፣ አትንኩት፣ አሸናፊ፣ ... የጊዜውን ክፋት ለማመልከት ያየውሰው፣ አይቸው፣ ደስታን ለመግለጽ ደስታ፣ ፍስሀ፣ አዱኛ፣ ሀጎስ፣ ገመቹ፣... በወቅቶች ደግሞ መስከረም፣ ለምለም፣ አበባው፣ ... ከንግስና ጋር ለማያያዝ መንግስቱ፣ ንጉሴ፣ ንግስት፣ ዘውዱ፣ ዘውዴ ... በስልሳ ስድስቱ አቢዮት የተወለዱ ልጆች አብዛኛዎቹ አቢዮት ይባሉ ነበር::ብቻ በልዩ ልዩ ምክንያት ደንበሬ፣ ዳርቻ፣ ስንዱ፣ መግቢያዬ፣ አንበርብር፣ አለሙ፣ ከበደ፣ አበጀ፣... የሚባሉ ስያሜዎችን መስጠት የእኛው ትውፊት ስለመሆኑ አሌ የማይባል ሀቅ ነው::በርግጥ የስነ ባህል (Folklore) ባለሙያዎቹ ከዚህ በላይ ሊሉ እንደሚችሉ እገምታለው::

ታዲያ የሚገርመው ወላጆች ልጆቻቸውን መሰየማቸው ብቻ ሳይሆን የራሳቸውንም ስም እንደ ቶም መቀየራቸው ነው::ሀገርኛ ስሞች ያለ መሰልጠን ምልክት ሆነዋል::ጎበዝ! ማን ያውቃል ኢትዮጵያችን እኮ ወደ ኋላ የቀረችው በስማችን ሊሆን ይችላል!! መጠርጠር ጥሩ ነው::የስያሜ ለውጣችን በየአመቱ ከሶስት ድጅት በላይ ለውጥ እያስመዘገብን ነው!!

እኔ ግን እላለሁ፡- ከሰማንያ በላይ ቋንቋ እና ብሄር አለን ብለን የምንመካ እኛን የሚገልጽ ወይም ለእኛ ስም የሚሆን ቃል ከሌለው በቋንቋችን እንፈር አንጅ አንመካ!! እንዴት በማንነታችን ተጨቁነናል፣ ቋንቋችን ማሳደግ አልቻልንም፣ ... እያልን በየቀኑ የምንደሰኩር ሰዎች ለምን ራሳችን ከግብራችንና ከስማችን ጋር ማዋሀድ ያቅተን? ቅድስና የሚሰጠው በአረብኛ ወይንም እብራይስጥና ጽርህ ቃላት ስያሜዎች ከሆነ በነቂስ ፍረድ ቤት ወጥተን እናስቀይርና እንመሳሰል::አሊያ ደግሞ የቃላቱ ትርጉም በአማርኛ አበበ፣ ከበደ፣ አልማዝ፣ በለጡ ... ወዘተ ከሆነ ብናውቀው መልካም ነው::

በየቀኑ አዳዲስ ስሞችን መስማት የተለመደ ነው::ስሞችም አመራማሪ ተመራምረውም ትርጉማቸው የማይደረስባቸው ቀላል አይደሉም::መጽሀፍ ቅዱስ እና ቁራን ከእምነት መጽሀፍነታቸው ይልቅ ለስም ማውጫ መዝገበ ቃላት የሚጠቀምባቸው ሰው የትየሌሌ ነው::የጥንቶቹ ነቢያት ዛሬ ስማቸው በሀበሻ ምድር ገኗል::መላዕክትም አልቀሩ::አንድ ህጻን እንደተወለደ ቤተሰብ ስም ለማውጣት ይመክራል::‹ማን ብዬ ልሰይመው/ ልሰይማት?› የሚለው ሀሳብ በጣም የሚያስጨንቃቸው ሰዎች በርካቶች ናቸው::ከዚያ በፊት መጽሀፍ ቅዱስ አሊያም ቅዱስ ቁራን ማንበብ ያልለመደ ሰው ‹‹ስም›› ፍለጋ መጽሀፍቱን ማገላበጥ ይጀምራል::የተለዩ ስም ማውጣት እንደጀብደኝነትም ይቆጠራል::

እስኪ አንድ ቀልድ ቢጤ ቁም ነገር ብጨምር አይከፋም::ሳነብ ያገኘውት ነው::አንድ አውሮፓዊ ሚሲዮን ቄስ አፍሪቃ መጥቶ የሰበከውን ሰው ካቶሊክ ካደረገ በኋላ የቀደመውን ስሙን ‹‹አቡኮን›› ሰርዞ ‹‹ጆን›› ብሎ ይሰይመዋል::ጆንም የካቶሊክ እምነቱን ለብዙ ጊዜ አጥብቆ ያዘ::የነጆን ሰፈር ድረቅ ይመታና የሚበላና የሚጠጣ ነገር ይጠፋል::እናም ጆን የቀድሞ ህይወቱ ይሻላል ብሎ ወደ አደኑ ያመራል::ከዚያም በጾሙ ጊዜ አሸኮኮ እየጠበሰ ሲበላ ያ አውሮጳዊ ሚሲዮን ቄስ ሊጠይቀው ይመጣል::ቄሴም ጆንን በጾም ስጋ መብላቱ አናዶት ‹‹እንዴት በጾም ስጋ ትበላለህ? ይህ ጥሩ ካቶሊክ አማኝ እንዳልሆንክ ያሳያል›› ይለዋል::ጆንም ‹‹እኔ ስጋ አልበላሁም ይህ አሳ ነው›› በማለት ፍጥጥ ብሎ ይከራከራል::ቄሴም የበለጠ ተናደው በድርጊትህ እንደመጸጸት እንዴት የበለጠ ትዋሸኛለህ ይሉታል::‹‹እርስዎ እኔን ትንሽ ውሃ ረጭተው አቡኮ የነበርኩትን ጆን አደረጉኝ፤ እኔም ትንሽ ውሃ ረጨውና አሳ ሁን አልኩት፣ አሳም ሆነ›› በማለት መለሰላቸው (ከዚህ ላይ አንባቢያን ጉዳዩን ከሀይማት አንጻር ሳይሆን ከማንነት ጋር ብቻ እንድትመለከቱት እማጸናለሁ::ሀይማኖት የግል አገር የጋራ እንደሆነች ማንም ይቀበላልና)::

ታዲያ ስንት አቡኮዎች አለን? ይህን ሰው ከአቡኮና ከጆን ማን ሊገልጸው ይችል ነበር? አቡኮ አይደለምን? ራስን ትቶ ወዴት ለመድረስ ነው? በግብር ወይስ በስም መለወጥ? ከመጽሀፍ ቅዱስ ውጭም ከየት እንደመጡ የማይታወቁ ቃላት ቀላል አይደሉም::ጠላት የዘራቸው እንክርዳድ ይሆኑ እንዴ? አማርኛውም ቢሆን እንዳለ የለም::አለሙ የሚባልን ልጅ አባቱ ቢያቆላምጡት / ሲያንቆለጳጵሱት ‹‹አለምዬ›› ሊሉት ይችሉ ይሆናል::እኔ ግን ‹‹አሌክስ›› በማለት ወደ ታላቁ ‹‹አሌክሳንደር›› ማስጠጋት ይጠበቅብኛል::‹‹ማርጋሬት›› የምትባል ልጅ ሰሞኑን ተዋውቂያለው::

አማርኛ፣ ኦሮምኛ፣ ትግርኛ አሊያም የእኛ ሀገር ትርጉም ያለው ስም መስጠት ለምን አልቻልንም!! አማርኛ ትርጉም ያለው ስያሜ ያለው የእስልምና እምነት ተከታይ ‹‹ክርስቲያን›› ነው ብለን የምናስብም አለን::ወሎ የተወለደ ሙስሊም አማርኛ፣ አሊያም ሀረርጌ የተወለደ ሙስሊም ኦሮምኛ ስያሜ ከሚኖረውና አረብኛ ትርጉም ካለው ስም የትኛው እርሱን እንደሚገልጽ ማወቅ በትምህርት መላቅም/መምጠቅ መመራመርም አያስፈልግም::

የሚገርመው መጽሀፍ ራሱ ይህን እንድናደርግ አይመክርም::ዳንኤል እና ሶስቱ ብላቴናዎች ናቡከነደነጾር በሚባል ንጉስ ተማርከው በሚገባ እንዲያዙ ተደርገው ነበር::ንጉሱም የሚመቸውን ስም ሰጥቶ የከለዳውያንን ትምህርት በዘመኑ ከነበሩ ዩንቨርሲቲዎች እንዲማሩ አድርጎ ነበር::ግን እነ ዳንኤል ራሳቸውን ሆኑ እንጅ በከለዳውያን ባህል አልተሸረሸሩም::ዮሴፍም በግብጽ ሀገር ያደረገው ይህኑ ነበር::ኢትዮጵያዊቷ ንግስት አዜብ/ ማክዳ/ ቤላክኔ/ ሳባ ሰሎሞንን ከመሰለ ጥበበኛ የወለደችውን ልጅ <<ምኒልክ>> አለችው እንጅ ዘር ስለአለበት በማለት እብራይስጥኛ ስም አልሰየመችውም::

ለማንኛውም ከቤት የወጣ ስም ጎረቤት አልተቀበለውም፤ አደነጋገረ::ከቤት አንድ ልጅ ለትምህርት ይሁን ለስራ ሌላ ቦታ ቢሄድ እና ገንዘብ ለመላክ ቢፈልግ አድራሻውን እና ሙሉ ስሙን ደግመን የምንጠይቅ ሰዎች ቀላል አይደለንም::አስቀይሮት ሊሆን ይችላልና ነው::<<አትንኩት>> የሚባል ልጅ ዩንቨርሲቲ ላይ <<ኢዩኤል>> ተብሎ መጥቶ ከአባቱ ጋር እንደተጣላ ነግሮኛል::ትርጉሙስ ሳናውቅ ስም የምንሰጥ ስንት ሰዎች አለን::<<ኢሳይያስ>> ማለት አዳኝ ማለት ነው::እናስ ኢሳይያስ ከመባልና መድሀኒት ከመባል የትኛው ይሻላል? ያዕቆብ ማለት አሰናካይ ማለት ነው፤ ታዲያ ኢትዮጵያ ውስጥ ስንት አሰናካይ ተብለው የሚያሰናክሉ ሰዎች አሉ?

እኔ ነገሬን ልጨርስ ነው::ቢጨንቀኝ ነው ኢትዮጵያ የሀዋርያትና የነቢያት ሀገር ሆናለች ያልኩ::በግብር ማንነታችን ብንይዝ አሪፍነት ይመስለኛል::አሊያ ግን የስነ ስም የትምህርት ክፍል ቢቋቋም መልካም ነው::የኔ መጠነ እውቀት ከዚህ በላይ አላስኬደኝም::

ሰላም

# ኢትዮጵያዊነት ...

ከገጽ 7 የዞረ

በውስጥ ጉዳይ ከማንኛውም አካል የበለጠ የሚመለከተው የደህንነት ተቋም ሃላፊዎች በአንድ ብሄር አባላት ቁጥጥር ስር መውደቅ ሌላው መፍትሄ ሊበጅለት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ትልቁ የቤት ስራም ለፖለቲካ ፓርቲም ይሁን ለአንድ(ለተወሰኑ) ሌሎች ቡድኖች የማያደላ ተቋማት ምስረታ ላይ መሆን አለበት፡፡የትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ስልጣን ቢይዝ ሲአይኤ ሁሌም አለ፡፡ ሞሳድ ሁሌም አለ፡፡ይህ የእኛም ናፍቆት ነው፡፡ኢህአዴግ በስልጣን ቆየም አልቆየም የደህንነት ተቋማቱም ይሁኑ መከላከያ ሰራዊቱ ሁሌም መኖር አለበት፡፡የናፈቀን ቀጣይነት ያላቸው ተቋማትና ስርዓታት ናቸውና!

መከላከያ ሰራዊቱ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ብሄሮች፣ብሄረሰቦችና ህዝቦች ሙሉ ነጸብራቅ መሆን አለበት ብለናል፡፡የአንዱ ወይንም የጥቂቱ ብቻ መሆን የለበትም፡፡በእርግጥ እዚህ ላይ ውትድርና ሀገራዊ የዜጎች ግዴታ ባልሆነበትና በፈቃደኝነት ብቻ ምልመላ በሚከናወንባቸው በተለይም እንደኢትዮጵያ ባሉ ባለብዙ ብሄር ሀገራት ምጥጥኑን ማምጣት ከባድ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ሙሉ በሙሉ ጠንካራ ወታደራዊ ዲስፕሊንን መፍጠርም አታካች ነው፡፡የአታካችነቱ ምክንያቶችም የብሄር፣ብሄረሰቦችና ህዝቦች በተመጣጣኝ ሁኔታ የትምህርት ሽፋን ባለመኖሩ ዝቅተኛውን የትምህርት መስፈርት በተመሳሳይ መልኩ የሚያሟሉ እጩ ማጣት፣ውትድርና የድሆችና የስራአጦች ምርጫ መሆኑ፣ከ1987 ዓ.ም. በፊት የመከላከያ ሰራዊቱ ወደ አንድ ብሄር(ትግራዋይ) ብቻ ያደላ መሆኑ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

አሁን በተራ ወታደር ደረጃ ያለው የመከላከያ ሰራዊት የብሄር ስብጥር ሲታይ አማራን ደቡብን ኦሮሞን በደንብ ያሳተፈ መሆኑ ይነገራል፡፡ በባለ ከፍተኛ ማዕረግ መኮንንች ቁጥር በኩል ደግሞ የትግራዊያኑ ቁጥር ከበርካታም በላይ ነው፡፡የማመጣጠኛ ወይንም ሚዛናዊ ውክልና መፍጠሪያ የማይለዋወጥ ሂሳባዊ ቀመር ሊኖር እንደማይችል ሃቅ ነው፡፡ይሁን እንጂ ህገ-መንግስቱ ከጸደቀ ጀምሮ ሀያ ዓመታት ሊሞላው ነውና እነዚህ ጊዜያት ደግሞ የአንድ ትውልድ እድሜ ናቸውና ብሄር፣ብሄረሰቦችና ህዝቦች እንደቡድን ካላቸው መብቶች አንዱ እና የደህንነት ዋስትና እንዳላቸው እንዲሰማቸውና የሚያረጋግጡበት በመከላከያ ሰራዊቱ ውስጥ ተወክለው ማየታቸው ነውና ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡በተለይም በቁጥራቸው አናሳ የሆኑ ኦሞቲክና ናይሎ ሳሃራዊ የሆኑት በኮሌነልነትና ጀነራልነት የተወከለ ፊት አለማየት የድሮውን በመውቀስ ነገር ግን ያንኑ በመድገም ባለንበት ከመሄድና ከአፋዊ ትርክት(rhetoric) ወደ ተግባር መሸጋገር ግድ ይላል፡፡

ከኢትዮጵያ ሰማይ ስር



# አገር ስጡኝ - አገር አልባ ባለሀገር (ባላገር)

ክፍል አንድ

(በእውተኛ ታሪክ ላይ ተመስርቶ የተለያዩ ሰዎችን ቃለ መጠይቅ በማድረግ የተዘጋጀ)

በሙሉቀን ተስፋዉ (የክፉ ሰዉ ሽንት መጽሀፍ ደራሲ)
Email: mulukentesfaw@gmail.com

ይህ የአንድምስኪን ኢትዮጵያዊእውነተኛ ታሪክ ነው።አያቱንበ ጣሊያን ወረራ፣አባቱን በሶማሊያ ወረራ፣ወንድሙንበኢትዮጵያውያንየርስበ እርስጦርነት፣ቤተሰቦቹንበደርግናበህወሓትጦርነት፣ሚስቱንናልጆቹንበ ጎሳ ተኮር መፈናቀልአጥቷል።በርካታ ታሪካዊ፣ ባህላዊ እና ስነ ሰባዊ (አንትሮፖሎጅካል) ጠቀሜታ ያለውን ጽሁፍ ባልደረባችን ሙሉቀን ተስፋዉ አዘጋጅቶታል።በተከታታይበዚህክፍልይተረካል። . . .

በዚህ ጊዜ ተወለድኩ ማለት አልችልም።እድሜዬ የአቅራብ ስሌት ውጤት ነው።ድሮ ላይ ልደት የሚከበረው ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነበር የሚመስለኝ።እርግጥ ነው የኔ ሀሳብ አሁንም ያው ነው።ልደት የምንለው በየዓመቱ ታህሳስ 29 ቀንን ነው።ያኔ እኛ ከጎድሩ እንቁር (ገና) እንለጋለን፤ ወላጆቻችን ግን ለሳምንት ያክል ላሊበላ ተጉዘው ያከብሩታል።በቃ ልደት ያ ነው ለኔ።ልደቴን ከማከብር እመብርሀንና አቡዬ ጻዲቁን ብዘክር እመርጣለሁ (የልደት ቀን ስጦታ የለመዳችሁ ሰዎች የተወለድክበትን ቀን ሳታውቅ እንዴት ማክበር ያምርሀል ብላችሁ እንደምትቦጭቁኝ አውቃለሁ)።ስለሆነም የተወለድኩት ምናልባትም በ1960ዎቹ መጀመሪያ ሳይሆን አይቀርም።ይህን ያልኩት‹‹የአቢዮቱ ነነ፣ ማንም አይነካነ›› የሚለው ዘፈን ሲመጣ ጥጆችን አግድ (እጠብቅ) ነበር አሉ።አሁን ላይ ሆኜ ሳስብ ይህ ዘፈን የተጀመረው የጃንሆይ ዙፋን በፍየል ወጠጤ የተደፈረበት መስከረም ሁለት 1967 መሰለኝ።በትንሹ እንኳ ከ1960 ላይ ሶስት አመት ሲደመር አሊያም ሲቀንስ አደርገን ብናሰላው የተወለድኩት ከ1957 እስከ 1963 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ ነው።

እንግዲህ ከእኛ አገር እድሜ የሚሰላው በዚህ መልኩ ነው።ልጅነቴ በብዙ ጥሩና መጥፎ ነገሮች የተሞላ ነበር።ግን መጥፎው ይበዛል።ዘመዶቼ አንዳንዴ በዘመኑ የተሰሩ ነገሮችን እያስተዎሱ በዚህ ቀን እንዲህ ነበር።እንትና ሲወለድ እኮ አንተ የአንድ ዓመት ልጅ ነበርክ ምናምን እያሉ ያሰሉት ነበር።

በ1960ዎቹ መጨረሻ የዚያድ ባሬ ሶማሊያ አገራችን ስትወር አባቴና አጎቴ ሀረርጌ ድረስ ሂደው ተዋግተዋል።አጎቴ ጥርሱን በድንጋይ ሆን ብሎ አውልቆት ይሆን አሊያም በጥይት አላውቅም ‹‹ጥርስህ ጎደሎ ነው›› ተብሎ ከጦር ተመለሰልን።ከጦርነት የተመለሰ ቀን እኔ ከከብቶቻችን ጋር ዱር ነው የዋልኩት።የጥይት ተኩስ እሩምታ ሰምቼ ደነገጥኩ።ጦርነቱ ከእኛ የደረሰ መስሎኝ የምገባበት ጠፋኝ።የእኔ ደግሞ ችግር በፈራው እና በደነገጥኩ ጊዜ ሽንት ሽንት ነው የሚለኝ።አስር ጊዜ መቀመጥና መሽናት ነው - ከድንጋጤ ጋር ምን እንዳገናኛቸው እስካሁን ባይገባኝም።

ከብቶቼን እነ ስንቡልንና ኳሊን ትቼ ወደ ቤቴ እግሬ አውጭኝ ብየ ሽመጠጥኩ።አጎቴ እየፎከረ ይንጎማለላል።

‹‹ከዚህ አንስቶ እስከ ፎገራ
ጥይት ዘርዛሪ እንደ ሽንበራ!!
አይ ዘራፍ ዘራፍ! የአባብዬ ልጅ....››

(አሁን ላይ ሳስበው አጎቴ የዘመተው ምስራቅ ኢትዮጵያ እሱ የሚለው እስከ ፎገራ፣ ፎገራ ደግሞ የግማሽ ቀን እንኳ የማይርቅ ሲሆን ለምን እንደዚያ ፎከረ ምናልባትም ግጥም ስለመታለት ይሆናል) ይልና ይህን ክላሽንኮቭ ጥይት ይቆለዋል።በእድሜ ጠና ጠና ያሉ የሰፈራችን ሰዎችም እሱን አጅበው አብረው ይተኩሳሉ (ምናልባትም ወጣቶቹ አንድም ወደ ጦርነት ሂደዋል አሊያም ተሸሽገዋል)።ለካ ደስታ ነው እንዲህ የሚያደርጋቸው።አባቴ ናፍቆኝ ይመጣል አብሮ መጥቷል ብዬ ባስብም እድለኛ አልነበርኩም።አጎቴን ጉልበቱ ደፋ ብየ ልስመው ሳስብ ጥይቱን ፈርቼ ከቤታችን እልፍ ብሎ ካለ ትልቅ ቋጥኝ ስር ተደበቅኩ።ተኩሱ አልፎ ሁሉም ወደቤት ገብተው ጠላ ሲጠጡ እኔ ሲተኩሱበት ወደነበረው ቦታ ሄድኩ።የጥይት ቀለህ ለቀማ ገብቼ አጎቴን መገናኘት ረሳሁት።የሰበሰብኳቸውን ቀለሀዎች ከቂጥ ከቂጣቸው ላይ እየነደልኩ በገመድ አስገብቼ ከሁሉቱ እንቦሶች አንገት ላይ አሰርኩት።ጥጃ አንገት ላይ ‹‹ኪል ኪል›› የሚል ብረት ማስገባት በዚያን ዘመንና ቦታ የተለመደ ነበር።

የአጎቴ ልጆች ‹‹አባት አልባ እንሆናለን›› የሚለው ስጋታቸው በአባታቸው መምጣት ስለተቀረፈ ቤታቸው ደስታ በደስታ ሆነ።እኛ ቤት ግን ያባታችን መቅረት ሳያንስ ከአምስት ዓመት በኋላ ሌላ ሀዘን መጣብን።

ከቤታችን እኔ ሰባተኛ ልጅ ስሆን የመጀመሪያው ልጅ ብቻ የአስኮላ ትምህርት ይማራል።‹‹ወንድም ጋሼ›› እንለዋለን።ወንድም ጋሼ በአገልግል እንጀራ ለሳምንት የሚሆነውን እየወሰደ ደብረ ታቦር ቤት ተከራይቶ ነበር የሚማረው።ኢህአፓ ነህ ብለው የደረግ ሚሊሻዎች ይዘው በምላሱ ስር ቀደው በአገጩ ገመድ አስገብተው አንጠልጠሉት።በስቅይት ብዛት ሚስጢር ያወጣል ብለው ቢያሰቃዩትም የነገራቸው ነገር ያለ አይመስለኝም።በመጨረሻ ሰኞ ገበያ ላይ በድጋሚ ሰቀሉት።ሞቶ እንኳ ሬሳውን ‹‹ወንድምጋሽን›› ያየ እንዲፈራ ሬሳውን ከአጅባር እስከ መሎ ድረስ ከተማ መሀል ለመሃል ይጎትቱት ነበር አለ።

እናቴን ‹‹ነይ አስከሬንሽን ውሰጂ›› የሚል መልዕክት ላምባ (ኩራዝ የሚያበራ ነዳጅ) ሊገዛ ከተማ ከሄደ ሰው መጣላት።እርር ብዬ አለቀስኩ።እናቴ መሬት ለመሬት እየተንከባለለች ፊቷን ሁሉ እየነጨች አነባች።አባት የለንም፤ ብቸኛ ወንድማችንንም በዚህ መልኩ ተነጠቅን።

አንድያ ወንድሜን አጣሁት።ከኔ በላይም በታችም ያሉት ሁሉም ሴቶች ናቸው።ከዚያ በኋላ ከሰው ጋር ስጣላ ‹‹ለወንድም ጋሽ እናገራለሁ›› እያልኩ የሚያሽንፉኝን ሰዎች መናገር አቆምኩ እንጅ የልጅ ነገር እንዲሉ ረሳሁት።

የሚገርመው ግን በትውልድ ቿረት ቤተሰቦቻችን በጦርነት ማለቃቸው ነው።አባቴ ሲል እንደሰማሁት አባቱ (አያቴ) በጣሊያን ወረራ ዘመን ከራስ ካሳ ጦር ጋር ዘመቶ በክብር ለሀገሩና ለሰንደቅ ዓላማው ህይወቱን ሰውቷል።አያቴ ሀገሩን ለማስከበር በአደረገው ህይወቱን አጥቷል፣ አባቴም ለተመሳሳይ ዓላማ የደረሰበት አልታወቀም።እስካሁን ግን ግልጽ ያልሆነልኝ ወንድሜ የተሰዋለት ነው።

(ከእኛ ቤት እልፍ ብሎ አንድ ትልቅ ገደል አለ።ከደብረ ታቦር ከተማ የአንድ ሰዓት ጉዞ ሳብ ቢል ነው።ገደሉ ‹አባት መጣያ› ይባላል።ማናቸውም ፍጥረት ከብትም ሆነ ሰው በዚያ ገደል ከገባ በህይወት ዳግም አይገኝም።በቀያችን ያሉ ሰዎች ሁሉም ከህጻን እስከ አዋቂ የገደሉን ስያሜ ትውፊት ተመሳሳይ በሆኑ መልኩ እርግጠኛ ሆነው ይናገራሉ።በድሮ ዘመን ከገደሉ አጠገብ የሚኖር ሰው ነበር።አንድ በእድሜ ሽማግሌ የሆነ ‹ተጠዋሪ› አባትም ነበረው።ይህ ልጅ ግን አባቱን ያለምንም ስራ መመገብ አንገሽገሸውና ለሽማግሌው አባቱ ስራ አዘጋጀለት።ስራውም የጓሯቸውን በቆሎ (ማሽላ) ጦጣ እና ዝንጀሮ እየበላ ስላስቸገራቸው አዛውንቱ እንዲጠብቁ ተነገራቸው።አዘውንቱ ግን በቆሎ ሊጠብቁ ከተቀመጡበት ጥላ ስር እንዳሉ እንቅልፍ ወሰዳቸው።የጦጣ እና የዝንጀሮ መንጋ መጥቶ ጓሮውን አወደመው።ልጅየው መጥቶ ሲመለከት አባት ተኝቶ ጓሮው ደግሞ ወድሞ አገኘው።ከዚያም ተናዶ አባቱን ወደ ገደሉ ወሰዶ

‹‹ምን ሰርተህ ልትበላ ነው!›› ብሎ ሊጥለው ሲል ኣዛውነቱ አባት እንዲህ አሉት ‹‹ልጄ የእጅህን አትጣው››።ከዚያ በኋላ ልጅም አባቱን በገደሉ ሳይወረውር ተዋቸው።ነገር ግን ልጅየውም ሲያረጅ የገዛ ልጁ በተመሳሳይ መልኩ ወደዚያው ገደል ሊጥለው ሲል ‹‹ልጅ አንተ ይህን የምትሰራውን ስራ እኔም በአባቴ ላይ እድርጌ ነበር።አንተም የእጅህን አትጣው›› ብሎ ረገመው።ይህ እርግማን እስከ አምስት ትውልድ እንደ ደረሰ ይነገራል።

ይህን ተረት/ታሪክ የምነግራችሁ የዘመዶቼ ተመሳሳይ ከቅደመ አያት የመጣ ተመሳሳይ አሟሟት ታሪክ ነው።ምናልባት በአገር ነጻነት ላይ መሞትም እንደዚህ እርግማን ይሆን እንዴ?)

ጊዜ እየሄደ ጦርነቱም እያየለ መጣ።የሚገለባበጡት የጦር ሚጎች የእኛ ሰፈር መለማመጃቸው ይመስል ሰማዩን ሲያርሱት ይሰነብታሉ።ሁሌ የሚወራው ጦርነቱ ‹‹ዛሬ ጉና ደርሷል!›› እያለ ሲያወራ ሌላው ደግሞ ‹‹የለም የለም ክምር ድንጋይን አልፎ ጋሳይን ሁሉ ታጋዮቹ ተቆጣጥረውታል አሉ›› ይላል ሌላኛው።ሶስተኛው ደግሞ ‹‹ኧረ ወያኔዎቹ በጣም አይለዋል አሉ።በቆረጣ እዚህ አለምሳጋ ጫካ ውስጥ አድፍጠዋል እየተባለ ነው።›› ወያኔና ታጋይ የህወሓት ጦር መጠሪያ ስሞች ናቸው።

ክፉ ዘመን ከመጣ፣ የዓለም ፍጻሜን ጨምሮ ‹ክበብ› ያለችው ‹ቆልማሚት ብሳና› መሬት ትነካለች ስለሚባል ሁልጊዜ የጠዋት ጠዋት ስራችን ‹ቆልማሚት›ን ያለችበትን ሁኔታ መጎብኘት ነበር።በታምር መሬት ነክታ ቢሆንስ! እያልን።

(የጸሀፊው ማስታዎሻ፡- ክበብ የሚሉት የአጼ ሱስንዮስ ቤተ መንግስት እንደነበር የሚነገርለትን ግንብ ነው።ግንቡ ደንቀዝ ከሚገኘው የሱስንዮስ ግንብ (ቤተ መንግስት) ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው።ቦታው ከደ/ ታቦር ከተማ 8 ኪሎ ሜትር ገደማ ወደ ምዕራብ ያስኬዳል።ልዩ ስሙ አሪንጎ አቦ ይባላል።ታዋቂው የታሪክ ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስትም ስለዚህ ቦታ ጽፈዋል።አጼ ሱስንዮስ (ከ1608-32 እ.ኤ.አ) የነገሱ ንጉሥ ሲሆኑ ከዚህ ቦታ ለተወሰነ ጊዜ እንደነበሩ የታሪክ ድርሳናት ያሳያሉ።ንጉሱ ኮትልከው (ካቶሊክ ሆነው) ብዙ ሰውም ያስፈጁት ከዚሁ ቦታ ነው።አንዲት ፍቅርተ ክርስቶስ የተባለች ሠማዕትም ከዚሁ ቦታ እንደተሰዋች ገድሏ ያሳያል።ይህች ሠማዕት አሁን በወሎና በጎንደር መካከል ገዳም አላት።እማሙዝ/ ፍቅርተ ክርስቶስ ገዳም ይባላል።ቤተ ክርስቲያኒቱ የተሰራችው ከስሚዛ ዛፍ ሲሆን እስከእለተ ምጻትም እንደማይፈርስ ገድሏ ይናገራል (ገድለ ፍቅረተ ክርስቶስ ይመልከቱ)።ከዚሁ ያሉ ብዙ ታሪካዊ ነገሮች አይቻለሁ።ወንዙ አጤ ውሃ ይሉታል።የንጉሱ መሆኑን ለመግለጽ ይመስላል።የነገስታቱ ልብስ የሚታጠብበት ከአለት ተቀርቁሮ የተሰራ የድንጋይ ማጠቢያ (ጢሽት) እንዲሁም የተሰጣውን ልብስ ሌባ እንዳይወስደው መከላከያ አጥሩ እስካሁን ድረስ አለ።የድንጋዩን ማጠቢያ እስካሁን የአካባቢው ሰዎች በየተራ ይጠቀሙበታል።ወንዙ ልብስ ከሚታጠብበት ትንሽ እልፍ ብሎ ከ300 ሜትር በላይ የሚረዝም ፏፏቴ ፈጥሮ ከስር ሰይጣን ባህር ከሚሉት ላይ ያርፋል።ፏፏቴው በክረምት የወንዙ ውሃ ሲጨምር እጅግ በጣም ያምራል።አጼ ሱስንዮስን ስልጣን እንዲለቅ የተናገረችው ሴት ከዚህ ባህር ሌሊት ሌሊት ትጸልይ ነበር አሉ።እሷም የተናገረችው ‹ሱስንዮስ ይፍለስ፣ ፋሲል ይንገስ፤ የሮም ሀይማኖት ትርከስ፣የእስክንድር ሀይማኖት ትመለስ!!› የሚል ነበር አሉ።አዋጁ እንደታወጀ ምላሳቸው ተጎልጉሎ ወጥቶ የነበረው ሱስንዮስ ምላሳቸው ተመልሶ ንስሀ ገብተው እንደ ሞቱ እንዲሁም የፋሲል ንግስና 170 ኪሎ ሜትር ራቅ ብሎ ወደ ጎንደር እንደተዛወረ የአካባቢው የእድሜ ባለጸጎች ይናራሉ።አርባ አራቱ የጎንደር አብያተ ክርስቲያናትም ከዚሁ ነበሩ።ብዙ የቤተ ክርስቲያን ፍርስራሽ ቦታዎች አሉ።ሁሉም የተገነቡበት ግንብ ከፋሲል ግንብ ጋር ተመሳሳይ ነው።አንዲት የነገስታቱ ውሃ መጠጫ የነበረች ሳትሆን አትቀርም በጣም ተፈጥሯዊ የሆነች ‹ትግዛ› የምትባል በክረምትም በበጋም የማትደርቅ ተመሳሳይ የውሃ ፍሰት ያላት ምንጭ አለች።አሁን ላይ ግን የአቦ/ የገብረ መንስ ቅዱስ ጸበል መቅጃ ብቻ ናት።ምንጩ ከሰው መኖሪያ ትንሽ ራቅ ያለ ቢሆንም ብዙ ሰው የውሃው ጣዕም ልዩ ነው በማለት እስካሁን ድረስ ጸበሉ ከሚቀዳበት ራቅ ብሎ የሚፈሰውን ሰዎች ይቀዱታል።የዘመን መለወጫ - የቅዱስ ዮሀንስ ሌሊት የአካባቢው ነዋሪ ህዝብ ውሃውን ወፍ ሳይቀምሰው (ወፎች ሳይነሱ) ይጠመቁበታል።ከብዙ በሽታም እንደተፈወሱ የሚናገሩ አሉ።በዚሁ አጋጣሚ ግን ግንቡ በገበሬዎች እየፈረሰ ስለሆነ የክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ጥበቃ እንዲያደርግለት ማሳሰብ አስፈላጊ ነው።

ወደ ቆልማሚት ብሳና ታሪክ ስመጣ ደግሞ ያነጋገርኳቸው ሰዎች በሚከተለው መልኩ ገልጸውታል።አጼ ሱስንዮስ ሰውነታቸው በሙሉ ጸጉር ነበር።ንጉሱ ሲበዛ ሴሰኛ እንደነበሩም ይነገራል።በየቀኑ አንዳንድ ሴት በየደብሩ እየተመረጠች ለንጉሡ ትመጣለች።ሲነጋ የንጉሡን ሰውነት በጸጉር መሸፈን እንዳታወራ ተገድላ ከአንዲት ብሳና ስር ሁሉም ይቀበራሉ።ይህ በየቀኑ የሚፈጸም ነው።ብሳናዋ ወደ ላይ ቀጥ ብላ ከወጣች በኋላ ሴቶቹ ወደሚቀበሩበት ቦታ በሀዘን አጎነበሰች።መሬት ልትነካ በአንድ ሰው ቁመት ልክ ሲቀራት እንደገና አግድም ማደግ ጀመረች።/ከዚህ ቦታ የሚቀበሩት ሴቶቹ ብቻ ሳይሆኑ ካቶሊክ አንሆንም የሚሉ ሰማዕታት ጭምር እንደሆኑ የሚናገሩም አሉ።የንጉሡን ወደ ፈረንጅ ሀይማኖት መለወጥ ዜና መዋዕላቸው ደጋግሞ ገልጾታል።/ ብሳናዋ የምታመለክትበት አቅጣጫ ያለው ሰፈር እስካሁን ድረስ አዘኔ ይባላል።የሰዎቹ መቀበሪያ ነበር የተባለው ቦታ አሁን ድረስ ጎድጎድ ያለ ነው።እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስም እህል አያበቅልም ነበር።የሆነው ሆኖ በ993/4 ዓ.ም. ‹ቆልማሚት› መሬት ሳትነካ ወድቃለች።መሬት ነክታ ቢሆን እውነት ክፉ ዘመን ይመጣ ነበር! ቆልማሚት ሳትመልሠው ሂዳለች።

እንዲህ አይነት ንግር በብዙ ቦታዎች አለ።ለምሳሌ ጎንደር ጃንተክል ዋርካ አለ።ከቀደሙት ነገስታት አንዱ ሳይተክለው እንዳልቀረ ይነገራል።ጃን - ራስ (ጃን ሆይ) የነገስታቱ መጠሪያ በመሆኑ።የጃንተከል ዋርካ ቅርጫፎች መሬት የነኩ ጊዜ ‹ሴቶች ሁሉ ይባልጋሉ› የሚባል ንግርት እንዳለ ጎንደር የሄደ ሁሉ ይሰማል።የንግርቱን መስራት አለመስራት ዋርካው መሬት እስከሚነካ መጠበቅ ግድ ይላል።)

(በሚቀጥለው ሳምንት ይቀጥላል)

## እኔን ...

ከገጽ 12 የዞረ

ትብብር ቢያስፈልግም በተለይ በግንባር ቀደምትነት እናንተ ሀብታችሁን ገንዘባችሁን እያፈሰሳችሁ በበጎ ተግባራት አርያ መሆን ይገባችሁዋል፤ ካልሆነ የትውልድን ጥፋት ኃላፊነት በጎደለው መልኩ የምትደግፍ ከሆነ፤ ሀገሪቱ ከእናንተ የምታገኘው ጥቅም በጉዳት ከተተካ በሀገሩ ፖለቲካዊ, ኢኮኖሚያዊ, ማህበራዊ, ታሪካዊ እና ወቅታዊ ጉዳዮች ንቁ ተሳትፎ ሳያደርግ በአውሮፓ እግር ኳስ ናፍቆት እንዲኮበልሉ ራሳቸውን ሀገራቸውን እንዲርሱ በማድረግ የጥፋቱ አንድ አካል እንደሆናችሁ ልታውቁ ይገባል አስረግጬም ልነግራችሁ እወዳለሁ፡ ፡ በእናንተ ገንዘብ ውሻ ከሰው የተሻለ ክብር እንዲያገኝ እየተደረገ ያለበት ወቅት ላይ ነን፡፡ በአርዕያ እግዚአብሄር ለተፈጠረ የሰው ልጅ የሞራል ልዕልዕና ቅድሚያ ስጡ ይህ ካልሆነ ማግኘታችሁ ከማጣታችሁ አይሻልምና ሀገራችሁን ወገናችሁን አስቡ፡፡

ሰውን የሚያከብር ሚዲያ ባለሀብት እንጂ ለውሻ የገንዘብ ስጦታ እያደረጉ ወገኖቻቸውን የረሱ ባለሀብቶች በአፍንጫችን ይውጡ፡፡ ጋዜጠኞቻችን እናንተም ብዙ ህዝብ በሚያደምጠው ጣቢያ ቀርቦ ውሻን ሙዚቃ ጋብዞ ማስጨፈር የውሻ ህይወት ታሪክ አፍ ከፍቶ ማዳመጥ ለውሻ ሽልማት መስጠት ኃላፊነት የጎደለው ተግባር ነው፡፡አሁን ወገኖቻችሁ ያሉበትን ሁኔታ ማሰብ ካልቻላችሁ እናንተም አንደዚየው.............................፡፡ ለዛሬ እኔን እርር ድብን አድረገው ያበሸቁኝ እነዚህ ናቸው እናንተንስ?????????

# ልማታዊ መንግስት-እንደ ቻይና፤ ነገሩስ ባልከፋ

ደስታው አንዳርጌ (ዶ/ር)

እስያውያን፤ በተለይም ደግሞ ሀገረ ቻይና ለብዙ ድሃ አገራት አርዓያ የሚያደርጓት ብዙ ምክንያቶች አሉ/ዋት። በዋነኝነት ግን ቻይና ከሌሎቹ የእስያ አገራት በተቃራኒ ተዓምራዊ እድገት ያስመዘገበችው በምዕራባውያን ድጋፍ ሳይሆን ከምዕራባውያን ፍላጎት በተቃራኒ መሆኑ ነው። ምዕራባውያን እንደነ ጃፓን፣ ታይዋን፣ ደቡብ ኮሪያ የመሳሰሉትን አገራት ለመደገፍ ግልጽ ጅኦፖለቲካዊ ምክንያት አላቸው። ቻይናን ግን ቢችሉ ቢኮረኩሟት ይወዳሉ። በቻሉት መጠን ሲኮረኩሟትም ብዙ ጊዜ አይተናል። ምሳሌ ላቅርብ፤ ባለፉት ፴ አመታት ቻይና ብቻዋን ከድህነት ማጥ ያወጣችው ህዝብ ቁጥር ሌላው አለም ባጠቃላይ ተደምሮ ካደረገው ሁሉ ይበልጣል። ይህ ምናልባትም በታሪክ አቻ የሌለው ስኬት ነው። በአንጻሩ የጦር መሳሪያ በመሸመት በአለም ተወዳዳሪ የሌላት ሕንድ አንድ ሦስተኛው ህዝቧ በየቀኑ በርሀብ አለንጋ ይገረፋል። ከዚህ በላይ የሰብአዊ መብት መጓደል የለም። ምእራባዊያን መንግስታትና ተመሳሳይ የፖለቲካ አጀንዳ ያላቸው ምዕራባዊያን 'የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች' ግን ህንድ ውስጥ በሚሊዮን የሚቆጠር ህዝብ ያላግባብ (በነገራችን ላይ አገሪቱ ብዙ ሚሊዮን ቶን ትርፍ የምግብ እህል ታመርታለች)በርሃብ ሲረግፍ ሳይሆን ቻይና ውስጥ አንድ ተቃዋሚ ሲታሰር ነው ሰብአዊ መብት ትዝ የሚላቸው። እውነቱ ግን ቻይና ከሰብአዊ መብት ኣንጻር እንኳን ቢታይ ከብዙ አገራት (ከብዙ ምዕራባዊያንም ጭምር) የተሻለ ሪኮርድ ነው ያላት። ስለሆነም በተለይ እንዳሁኑ አቅሟ ሳይፈረጥም በሚደርስባት ተፅእኖ ሳትበገር ለስኬት በመብቃቷ ቻይና በራስ የመተማመንና በጥረት ለስኬት የመብቃት ተምሳሌት ተደርጋ ብትወሰድ አግባብ ነው። ከዚህ አንጻር እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ድሀ አገራት የቻይናን አርዓያነት ቢከተሉ በመሰረቱ ችግር አይመስለኝም። ችግሩ ቻይና እና ሌሎች እስያውያን የታደሉት ኢትዮጵያ የጎደላት በርካታ ቁም ነገሮች መኖራቸው ላይ ይመስለኛል። የአንድን አገር ብልጽግና ከሚወስኑት ዋና ዋና ጉዳዮች ግንባር ቀደሞቹ፤ ብቃትና ተአማኒነት ያለው የፖለቲካ አመራር፣ የዜጎች ሳይንሳዊነት፣ የአገር ፍቅርና የሃላፊነት ስሜት፣ የመቻቻልና የመተባበር መንፈስ፣ ታታሪነትና ተወዳዳሪነት ይመስሉኛል። የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በእነዚህ ሚዛኖች እንየው፤

### ሀ. ተአማኒነት ያለው የፖለቲካ አመራር

ስኬታማወቹ የእስያ አገራት መንግስታት ሁሉም (ያለምንም ልዩነት) የሚያመሳስላቸው ቢኖር ጠንካራ ብሄርተኞች መሆናቸው ነው። ለምሳሌ ከቻይና ጋር ወዳጅነት የሚፈልግ መንግስት ሁሉ በመጀመሪያ 'አንድ ቻይና' የሚል መፈክር ማሰማት ይጠበቅበታል። ለ 'አንድ ቻይና' እውቅና ሳይሰጥ ከቻይና ጋር መልካም ግንኙነት ያለው መንግስት የለም (ስለሆነም ታይዋን በጣም የበለጸገች ዲምክራሲያዊና የተረጋጋች አገር ብትሆንም ለዘመናት ከጥቃቅን የፓስፊክ ደሴት አገሮች ውጭ እውቅና የሰጣት ብዙም አገር የለም)። ጠንካራ ብሄርተኝነት ማለት ይህ ነው። ብሄርተኝነት የጎሰኝነት ተቃራኒ ነው፤ አንዱ ሲገን ሌላው ይቀጭጫል። ብሄርተኝነት አንድነትን ማጽናት ሲሆን ጎሰኝነት በተቃራኒው አንድነትን መሸርሸር፣ ልዩነትን መስበክ ነው። ብሄርተኝነት እንደዝንጀሮ በጎሳ ከመቧደን ወጥቶ እንደሰለጠኑት ሕዝቦች ዘመን በሚሻገሩ ሀሳቦችና ዘላቂ የጋራ ጥቅም ዙሪያ መተባበር ማለት ነው። ብሄርተኝነት ከፖለቲካ በላይ ነው። ተወደደም ተጠላም የአለም ህዝብ የተዋቀረው በሉአላዊ አገራት ነው። በአንድ ሉአላዊ አገር ውስጥ የሚኖሩ ህዝቦች ደግሞ እጣቸው የተሳሰረ ነው። ከፖለቲካ በላይ የሆኑ ጉዳዮች የግድ አንድ ያረጓቸዋል። የፈለገው ስልጣንና ገንዘብ ይኑርህ በኢትዮጵያዊነትህ ትለካለህ። አንድ ጊዜ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ጂ፰ ስብሰባ ላይ ይመስለኛል የሚያናግረው አጥቶ ሲቁለጨለጭ አይተናል። አንዳንድ የዋህ ኢትዮጵያውያን መለስን ስለሚጠሉ ብቻ በሁኔታው ቀልደዋል። ነገር ግን መለስ ከጆርጅ ቡሽ ያነሰ ፖለቲከኛ ስለሆነ አልነበረም የሚያናግረው የጠፋው፤ የደሀና ለማኝ አገር መሪ ስለሆነ እንጂ። በሌላ አነጋገር የተዋረደው መለስ ሳይሆን ኢትዮጵያዊነት ነው። የአገር መሪም ብትሆን በደሀ አገርህ ሚዛን ነው የምትታየው። የትም አገር ሂድ የየትኛው ጎሳ አባል መሆንህ ግድ የሚሰጠው የለም።

ብሄርተኝነት ፖለቲካዊ ችግሮች ቢኖሩም እንኳን ከፖሊቲካ በላይ በሆኑ አገራዊ ጉዳዮች ላይ አንድ መሆን ማለት ነው። ብሄርተኝነት ለየትኛውም የውጭ ሀይል በር አለመስጠት ማለት ነው። ብሄርተኝነት እንኳን የኢትዮጵያን ጥፋት ከሚመኙ (ሻአቢያን ከመሰሉ) ሀይሎች ይቅርና ኢትዮጵያ ውስጥ ሰብአዊ መብት እንዲከበር እንታገላለን ከሚሉን የውጭ ሀይሎች (ሃሳዊ መሳዮች) ጋር አለማበር ማለት ነው። ብሄርተኝነት የአሜሪካ መንግስት ወያኔን እንዲያስታግስልህ አለመማጸንም ነው። ብሄርተኝነት እንደ ቻይና በራስ መተማመን ነው። ብሄርተኝነት እኛ ኢትዮጵያውያን የራሳችን ችግሮች ራሳችን መፍታት እንችላለን ብሎ ከልብ ማመን ነው። ብሄርተኝነት ያለጥርጥር ሀይል ነው (በጣም ተለጥጦ ወደእብሪት እስካልሄደ ድረስ)። ከነቻይናና ሌሎች እስያውያን ስኬት ጀርባ ያለው አንዱ ሚስጥር ይህ ሃይል ነው። ወደኛ ስንመጣ ከብሄርተኝነት ይልቅ ጎሰኝነትን ለማጉላት የሚተጋ መንግስት ነው ያለን። ጎሰኛ መንግስት ደግሞ ኢትዮጵያውያንን ሁሉ አስተባብሮ እንደቻይና ተአምር ለመስራት ዕድል የለውም። አብዛኛው ተቃዋሚም ቢሆን አንጋጦ የውጭ አዳኝ (ኤክስተርናል ሳልቬሽን) የሚጠብቅ ነው። በኢትዮጵያውያን ህዝብ ሀይል(ኤጀንሲ)ሳይሆን በሃሳባዊ የውጭ ድጋፍ የሚተማመነው ይበዛል። ለመረጣቸው ህዝብ ጊዜ ያልነበራቸው የቅንጅት መሪወች ከእስር በተፈቱ ማግስት ወደውጭ ለመፈርጠጥ እንዴት እንደተራወጡ ማስታወስ ብቻ በቂ ነው።

ሌላው ቻይና ውስጥ የፓርቲ አምባገነንነት እንጅ የግለሰብ አምባገነንነት የለም። የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ አመራር በየጊዜው በሚደረግ ምርጫ ይቀየራል። ያ ደግሞ ተጠያቂነት እዲኖር ያደርጋል። ከምንም በላይ የቻይና መንግስት ሊብራል ባይሆንም ጨዋ(ዲሰንት)መሆኑ አይካድም። ወደኛ ስንመጣ ሊብራሊዝምን በታሪካችን አናውቀውም። ጨዋ(ስልጡን) መንግስታት ግን ነበሩን። ለምሣሌ በንጉሱ ዘመን ተማሪዎች ፊውዳሊዝም ይውደም እያሉ ሲፎክሩ የጸጥታ ሀይሎች በሰለጠነው አለም እንደምናየው መስመራቸውን ጠብቀው ሁኔታውን ይከታተላሉ እንጅ በጥይት ጭንቅላት ሲመቱ አልታዩም። በአጠቃላይ በንጉሱ ረጅም የስልጣን ዘመን በፖለቲካ ምክንያት ያለፍርድ የተገደሉት ሰዎች በጣት ይቆጠራሉ። ደርግ ሲመጣ ያ ጨዋነት ገደል ገባ። ቢሆንም የደርግ ሹማምንቶች አገር ሸጠዋል ወይ ደግሞ ሚሊዮን ብር ዘርፈው ወደ ውጭ አሸሽተዋል ያላቸው የለም። ስለዚህ ቢያንስ የሚታመኑበት አንድ ሁለት ጉዳዮች ነበሯቸው ማለት ነው። ህወሃት/ኢህአዴግን ግን ይህን አያደርግም ብሎ የሚወራረድ አይገኝም።

### ለ. ሳይንሳዊነት (እውቀትና ዕምነት)

የሰውልጅ ታሪክ ረጅም ነው። የኢኮኖሚ ብልጽግና ታሪክ ግን ግፋ ቢል ከሁለት መቶ ዓመት አይዘልም። አብዛኛው የሰውልጅ ታሪክ የድህነተና የጉስቁልና ነው። ከስምንት ሺ አመት በፊት (ኒኦሌቲክ ዘመን በሚባለው) ጊዜ የሰው ልጅ አደንና ፍራፍሬ ለቀማን ትቶ እርሻ እንደጀመረ ይታመናል። ከተሞች ተቆረቆሩ፤ ንግድም ተጀመረ። ይሁን እንጅ ረሀብና ቸነፈር በየጊዜው ይጨርሰው ስለነበር የአለም ህዝብ ቁጥር ፩ ቢሊዮን የሞላው ከብዙ ሺ አመታት በኋላ በ1800 ዓ.ም አካባቢ ነው። ከዚያ ግን ፪ ቢሊዮን ለመሙላት 123 አመታትን ነው የፈጀበት። ፫ ቢሊዮን ለመሙላት ደግሞ 33 አመታትን ብቻ። ይህ የሆነው በተአምር አይደለም። በተለይ የአውሮፓውያንን የኢንዱስትሪ አብዮት ተከትሎ ለበርካታ በሽታዎች መድሃኒት መስራት በመቻሉና ለህይወት አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮችን በዋንኛነት ምግብን በቀላሉ ማምረት በመቻሉ እንጂ። ባጭሩ በሰውልጅ ረጅም የጉስቁልና ታሪክና አጭር የብልጽግና ጉዞ መካከል ያለው ልዩነት አንድ ብቻ ነው፤ ሳይንስ። ርግጥ ነው፤ ሳይንስ ለጥፋትም ሊውል ይችላል። ነገር ግን ወደ እውቀትና እድገት የሚያደርሰው መንገድ ሳይንስ ብቻ ነው።

እድገት በምትሀት አይመጣም። ለምሳሌ ስለተዓምራዊ የኢኮኖሚ እድገት ሲነሳ ጃፓን በግንባርቀደምትነት ትጠቀሳለች። ርግጥ ነው ጃፓን በሁለተኛው የአለም ጦርነት ዶግ አመድ ሆና ነበር። ብዙዎቻችን ስለ ሂሮሽማና ናጋሳኪ ሰምተናል። ነገር ግን የጃፓን ዋና ዋና ከተሞች በሞላ በኢንሴንዲሪ ቦምብ ጋይተው በአገሩ መጠለያ፣ የሚላስ-የሚቀመስ ጠፍቶ ነበር። ይሁን እንጅ ጃፓናዊያን አገራቸውን መልሶ መገንባት ብቻ ሳይሆን በአለም ሁለተኛዋ ታላቅ ኢኮኖሚ ለማድረግ የፈጀባቸው ሶስት አስርት አመታት ብቻ ነበር። ይህ የሆነው ግን እንደሚባለው በተአምር ሳይሆን ጃፓናውያን ምናልባትም በአለም ላይ አቻ የሌለው የአገር ፍቅርና ታታሪነት የታደሉ ብቻ ሳይሆኑ በሳይንሳዊ እውቀት የበለጸጉ ስለሆኑ ነው። በ 19ነኛው መቶ ክፍለዘመን እንኳን ጃፓን ከአውሮፓውያን (ይህ ማለት ከአለም)የላቀ የእውቀት ብርሀን (ሊትሬሲ ሬት) ነበራቸው። በተመሳሳይ ዛሬ ሁሉም ሰው ስለ ቻይና ተዓምራዊ እድገት ያወራል። ብዙ ሰው ግን ቻይና ኢኮኖሚዋ ከመተኮሱ ከአርባና አምሳ አመት በፊት እጂግ ግዙፍ የተማረ የሰው ሀይል እንደነበራት ይዘነጋል። እድገት የሚጀምርው ከሰወች አስተሳሰብ ነው። የአንድ አገር ህዝብ ሳይንሳዊ እውቀት ከታጠቀ፣ የአገር ፍቅር፣ የመተባበር መንፈስ፣ ታታሪነት፣ መቻቻልን ከተጎናጸፈ መንገዱና ህንጻው ዝርዝር ጉዳይ ነው፤ በአጭር ጊዜ የሚደርስ። እስያውያን ለሳይንስ በጣም ቅርብ ናቸው።

ወደኛ ስንመጣ በመጀመሪያ ስለሳይንስም ስለእድገትም ያለን ግንዛቤ ግራ ያጋባል። በልመና ገንዘብ በልመና ባለሞያ የተሰራ ህንጻ የእድገት ምልክት የሚመስለን ብዙ ነን። ዱቄት መለመን ራሱ ሞት ነው። ጋጋሪ መለመን ግን የሞት ሞት ነው። እኛ ግን ዱቄት ለምነን፤ ጋጋሪ ለምነን ባስጋገርነው ቂጣ ተዓምር የፈጠርን ያህል አገር አይብቃን ስንል ሀፍረት እንኳን አይሰማንም። ከእውቀትና ከእውነት ጋር ተጣልተን የምንኖር ይመስለኛል። ድርቅ ያለ እውነት አንወድም። ፕሮፌሰር መስፍን አንድ ጊዜ አበሻ ስንት ልጆች አሉህ ብትለው ክብሩ ይስፋ ሁለት ሶስት አሉኝ እንጂ ሁለት ወይም ሶስት ብሎ ርግጡን አይናገርም ያሉት ትዝ ይለኛል። ሪኮርድ አንወድም። ሌላው ቀርቶ እድሜያችን እንኳን ስንጠየቅ የምንደናገጥ ብዙዎቻችን ነን። ለአበሻ ሁሉ ነገር የእምነትና የምልኪ ጉዳይ ነው። ሽዎች በየጊዜው በርሀብ የሚረግፉባት አገር እየኖርን 'ፈጣሪ የከፈተውን ጉሮሮ ሳይዘጋው አያድርም' እያልን የምንቀልድ ጀግኖች እኮ ነን። ለምን እንደሆነ አላውቅም በምናየው ነገር አናምንም፤ ወይም የምናየውን አናስተውልም። ተምረንም ከሳይንሳዊ አስተሳሰብ ጋር ብዙም አንላመድም።

### ሐ. የአገር ፍቅርና የሃላፊነት ስሜት

መንግስትን ማማት በጣም ቀላል ነው፤ የሚቸግረው ራስን መጠየቅ ነው። ባላፉት በርካታ አመታት ኢትዮጵያ ውስጥ የተወጠኑ ጅምሮች ሁሉም ማለት ይቻላል ከሽፈዋል(የፕሮፌሰሩን ቃል ልዋስና)። ችግራችን ፖሊቲካዊ ቢሆን ኑሮ ይህ ባልሆነ። ቢያንስ ፖለቲካዊ ያልሆኑ ጉዳዮች ለምን ይከሽፋሉ? እንዲያውም የኢትየጵያ (በአጠቃላይ የአፍሪካ) ችግር በመሰረቱ ፖለቲካዊ አይመስልም። ችግሩ ፖሊቲካዊ ቢሆን ኑሮ "ናጽነትን መረጡ" የተባሉት ወገኖቻችን አሁንም "ናጽነት" ላም አለኝ በሰማይ ባልሆነባቸው ነበር። የአንድ አገር ፖለቲካ ከዚያ አገር ህዝብ ተጨባጭ ሁኔታ (ማለትም ታሪክ፣ባህል፣ አስተሳሰብ፣ ስልጣኔ፣ ወዘተ)ውጭ ሊሆን አይችልም። ኢህአዴግ ተቃዋሚዎችን አይታገስም ስንል በታሪካችን ነገስታት በተቀቡ ማግስት የመጀመሪያ ስራቸው ወንድሞቻቸውን አምባ ግሼን ማጎር መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል። ሌላው ቀርቶ በተቃዋሚው ጎራ ያሉት አንዳንዶቹ መሪዎች ያው እንደ ኢህአዴግ መሪወች ለ፳ ምናምን አመታት አልተቀየሩም። ብዙወቹ እንደወያኔ በመርህ ሳይሆን በቋንቋ የተደራጁ ናቸው። አመራራቸው በማያሻማ ሁኔታ ከሽፏል (ይህቺ ቃል ተመችታኛለች)፤ እነሱ ግን ቦታ አይለቁም። በወያኔ የመጀመሪያ ዓመታት እነ መለስ የባህር በር ከግመል ማጠጫነት ያለፈ ጥቅም የለውም ሲሉ፤ አወ ርግጥ ነው እያሉ ሲያጨበጭቡ የነበሩ አሁን ደግሞ ተቃዋሚ ነን የሚሉ ብዙወች እንዳሉም እናውቃለን። ሌሎቹ ደግሞ ከኢህአዴግ ጋር ሊሄዱ የሚችሉትን ያህል ሄደው ያሰቡትን ያህል ጥቅም አላገኙ ሲሉ ወይም ተፈላጊነታቸው ሲቀዘቅዝ ተገልብጠው ተቃዋሚ ነን የሚሉ ናቸው። ከዚያ በቃ ሲያጎበድዱላቸው የነበሩትን ጌቶቻቸውን ገመና ያለሀፍረት መቀባጠር ውርደት ሳይሆን ጀብዱ የሚመስላቸው ናቸው (በጣም የሚገርመው እንደነዚህ ያሉ ነውረኞች ሰሚ ያገኛሉ)። ጡረታ ሲወጣ ኢትዮጵያ ትዝ የምትለውም ብዙ ነው። ስለሆነም ባህላችን (በተለይም የሞራል እሴቶቻችን) መመርመር የሚያስፈልግ ይመስላል።

በጣም የሚቸግረን ሌላው ጉዳይ ደግሞ ለስራችን ሀላፊነት መውሰድ ነው። ሁልጊዜ ሃላፊነቱን ለሆነ አካል ነው የምናስተላልፈው። ቢቻል ደግሞ ያ አካል የማይታይ ቢሆን ይመረጣል። ለምሳሌ ሰውየው ሚስቱን አንቆ የገደላት ክፉ ወይም ደደብ ስለሆነ ሳይሆን ሰይጣን አሳስቶት ነው፤ ወይ ቀን ጥሎት። ያ ሁሉ ካልተሳካ ግን ሃላፊነቱን የግድ መንግስት መውሰድ ይኖርበታል። ሀላፊነቱን ለውጭ ሀይሎች ማስተላለፍም በኛ ቤት ችግር የለውም። ለምሳሌ ኢትዮጵያ ውስጥ ፍትህና ነጻነት እንዲኖር ማድረግ የአሜሪካ መንግስት ሀላፊነት ነው። በየጊዜው ዋሽንግተን ዲሲ የሚካሄደው ሰልፍ እኮ አላማው አሜሪካ ይህን ሀላፊነቷን እንዳትዘነጋ ለማስታወስ ነው። ፕሬዘደንት ኦባማ ምነው ከዳሽን አይነት ሮሮም በየጊዜው እንሰማለን፤ አፍሪካን ማስተካከል የፕሬዘደንቱ የቤት ስራ ይመስል። ድርቅ ብለን የኢትዮጵያ ጉዳይ ይመለከታችኋል የምንላቸው ሀይሎች መብዛታቸው! ሃላፊነቱ ለጠላት ማስተላለፍም ቢሆን ለኛ ችግር የለውም። ለምሳሌ ኢህአዴግ የበተናቸው የደርግ ሰራዊት አባላት ለደረሰባቸው ውርደት ራሳቸውን አይደለም የጠየቁት፤ ሃላፊነቱ የኢህአዴግ ነው። የአመራር ችግር ነው ወዘተ እያሉ ከሀላፊነት መሸሽ ይቻል ይሆናል፤ እውነቱ ግን


## ልዩ እና ሸንቋጭ የሆነ መጽሐፍ በገበያ ላይ!

‹‹ይህ መጽሐፍ የተሰናዳው ለሠርቶ አዳሪውም፣ ለአውደልዳዩም ( ካስፈለገም- ለዘረጦውም)፣ ለሀገር ተቆርቋሪውም፣ ለሀገር ሻጩም፣ ለወሽካታውም፣ ለእውነት ሟቹም፣ በአእምሮ ራቁትነት ለሚናጡ መሪዎችም (ወስላታ ተቃዋሚዎችን መሸንቆጡንና ‹መሪ› ማስጨበጡንም ሳይዘነጋ)… ነው። መጽሐፉን በማንበብ የሚኖረው የስሜት መለዋጥን የሚወስነው ግን የአንባቢው ማንነት ነው።ሰነፉም፣ ታታሪውም፣ ወሽካታውም እውነተኛውም… በአንድ ዐይነት ስሜት እንደማይቀበለው አውቃለሁ።›› ‹‹ስለሆነም መጽሐፉ ይዞት ከተነሣው ዓላማ አንጻር ‹የእናት ኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባኛል› የሚሉ አንባብያንን ጥያቄ ይመልሳል ብዬ ዐስባልሁ።…›› ሲል ደራሲው ኹለተኛ አብራኩ ስለሆነው ‹የከተማው አህያ› መጽሐፍ በፌስ ቡክ ገፁ ላይ አስፍሯል።

